**Cambridge Public Schools (የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች)**
**159 Thorndike Street, Cambridge, Massachusetts 02141**

---

# ኬምብሪጅ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች

# የመብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ

## ማውጫ

ክፍል ገጽ

1.0 ፖሊሲ ........ 1

2.0 መገኘት ........ 2

3.0 የግለሰብ ፍተሻ ........ 6

4.0 የተማሪዎች ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች፣ ጠረጴዛዎች እና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ........ 9

5.0 የግለሰብ ነጻነት ........ 10

6.0 ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት ........ 31

7.0 የመሰብሰብ ነጻነት ........ 33

8.0 የትምህርት ቤት መገልገያዎችን መጠቀም ........ 33

9.0 ያለባበስ ደንብ ........ 33

10.0 የኃይማኖት ነጻነት ........ 34

11.0 የተማሪ ጋብቻና እርግዝና ........ 35

12.0 የተማሪ አስተዳደር ........ 35

13.0 የቅጣት ፖሊሲና ሂደቶች ........ 35

14.0 ጊዜያዊ ማባረር ........ 37

15.0 ድንገተኛ ማስወጣት ........ 47

16.0 የጊዜያዊ ማስወጣት ምክክር ........ 48

17.0 ማስወጣቱን ይግባኝ ማለት ........ 51

18.0 የልዩ ትምህርት/504 ዕቅድ የቅጣት ሂደቶች ........ 53

19.0 የመባረር ፖሊሲ - የጦር መሳሪያዎች፣ አደንዛዥ ዕጾችና ድብደባዎች ........ 57

20.0 ከትምህርት ቤት ውጪ ምግባር ........ 67

21.0 ከትምህርት ቤት በወጡበት ጊዜ ትምህርታዊ አገልግሎቶችና የትምህርት ሂደት ........ 68

22.0 ማባረር ........ 69

23.0 የሙብት ንፍገትን ለማስተካከል ይግባኝ የማለት ሙብት ........ 70

24.0 የተማሪ መመሪያ መጽሐፎች ........ 72

ተጨማሪ መግለጫ ሀ ........ 73

**መብትና ኃላፊነት**

በኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተማሪ ሥነ ምግባር አስተዳደር

## 1.0 ፖሊሲ

1.1 የትምህርት ቤት ኮሚቴው በሥልጣኑ ሥር ያሉትን ተማሪዎች የሥነ ምግባር አስተዳደር ደንቦች አውጥቶ በጽሑፍ ያቀርባል።

1.2 በእነዚህ ደንብና መተዳደሪያዎች ውስጥ የተጠቀሟቸው የሚከተሉት ቃላቶች የሚከተሉትን ትርጉሞች ይዘዋል፦

ሀ. “ተማሪ” ማለት ማንኛውም በኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ሥልጣን ሥር በሚተዳደር የመንግሥት ትምህርት ቤት ውስጥ የተመዘገበ ዕድሜው በተማሪ ዕድሜ ያለ ሰው ነው።

ለ. “ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች” ማለት ተማሪው ዕድሜው 18 ሞልቶት በጽሑፍ የእነዚህ ደንቦችና መተዳደሪያዎች መብቶችና አቅርቦቶች ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ ተብዬው ካሁን በኋላ አይመልከተው/አይመልከታት ብሎ በጽሑፍ እስካላቀረበ/እስካላቀረበች ድረስ በስቴቱ ሕግ መሠረት የማንኛውም ተማሪ ወላጅ፣ አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ ነው።

1.3 የትምህርት ቤት ኮሚቴው በጽሑፍ ባቀረባቸው ደንቦችና መተዳደሪያዎች መሠረት፣ እያንዳንዱ ግለሰብ በኬምብሪጅ ውስጥ የመንግሥት ትምህርት ቤት የመሄድ መብት አለው።

1.4 የትምህርት ቤት ኮሚቴው ባወጣቸው ደንቦችና መተዳደሪያዎች ውስጥ ባሉት አመራርና ሂደቶች መሠረት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የትምህርት ቤት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ ወይም የትምህርት ቤት ኮሚቴ አባል ምንም ዓይነት የቅጣት እርምጃ ተማሪ ላይ መውሰድ አይችልም። የትምህርት ቤት ኮሚቴውን ደንቦችና መተዳደሪያዎች ሳይከተል የተወሰደ ማንኛውም የቅጣት እርምጃ የሚነሳና የሚወገድ ይሆናል።

1.5 እያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ ደንቦች ሥራ ላይ በሚውሉበት ወቅት የደንብና መተዳደሪያዎች ቅጂ ለእያንዳንዱ ተማሪ በነጻ ይቀርባል። የተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ማናቸውም እንፈልጋለን የሚሉ የማህበረሰብ አባላትም ቅጂዎቹን ማግኘት ይችላሉ።

1.6 ደንቦችና መተዳደሪያዎችን ለመጨረሻ ጊዜ ከማጽደቁና ከማተሙ ወይም ከማሻሻሉ በፊት፣ የትምህርት ቤት ኮሚቴው ሕዝቡ ፊት ጉዳዩን ያቀርባል። ጉዳዩ ከመቅረቡ ቢያንስ አንድ ሳምንት በፊት፣ የትምህርት ቤት ኮሚቴው በሐሳብ ደረጃ የቀረቡትን የደንቦቹን ቅጂ እንዲያቀርብ ጥያቄ ከቀረበለት ደንቦቹንና መተዳደሪያዎቹን ከማጽደቁ ወይም ከማሻሻሉ በፊት ቅጂ ያቀርባል። ጉዳዩ ከመቅረቡ ቢያንስ አንድ ሳምንት በፊት፣ የትምህርት ቤት ኮሚቴው በሐሳብ ደረጃ የቀረቡትን የደንቦቹን ቅጂ እንዲሁም ጉዳዩ የሚቀርብበትን ሰዓትና ቦታ ለተማሪዎችና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ያሳውቃል። በተጨማሪም የትምህርት ቤት ኮሚቴው የከተማው ጋዜጣ ላይ ጉድዩ ለሕዝብ እንደሚቀርብ ማስታወቂያ ያወጣል። የትምህርት ቤት ኮሚቴው ደንቦቹን በመጨረሻ ከማጽደቁ በፊት ጉዳዩ ለሕዝብ በቀረበበት ወቅት የተሰነዘሩትን አስተያየቶች ከግምት ያስገባል፣ ሆኖም በነሱ አይወሰንም። ደንቦቹ የሚጸድቁት በድምጽ ብልጫ ይሆናል።

1.7 የትምህርት ቤት ኮሚቴው እስከሚያጸድቃቸው፣ እስከሚያትማቸውና በትምህርት ቤት ማህበረሰብ ውስጥ እስከሚያሰራጫቸው ድረስ ማናቸውም ሕጎች፣ ደንቦች ወይም ማሻሻያዎች በሥራ ላይ አይውሉም።

1.8 በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ያሉት ደንቦችና መተዳደሪያዎች የሚመለከቱት በተለይ በትምህርት ቤት ኮሚቴው ሥልጣን ሥር የሚተዳደሩ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ ተማሪዎችን ሥነ ምግባርን ነው።

1.9 ተማሪዎች ሁሉ በኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚሰጡ ማናቸውም መርሃ ግብሮች ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ አዘጋጅቶ ማቅረብ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤት አንዱ መመሪያው ነው። ተማሪዎች፣ ሠራተኞችና ጎብኝዎች ትምህርት ቤት ውስጥ እስካሉ ወይም በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ በሚሆኑበት ወቅት ደህንነታቸው የተጠበቀ የመሆኑ ኃላፊነት የሁሉም ሠራተኛ ነው። የትምህርት ቤት መምሪያ ሠራተኞች ለደህንነት አስጊ የሆነ ሁኔታ(ዎች) በሚያጋጥማቸው ወቅት፣ አቅማቸው በሚፈቅደው መጠን ሁሉ ሌሎች ለጉዳት እንዳይጋለጡ ጥረው በመቀጠልም የተፈጠረውን ሁኔታ ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ማሳወቅ አለባቸው። ዋና ተቆጣጣሪው/ዋ ወይም ትወካዩ/ተወካይዋ አልፎ አልፎ የዚህን ፖሊሲ ዓላማዎች ሥራ ላይ ለማዋል የ"አስተዳደራዊ ሂደቶች" ማስታወቂያ ሊያወጣ/ልታወጣ ይችላል/ትችላለች።

## 2.0 መገኘት

2.1 ትምህርት በደንብ ለመማር፣ የተማሪዎችን ሁሉ ስኬታማነት ለማሻሻል፣ ትምህርት ቤት ውስጥ አክብሮት የተሞላ ባሕርይ ለማጎልበትና ተማሪ በትምህርት እንዲጎብዝ ዘላቂና ጽኑ በሆነ መንገድ ተማሪዎች ትምህርት ቤት መገኘት አለባቸው። የተማሪ መገኘት ፖሊሲ ዓላማ ተማሪዎች እለት ከእለት ጽኑ በሆነ መንገድ ትምህርት ቤትና ክፍል ውስጥ እንዲገኙ ለማበረታታት ነው። ተማሪዎች በሙሉ ቢያንስ ዘጠና አምስት በመቶውን (95%) ጊዜ ትምህርት ቤትና በክፍል ውስጥ እንዲገኙ ይጠበቅባቸዋል። ያለ በቂ ምክንያት ብዙ ጊዜ ከትምህርት ቤት የሚቀር ወይም የሚያረፍድ ተማሪ ይህንን ፖሊሲ ጥሷል ማለት ነው።

ሀ. አንድ ተማሪ የሚቀር ከሆነ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ትምህርት ቤቱ ጋር ደውለው ተማሪው እንደሚቀር ያንኑን ጠዋት ሳያሳልፉ ማሳወቅ አለባቸው።

ለ. ካልደወሉ፣ ተማሪው ትምህርት ቤት ሲመለስ ከወላጆቹ/ከአሳዳጊዎቹ፣ከተንከባካቢዎቹ ወይም ከዶክተሩ ተማሪው ለምን እንደቀረ የሚያብራራ በጽሑፍ የቀረበ ማስረጃ ይዞ መምጣት አለበት። ሆኖም ተማሪው ይህንን ይዞ ካልመጣ በትምህርት ሰዓት ወደቤት ተመልሶ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ማብራሪያ ይዞ እንዲመለስ አይደረግም።

ሐ. በሕመም ምክንያት ነው ተብሎ በተደጋጋሚ ወይም መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ተማሪዎች ከቀሩ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ኃላፊ ይህ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ከዶክተሩ ደብዳቤ እንዲቀርብ ሊጠይቅ/ልትጠይቅ ይችላል/ትችላለች።

መ. አንድ ተማሪ ለረጅም ጊዜ እንደሚቀር አስቀድሞ ከታወቀ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊውን ተገናኝተው ትምህርቱን ለማጠናቀቅ ምን ማድረግ እንዳለበት መጠየቅና አስፈላጊውን መሰናዶ ማድረግ አለባቸው።

ሠ. አንድ ተማሪ ሁልጊዜ ያለ በቂ ምክንያት የሚቀር ወይም የሚያረፍድ ከሆነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ተማሪው ትምህርት ቤት በተሻለ መንገድ መገኘት እንዲችል ከተማሪውና ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር አብሮ ዕቅድ ያወጣል። በተጨማሪም

ሁልጊዜ ያለ በቂ ምክንያት የሚቀር ወይም የሚያረፍድ ተማሪ ወደ Office of the Safety and Security (የደህንነት ጥበቃ ቢሮ) ይላካል። የደህንነት ጥበቃ ዳይሬክተሩ ከተገቢው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ጋር ምክክር ካደረገ በኋላ እያንዳንዱን ጉዳይ አይቶ ተገቢውን ማረሚያ ያስተላልፋል፣ ይህም አልፎ አልፎ ተማሪው በፍርድ ቤት ትእዛዝ ሥር ተጨማሪ አገልግሎቶች ያስፈልገዋል ተብሎ ከተገመተ ወደ Middlesex County Court (ሚድልሴክስ አውራጃ ፍርድ ቤት) መላክን ሊጨምር ይችላል።

በቂ ማስረጃ ያላቸው ምክንያቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

ሀ. ሕመም ወይም ተገልሎ መቆየት ካስፈለገ፣

ለ. እጅግ አሰቃቂ ገጠመኝ፣ ሐዘን፣ የቤተሰብ ሞት ወይም ቤተሰብ ውስጥ የጠና በሽታ ሲከሰት፣

ሐ. ሐይማኖታዊ በዓል ለማክበር ወይም አስቦ ለመዋል፣

መ. ከትምህርት ሰዓት ውጭ በጭራሽ ሊያዙ የማይችሉ የዶክተር ወይም የአማካሪ ቀጠሮዎች፣

ሠ. በግል መገኘት አስፈላጊ የሆነባቸው ሕግ ነክ ጉዳዮች፣

ረ. ከትምህርት ቤት ለጊዜው ወይም እስከመጨረሻ መባረር፣

ሰ. ከምትህርት ጋር የተያያዙ ጉዞዎችና ስብሰባዎች፣

ሸ. የኮሌጅ ጉብኝቶች (አሥራ አንደኛ ክፍል ላይ ሁለት ቀኖችና አሥራ ሁለተኛ ክፍል ላይ ሶስት ቀኖች)፣

ቀ. አንድ ተማሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባለበት ጊዜ ከአምስት ቀን በላይ የማይፈጅ አንድ ጉዞ ወይም ትምህርት ነክ ተሞክሮ ውስጥ መሳተፍ፣ ወይም

በ. የአየር ሁኔታው ልጁን አደጋ ላይ ወይም ሕመም ላይ የሚጥል ከሆነ።

የትምህርት ቤት አስተዳደሩ ከፈቀደ፣ በስድስት ወር ውስጥ ከሰባት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ አንድ ተማሪ በሌሎችም ልዩ ምክንያቶች ሊቀር ይችላል።

<u>በቂ ማስረጃ የሌላቸው ምክንያቶች:-</u>

ሀ. ከትምህርት ቤት፣ ከትምህርት ክፍሎች ወይም ከጥናት ክፍሎች ያለ በቂ ምክንያት መቅረት፣

ለ. የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው አስቀድሞ ፈቃድ ያልሰጠባቸው ጉዞዎች፣

ሐ. የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው አስቀድሞ ፈቃድ ሳይሰጥ ሥራ መፈለግ፣

መ. ፈተና ላለመፈተን ቤት መቅረት ወይም ለፈተና ለማጥናት ቤት መቅረት፣

ሠ. የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ቢሮ ውስጥ ሳይፈርሙ በትምህርት ሰዓት ከትምህርት ቤት ወጥቶ መሄድ፣

ረ. አርፍዶ መተኛት ወይም በሌላ መንገድ ከትምህርት ቤት ማርፈድ (ሶስት ጊዜ ያለምክንያት ማርፈድ እንደ አንድ መቅረት ይቆጠራል)፣

ሰ. ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ውጪ በአካባቢው ተገኝቶ ክፍል አለመግባት፣ ወይም

ሸ. ማንኛውም ሌላ ያለፈቃድ የመቅረት ሁኔታ ወይም በቂ ምክንያት ኖሮ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ግን ስልክ በመደወል ያላሳወቁት ወይም ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወይም ከዶክተሩ የጽሑፍ ማስረጃ ሳይዝ ከተመለሰ።

ተማሪው ትምህርት ቤት ባለበት ወቅት በአስተማሪዎችና በትምህርት ቤት ባለ ሥልጣኖች ቁጥጥር ሥር ስለሆነ፣ በጊዜ መሄድ ካስፈለገው ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊ ፈቃድ የማግኘት ግዴታ አለበት። ማንኛውም ከመሄዱ በፊት በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊ ቢሮ ውስጥ ሳይፈርም የሚሄድ ተማሪ ይቅርታ አይደረግለትም እንዲሁም ለሚያመልጠው ትምህርቶችና ሥራዎች ነጥብ አያገኝም። እያንዳንዱ አስተማሪ የሚቀሩና የሚያረፍዱ ተማሪዎችን መዝገብ ይይዛል። ማንኛውም የትምህርት ሰዓት ከተጀመረ በኋላ ክፍል ውስጥ የሚገባ ተማሪ አርፍዷል ተብሎ ይመዘገባል። አንድ ተማሪ ያለምክንያት ሲቀር ወይም ያለምክንያት ሲያረፍድ ወይም ከሁለት (2) በላይ የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች ላይ ሳይገኝ ሲቀር ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ይነገራቸዋል። አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት ቀርቶ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በሶስት (3) ቀን ጊዜ ውስጥ ምንም ዓይነት ማስታወሻ ትምህርት ቤቱ ካልደረሰው፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ማሳወቅ አለበት። አንድ ልጅ ባለፉት ስድስት (6) ወራት ውስጥ በቂ ማስረጃ ሳይሰጥ አምስት (5) ቀናት ካረፈደ፣ አምስት (5) ቀናት ወይም አሥር (10) ግማሽ ቀናት ከቀረ፣ ወይም በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ ከአምስት (5) ቀናት በላይ ያለ በቂ ምክንያት ከቀረ ወይም ከሁለት (2) በላይ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ላይ ሳይገኝ ከቀረ ልጁ የተመዘገበበት ትምህርት ቤት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ለትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ ከአምስት (5) ቀን በላይ ያለበቂ ምክንያት ከቀረው ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ተገናኝቶ መፍትሄ ለማግኘት ተገቢ ጥረት ማድረግ አለበት። የመፍትሄው እርምጃዎች በጋራ የሚጎለብቱ ሲሆን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ፣ ተማሪውና የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ሁሉ የተስማሙበትና ሌሎች የሚመለከታቸው የትምህርት ቤት ሠራተኞችና የደህንነት ሹሞች፣ የጤናና የሕዝብ አገልግሎት፣ የመኖሪያ ቤት ድርጅቶችም እንዳስፈላጊነቱ ሐሳብ የሰጡበት መሆን አለበት።

ማንኛውም በቂ ምክንያት አሳይቶ ከትምህርት ቤት ወይም ከክፍል የቀረ ተማሪ የቀረበትን የቤት ሥራ፣ ፈተና፣ ፕሮጀክት፣ ፈተና ወይም ሌላ ሥራ የማካካስ መብት አለው። ከአምስት (5) ተከታታይ ቀናት በላይ ከትምህርት ቤት ለታገዱ ወይም ለተባረሩ ተማሪዎች የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ለትምህርት ቤቱ ባጠቃላይ የትምህርት አገልግሎት ዕቅድ መኖሩን ያረጋግጣል። በተጨማሪም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ማንኛውም ከአምስት (5) ተከታታይ ቀን በላይ በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ውጭ ከትምህርት ቤት የታገደ ወይም የተባረረ ተማሪ በተባረረበት ወቅት ትምህርቱን የማሻሻል ዕድል ማግኘቱን ማረጋገጥ አለበት፣ ይህም ማናቸውም ያመለጠው የቤት ሥራ፣ ፈተና፣ ፕሮጀክት ወይም ሌላ ሥራ ነጥብን ይጨምራል።

በቂ ምክንያት ኖሮት ከአምስት (5) ቀን በላይ የቀረ ተማሪ የቀረበትን የቤት ሥራ ከቤት ማግኘት እንዲችል ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ትምህርት ቤቱን ማሳወቅ አለባቸው። ለበጣም ረጅም ጊዜ (2 ሳምንት ወይም ከዛ በላይ) በሕመም ወይም በጉዳት ምክንያት የሚቀር የማንኛውም ተማሪ የቤት ትምህርት ማግኘት እንዲችል የሚያስፈልገውን መሰናዶ ለማድረግ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ትምህርት ቤቱን ማሳወቅ አለባቸው።

አጥጋቢ ምክንያት የሌላቸው የመቅረት ወይም የማርፈድ ሁኔታዎች የቅጣት እርምጃ ሊያስከትሉ ይችላሉ። ያለ በቂ ምክንያት መቅረት፣ ማርፈድ ወይም ከክፍል መቅረት የሚያበዛ ተማሪን ከትምህርት ቤት ከማገዳቸው በፊት የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣኖች ሁሉንም ተገቢ የቅጣት እርምጃ፣ ማለትም ወደ ወጣቶች ፍርድ ቤት መላክን፣ ልዩ ትምህርት ያስፈልገው እንደሆነ ለማወቅ የልዩ ትምህርት ግምገማ እንዲደረግለት ሁኔታዎችን ማመቻቸትን ጨምሮ የመሳሰሉትን እርምጃዎች እንዲወስዱ ይደረጋል። ተማሪው አስተማሪው በሰጠው መመሪያ መሠረት ያመለጠውን

የቤት ወይም የክፍል ሥራ ካላካካሰ በስተቀር ያለ በቂ ምክንያት ከትምህርት ቤት ቀርቶ ወይም አርፍዶ ላመለጠው የክፍል ሥራ ነጥብ አይሠጠውም፣ አስተማሪዎችም ተማሪው ወደ ክፍል ሲመለስ ተማሪው ያመለጠውን ፈተና፣ የቤት ሥራ፣ ፈተና፣ ፕሮጀክት ወይም የክፍል ሥራ እንዲያካክስ አግባብ ያለው በቂ ጊዜ መስጠት አለባቸው። ኃይማኖታዊ በዓል ለማክበር የቀረ ተማሪ ላይ ምንም ዓይነት የአድሎ ተጽዕኖ አይደርስበትም። በኃይማኖታዊ በዓሎች ወቅት አስተማሪዎች አስፈላጊ ፈተናዎችን፣ የመጨረሻ ፕሮጀክቶችን ወይም ዋና ጽሑፍ/ሪፖርቶችን ከመስጠት በተቻለ መጠን መቆጠብ አለባቸው።

Cambridge Rindge and Latin School (ኬምብሪጅ ሪንጅ እና ላቲን ትምህርት ቤት) እና High School Extension Program (የሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ተጨማሪ መርሃ ግብር) በማንኛውም ክፍል ውስጥ ማናቸውንም አራት (4) ጊዜ ከትምህርት ቤት የመቅረት ሁኔታ ሲከሰት እንደ Attendance Violation (AV) (ሰዓት መተላለፍ) ይቆጥሩታል። በበቂ ምክንያት አለመገኘት፣ በሕመም ምክንያት አለመገኘትን ጨምሮ ከሚከተሉት ምክንያቶች የሚመደብ ከሆነ ተማሪ ላይ እንደ ወቀሳ አይያዝበትም፣ እንዲሁም Attendance Violation (AV) አያስሰጥም፦ (ሀ) እጅግ አሰቃቂ ገጠመኝ ኖሮ ሲቀር፣ ሐዘን፣ ቤተሰብ ውስጥ ሞት ተከስቶ ሲቀር፣ (ለ) ኃይማኖታዊ በዓል ለማክበር ሲቀር፣ (ሐ) ከትምህርት ሰዓት ውጪ በጭራሽ ሊደረግ የማይችል የሐኪም ቀጠሮ ወይም የአማካሪ ቀጠሮ ሲኖር፣ (መ) በግል መገኘት የሚያስፈልገው ሕግ ነክ ቀጠሮ፣ (ሠ) ከትምህርት ቤት ውጭም ሆነ ውስጥ ከትምህርት መታገድ፣ (ረ) የትምህርት ጉዞዎች እና ስብሰባዎች፣ (ሰ) የኮሌጅ ጉብኝቶች (አሥራ አንደኛ ክፍል ላይ ሁለት ቀን፣ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ላይ ሶስት ቀን)፣ እና (ሸ) አንድ ተማሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባለበት ዓመታት ውስጥ አንድ ርዝመቱ ከአምስት ቀን በላይ ያልሆነ ጉዞ ወይም የትምህርት ተሞክሮ።

ሆኖም በማንኛውም ክፍል ውስጥ አራት (4) ጊዜ ያለበቂ ምክንያት መቅረት Attendance Violation ያስሰጣል። በዚህ ጊዜ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ ለተርሙ የ AV ነጥብ ይሰጣል። በተጨማሪም ሶስት (3) ጊዜ በቂ ምክንያት ሳይኖር ማርፈድ እንደ አንድ (1) በቂ ምክንያት የሌለው መቅረት ይቆጠራል። በቂ ምክንያት የሌለው መቅረት የሚከተሉትን ያካትታል፦ (ሀ) ከትምህርት ቤት ወይም ከክፍል ጊዜ ያለ በቂ ምክንያት መቅረት፣ (ለ) የትምህርት ቤት ኃላፊው አስቀድሞ ፈቃድ ያልሰጠበት ጉዞ፣ (ሐ) ያለ ትምህርት ቤት ኃላፊው ፈቃድ ሥራ ፍለጋ፣ (መ) ፈተና ላለመፈተን ወይም ለፈተና ለመዘጋጀት ቤት መቅረት፣ (ሠ) የተማሪዎች ኃላፊ ቢሮ ውስጥ ሳይፈርሙ ትምህርት ቤቱን ጥሎ መውጣት (ከክፍል መቅረት)፣ እና (ረ) ተኝቶ ማርፈድ ወይም እንዲሁ አርፍዶ መድረስ፣ (ሰ) ትምህርት ቤት አካባቢ መቆየት ሆኖም ክፍል ውስጥ አለመግባት (ከክፍል መቅረት)፣ እንዲሁም (ሸ) ማንኛውም ሌላ ያለ በቂ ምክንያት መቅረት ወይም ያለፈቃድ የመቅረት ሁኔታ ወይም በቂ ምክንያት ኖሮ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ግን ስልክ በመደወል ያላሳወቁት ወይም ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወይም ከዶክተሩ የጽሑፍ ማስረጃ ሳይዝ ከተመለሰ። በተጨማሪም አንድ ተማሪ አሥራ ሁለት (12) ጊዜ ያለ በቂ ምክንያት አንድ ክፍል ውስጥ አርፍዶ ከደረሰ ለዛ ትምህርት AV ይሰጠዋል።

በትምህርት ቤት አውራጃው ፖሊሲ መሠረት፣ አንድ ተማሪ በቀረ እና/ወይም ባረፈደ ቁጥር ትምህርት ቤቱ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን/ተንከባካቢዎችን ያሳውቃል እንዲሁም አራት ጊዜ ያለ ምክንያት ከቀረ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን/ተንከባካቢዎችን ያሳውቃል። በተደጋጋሚ መቅረት ለሚያስገድድ ሐመም ወይም ማናቸውም ከአራት (4) ቀን በላይ ለሚያስቀሩ ሕመሞች ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የሕክምና ፈቃድ መጠየቅ ይችላሉ። AV በሚሰጥበት ጊዜ፣ AVው በተሰጠ በአሥር (10) ቀን ውስጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች Cambridge Rindge and Latin School ወይም High School Extension Program ውስጥ የሚገኘው የይግባኝ ኮሚቴ ፊት አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ፣ ይግባኙ ተቀባይነት ካላገኘ ተቀባይነት ካላገኘበት ቀን ጀምሮ እስከ አሥር (10) ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ለትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ በጽሑፍ ይግባኝ ማለት ይችላሉ። የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ውሳኔ የመጨረሻው ይሆናል።

የትምህርት ማህበረሰብ ቡድኖች የ AV መስፈርት ከሚያሟሉ ተማሪዎች ጋር አብሮ በመሥራት ከሚከተሉት ሶስት (3) ድጋፎች ውስጥ አንዱን በሥራ ላይ ያውላሉ፦

ሀ. መልሶ የመግዛት ውል መሙላት (ለሁሉም ተማሪ የሚቀርብ)
ለ. ተማሪውን የተማሪዎች ወርክሾፖች ውስጥ ማስመዝገብ (ተጨማሪ የጊዜ ማስተዳደርና የተማሪ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው
ሐ. ከ LC ቡድን ጋር በመተባበር የተዘጋጀ የግል ድጋፍ ዕቅድ (ከአቅም በላይ ችግር ላጋጠማቸውና ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች)

አንድ ተማሪ የድጋፍ ዕቅዱን ስኬታማ በሆነ ሁኔታ ካላጠናቀቀ 1 ነጥብ ሊቀነስበት ይችላል።

**ትምህርት ቤቱን ለቅቀው የሚሄዱ ተማሪዎችን በሚመለከት ማስታወቂያ**

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች አስተዳደር ተማሪዎች አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ተግቶ ይሠራል። አሥራ ስድስት ዓመት ወይም ከዛ በላይ ዕድሜ ያለው ተማሪ ትምህርት ቤቱን ለቅቆ መሄድ ከፈለገ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች አስተዳደር የ M.G.L.c. 76፣ §18 መስፈርቶችን በመከተል የሚከተሉትን ሂደቶች ሥራ ላይ ያውላል፡-

1. ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ለተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ተማሪው (ሀ) ተማሪው ደግሞ ላይመለስ ከትምህርት ቤት መውጣት እንደሚሻ ማሳወቁን፣ ወይም (ለ) ተማሪው ከትምህርት ቤት ለአሥራ አምስት (15) ተከታታይ ቀናት የቀረ መሆኑንና በመጨረሻ ተማሪው ትምህርት ቤት የተገኘበትን ቀን የሚገልጽ ደብዳቤ ይልካል።

   ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ላይመለስ እስከመጨረሻ መውጣት መሻቱን ለመገምገም እንዲችልና ተማሪው ከትምህርት ቤት መውጣት የፈለገበትን ምክንያቶች ለመወያየት እንዲሁም ተማሪው ከመውጣቱ በፊት ሌላ የትምህርት አማራጮች ካሉ እነሱን ለማጤን ትምህርት ቤቱ ከተማሪውና ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ተሰብስቦ መወያያ ቀን ቀጠሮ ይይዛል። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የዚህ ስብሰባ ቀንና ሰዓት እንዲቀየርላቸው መጠየቅ ይቻላሉ፣ ማራዘም የሚችሉት ግን ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ደብዳቤውን በሰጠ እስከ አሥራ አራት (14) ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ነው።

2. ስብሰባው ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ከተማሪው ጋር ከተካሄደ በኋላ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ለተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የተወያዩባቸውን ነጥቦችና ማንኛውንም የደረሱበትን ውሳኔ ማለትም ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት እንደሚመለስ ወይም ሌላ ዓይነት የትምህርት ሁኔታ ውስጥ እንደሚገባ ወይም ሌሎች የትምህርት ድጋፍ አገልግሎቶች ውስጥ እንደሚሳተፍ ወይም እስከመጨረሻው ትምህርት ቤት ለቅቆ እንደሚሄድ የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣቸዋል።
3. M.G.L.c. 76፣ §18 ውስጥ ባሉት አቅራቢዎች መሠረት፣ ተማሪው እስከመጨረሻው ትምህርት ቤቱን ለቅቆ እንደሚሄድ ከታወቀና ተማሪው ሌላ ትምህርት መቀጠል ከፈለገ እንደ መባረር አይታይም።

ስለዚህ ሂደት ተጨማሪ ዝርዝር ለማወቅ የዚህ *መመሪያን* ክፍል 22 ይመልከቱ።

### 3.0 የግለሰብ ፍተሻ

በአሜሪካ ሕገ መንግሥት ማሻሻያ ቁጥር አራት መሠረት ተማሪዎች በመንግሥት ትምህርት ቤት ባለሥልጣኖችና አስተማሪዎች ከሚደረጉ አግባብ የሌላቸው ፍተሻዎችና መያዝ የተጠበቁ ናቸው።

ተማሪዎች የግል ሙብቴ የተጠበቀ ነው ብለው ቢጠብቁም የትምህርት ቤት ደንብ ወይም ሕጎች የጣሰ ነገር ይገኝባቸዋል ተብለው ባግባቡ ከተጠረጠሩና የፍተሻው ስፋት አግባብ ያለው ከሆነ ሊፈተሹ ይችላሉ።

3.1 **ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፦** የተማሪ ፍተሻ ከመደረጉ በፊትና የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ የሆነ ሠራተኛ ጥያቄያዊ ምርመራ ለተማሪው ከማቅረቡ በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ፈቃድ መስጠት አለበት።

**ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፦** ዋና ተቆጣጣሪው፣ ረዳት ተቆጣጣሪው፣ የተማሪዎች ኃላፊ ወይም የዋና ተቆጣጣሪው ተወካይ የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ለሚያደርጋቸው ፍተሻዎች አስቀድሞ ፈቃድ መስጠት አለበት።

3.2 **ሁሉም ክፍሎች (ከአጸደ ሕጻናት እስከ 12ኛ ክፍል)፦** ሁኔታው የሚፈቅድ ከሆነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ፣ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ወደ ትምህርት ቤቱ እና/ወይም ወደ አነስተኛ መማሪያ ማህበረሰብ ጋር የሚላከው የደህንነት ጥበቃ የትኛው እንደሆነ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

3.3 **ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፦** ተማሪዎች ፍተሻ በሚደረግባቸው ወቅት ወይም የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ የሆነ ሠራተኛ ጥያቄያዊ ምርመራ ለተማሪዎች በሚያደርግበት ወቅት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ መገኘት አለበት።

**ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፦** ተማሪዎች ፍተሻ በሚደረግባቸው ወቅት ወይም የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ የሆነ ሠራተኛ ጥያቄያዊ ምርመራ ለተማሪዎች በሚያደርግበት ወቅት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ፣ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ መገኘት አለበት።

3.4 **ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፦** ተማሪዎች በትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ጥያቄያዊ ምርመራ በሚደረግላቸው ወቅት በተቻለ መጠን ጾታው ከተማሪው ጋር አንድ ዓይነት የሆነ ግለሰብ አብሮ መገኘት አለበት። የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ተማሪዎች ላይ የሚያደርጋቸው ፍተሻዎች ሁሉ የሚመሩት ከተማሪው ጋር አንድ ዓይነት ጾታ ያለው ግለሰብ መሆን አለበት።

**ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፦** የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ተማሪዎች ላይ የሚያደርጋቸው ፍተሻዎች ሁሉ የሚመሩት ከተማሪው ጋር አንድ ዓይነት ጾታ ያለው ግለሰብ መሆን አለበት።

3.5 **ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፦** የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ፍተሻ ከማድረጉ በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት። አስቀድሞ ማሳወቅ ካልተቻለ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከፍተሻው በኋላ በተቻለ መጠን በፍጥነት እንዲያውቁ ይደረጋል፣ የዛንኑ ቀን ደብዳቤም ይላክላቸዋል።

**ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፦** የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ፍተሻ እንዳደረገ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ወዲያው ማሳወቅ አለበት። በተጨማሪ፣ የዛንኑ ቀን ደብዳቤ ይላክላቸዋል።

"የድንገተኛ ተጠሪ" ማለት ቅጣት ነክ ጉዳይ ሲያጋጥም፣ ጥያቄያዊ ምርመራን ወይም ፍተሻዎችን ጨምሮ ኃላፊነት ወስዶ ምላሽ እንዲሰጥ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የሰየሙት ግለሰብ ነው። በየትምህርት

ዓመቱ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ቅጣት ነክ ጉዳይ ሲያጋጥም፣ ጥያቄያዊ ምርመራን ወይም ፍተሻዎችን ጨምሮ በድንገተኛ ጊዜ ተጠሪ የሚሆን ግለሰብ እንዲሰይሙ ይጠየቃሉ፣ ይህም ግለሰብ ቅጣት ነክ ጉዳይ፣ ጥያቄያዊ ምርመራ ወይም ፍተሻዎችን በተመለከተ በወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ምትክ እነሱ እስከፈቀዱት መጠን ድረስ እርምጃ ይወስዳል።

3.6 **ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል፦** የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ለተማሪው ጥያቄያዊ ምርመራ ከማድረጉ በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ወይም የድንገተኛ ተጠሪውን አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት። አስቀድሞ ማሳወቅ ካልተቻለ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከምርመራው በኋላ በተቻለ መጠን በፍጥነት እንዲያውቁ ይደረጋል፣ የዛንኑ ቀንም ደብዳቤም ይላክላቸዋል።

**ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል፦** የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ለአንድ ተማሪ ጥያቄያዊ ምርመራ ሲያደርግ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን የማሳወቅ ግዴታ የለበትም።

3.7 **ከአጸደ ሕጻናት እስከ 12ኛ ክፍል፦** *ተማሪዎች በሙሉ ከጥያቄያዊ ምርመራና ከፍተሻ ጋር በተያያዘ ያሏቸውን የሚከተሉትን መብቶችና ኃላፊነቶች በዚህ በመብትና ኃላፊነት መመሪያ* (ካሁን በኋላ "*መመሪያ*" ተብሎ የሚጠቀስ) አማካኝነት እና/ወይም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ አማካኝነት ወይም በ CRLS *የተማሪ መመሪያ አማካኝነት ይነገራቸዋል፦*

*ሀ.* *ትምህርትን፣ ቅጣትን ወይም ሌላ ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ጉዳይ ማንኛውም ተማሪ በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ በትምህርት ሥርዓትና መርሃ ግብር ኃላፊ፣ በተማሪዎች ኃላፊ ወይም በረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ አመራር ሥር ጥያቄያዊ ምርመራ ሊደረግለት ይችላል።*

*ለ.* *ተማሪዎች ለፍተሻ ፈቃደኛ ከሆኑ ወይም አንድ የትምህርት ቤት ደንብ ወይም ማንኛውንም ሕግ ጥሰዋል ተብለው በአግባቡ ከተጠረጠሩ በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ በትምህርት ሥርዓትና መርሃ ግብር ኃላፊ፣ በተማሪዎች ኃላፊ ወይም በረዳት ተቆጣጣሪ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ አመራር ሥር ፍተሻ ሊደረግላቸው ይችላል።*

*ሐ.* *የደህንነትና ጥበቃ መመሪያ አባሎች የማንኛውም ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ያለ ተማሪ ጥያቄያዊ ምርመራ ውስጥ ወይም ፍተሻ ውስጥ ተሳታፊ ሲሆኑ፣ ድንገተኛ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ ከተማሪው ትምህርት ቤት አንድ ከተማሪው ጋር አንድ ዓይነት ጾታ ያለው ግለሰብና አንድ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ተወካይ የሆነ ግለሰብ በፍተሻና ጥያቄያዊ ምርመራው ላይ አብሮ መገኘት አለባቸው። በ* Cambridge Rindge and Latin School *ላሉ ተማሪዎች፣ ድንገተኛ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ ከተማሪው ትምህርት ቤት አንድ ከተማሪው ጋር አንድ ዓይነት ጾታ ያለው አዋቂና አንድ የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ተወካይ የሆነ ግለሰብ የደህንነትና ጥበቃ መመሪያ በሚያደርገው ፍተሻና ጥያቄያዊ ምርመራ ላይ አብሮ መገኘት አለባቸው።*

3.8 *የመመሪያው* ክፍል 3.0 ላይ እና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥና የ CRLS *የተማሪ መመሪያዎች የተጠቀሱት ቃላት "ጥያቄያዊ ምርመራ" እና "ፍተሻ" ትርጉማቸው እንደሚከተለው ነው፦*

*"ጥያቄያዊ ምርመራ" ማለት ለአንድ ተማሪ ኦፊሲዬላዊ በሆነ መንገድ ትምህርት ነክ፣ ቅጣት ነክ ወይም ማንኛውም ሌላ ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ጉዳይን በተመለከተ ጥያቄ ማቅረብ ነው።*

*"ፍተሻ" ማለት የአንድ ተማሪ ንብረትን ወይም አካልን መፈተሽ፣ የተማሪውን ቦርሳና ኪሶችንም ጨምሮ። ፍተሻ ማለት የተማሪውን አካል በልብሱ ላይ በመጠኑ መፈተሽንም ሊያካትት ይችላል።*

3.9 የትምህርት ቤት ደህንነት ጥበቃ ማንኛቸውንም የተማሪ ፍተሻዎች ካካሄደ በኋላ ዋና ተቆጣጣሪውና ዋና ሥራ አስኪያጁ በተቻለ መጠን በፍጥነት ማወቅ አለባቸው። በተጨማሪም የትምህርት ቤት ኮሚቴው አሁን ከሚደርሱት ሪፖርቶች በተጨማሪ የደህንነት ጥበቃ ያደረጋቸውን ፍተሻዎች በተመለከተ በየወሩ አጫጭር ሪፖርቶች ይደርሰዋል።

3.10 “የግል ምርመራ” ማለት የተማሪዎችን እና/ወይም የሠራተኞችን ደህንነት የሚመለከት በአንድ ክስተት ብቻ ያልተወሰነ ቀጣይነት ያለው የአስጊ ዛቻ ምርመራ ነው። ምርመራው የሚመለከተው አንድ ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ትምህርት ቤቶችን ወይም በአውራጃው ውስጥ ያሉ የCRLS ትምህርት ቤቶችን መሆን አለበት። በትምህርት ቤቱ አውራጃ ውስጥ ከአንድ ትምህርት ቤት በላይ የሚመለከቱ ሁሉም “የግል ምርመራዎች” ከዋና ተቆጣጣሪው ወይም ከዋና ሥራ አስኪያጁ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። የግል ምርመራው የሚመለከተው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ከአንድ ትንሽ ትምህርት ቤት በላይ ከሆነ የግል ምርመራው ፈቃድ የሚያስፈልገው ከትምህርት ቤቱ ተቆጣጣሪ ብቻ ነው።

## 4.0 የተማሪዎች ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች፣ ጠረጴዛዎች እና ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች

4.1 የተማሪዎች ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖችና ጠረጴዛዎች
ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖችና ጠረጴዛዎች የትምህርት ቤቱ ንብረት እንደመሆናቸው መጠን፣ የትምህርት ቤቱ መምሪያ ሳጥኖችንና ጠረጴዛዎችን የመፈተሽ መብትና አልፎ አልፎም አስቀድሞ ተናግሮ ወይም አስቀድሞ ሳይናገር ጠረጴዛዎችንና ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖችን የመመርመር መብት አለው።

4.2 የአንድ ተማሪ ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን እና/ወይም ጠረጴዛ ሕገወጥ ዕቃ ወይም ከትምህርት ቤት ሕግ ወይም ደንብ ጥሰት ጋር የተያያዘ ማስረጃ አለው ተብሎ ከተጠረጠረ፣ ወዲያውኑ የትምህርት ቤቱን ሕንጻ ወይም ውስጡ ያሉትን ሰዎች አደጋ ላይ የሚጥል ነገር ከሌለ ሊፈተሽ ይችላል። ፍተሻውን ማካሄድ የሚችሉት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ናቸው። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተወካይ ፍተሻ አርገው እንደጨረሱ በተቻለመጠን ወዲያውኑ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ማሳወቅና የዛኑ ዕለት ደብዳቤ መላክ አለባቸው። በተጨማሪ፣ የዛኑ ቀን ደብዳቤ ይላክላቸዋል።

4.3 ሕገወጥ ናቸው ተብለው የተጠረጠሩት ነገሮች በሙሉ ሲነሱ ሌሎችን አደጋ ላይ ይጥላሉ ተብሎ ካልታመነ በስተቀር ከተማሪው ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ወይም ጠረጴዛ ይወሰዳሉ። ይህ ከተደረገ ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኑ ይዘጋና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወዲያውኑ ይነገረዋል፣ ጠረጴዛውም ጥበቃ ተደርጎለት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወዲያው ይነገረዋል። ሕገወጥ ዕቃው ከቦታው የሚነሳው የሕንጻ ደህንነት ጥበቃ ዕቅድ ውስጥ በተዘረዘሩት ሂደቶች መሠረት ይሆናል። ማናቸውም የዕቃ ማስቀመጫ ሳጥኖች እና/ወይም ጠረጴዛዎች ውስጥ የቀሩ ሌሎች ዕቃዎች የትምህርት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ተወስደው ይጣላሉ። የተማሪ ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ የተቀመጠ ዕቃ ላይ ጉዳት ቢደርስ፣ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ምንም ኃላፊነት የለበትም፣ ከዓመቱ መጨረሻ የትምህርት ቀን በኋላም የተማሪ ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ እና/ወይም ጠረጴዛ ውስጥ የተተወ ዕቃ ላይ ጉዳት ቢደርስ፣ ቢሰረቅ ወይም ቢጠፋ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ምንም ኃላፊነት የለበትም።

4.4 ሁሉን ከፋች ቁልፎችና የተማሪ ሳጥን ቁልፎች ግልባጭ የሚቀመጡት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ቢሮ ውስጥ ይሆናል። የትምህርት ቤቱ መምሪያ የሚያድላቸው መቆለፍያዎችን ብቻ ነው መጠቀም የሚቻለው። ሌሎች መቆለፊያዎች ሁሉ በተማሪው ወጪ ይወሰዳሉ።

4.5 ተማሪዎች ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥናቸው ውስጥ መሣሪያ፣ አደንዛዥ ዕጽ ወይም የዕጽ መሳሪያ፣ አልኮል ያለው መጠጥ፣ የተሰረቀ ዕቃ እና ማናቸውም ሌላ ሕገወጥ የሆኑ በትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪዎች ጠቃሚ ያልሆኑ ዕቃዎች ማስቀመጥ አይችሉም።

4.6 ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች
ተማሪዎች ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ባሉ ጊዜ ወይም ትምህርት ቤቱ ባዘጋጀው ወይም ትምህርት ቤቱ ድጋፍ ባደረገበት ዝግጅት ላይ ሲገኙ ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን የመያዝ መብት ይፈልጋሉ። ከዚህ መብት ጋር ተያይዞ የሚመጣ አግባብ ያለው የአጠቃቀም ኃላፊነት አለ። ተማሪዎች ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ሆነው ወይም ትምህርት ቤቱ ባዘጋጀው ወይም ትምህርት ቤቱ ድጋፍ ባደረገበት ዝግጅት ላይ ተገኝተው ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ አምጥተው ሲጠቀሙ አግባብ ባለውና ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ መሆኑን ኃላፊነት ወስደው እንደሆነ መረዳት አለባቸው። በተጨማሪም ተማሪዎች ኤሌክትሮኒክ መሳሪያቸውን ለሰው ማዋስ አይችሉም። አንድ ተማሪ ይህን ካደረገ ሌላ ሰው ተጠቅሞት ለሚመጣ ማንኛውም መዘዝ ልክ በተማሪው እጅ ሆኖ እንደተከሰተ ተቆጥሮ ተማሪው ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

4.7 ተማሪዎች ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ ሲጠቀሙ የትምህርት ሂደትን በሚያውክ ሁኔታ ወይም በሚረብሽ ሁኔታ ሊሆን አይችልም። ለምሳሌ በትምህርት ላይ ወይም ትምህርት ቤቱ ድጋፍ ባደረገበት ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ ኤሌክትሮኒክ መሳሪያው ክፍት ከሆነ፣ ድምጽ የሚያሰማ ከሆነ፣ ንዝረት ካለው ወይም በሌላ ባማንኛውም መንገድ ሐሳብ የሚስብ ከሆነ መሳሪያው እየረበሸ ነው ማለት ነው። ኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎን ያላግባቡ መጠቀም መሳሪያውን እስከማስከልከል ሊያደርስና ቅጣትም ሊያስከትል ይችላል።

4.8 አንድ ተማሪ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ ትምህርት ቤቱ ድጋፍ ባደረገበት ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ አምጥቶ ቢጠፋበት፣ ቢሰረቅበት ወይም ቢጎዳበት የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ኃላፊነት የለባቸውም።

## 5.0 የግለሰብ ነጻነት

5.1 ተማሪዎች በትምህርት ቤት ሕንጻዎች ውስጥ፣ የትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዲሁም ከቤት ወደ ትምህርት ቤት በሚመላለሱበት ጊዜና በማንኛውም ትምህርት ቤቱ በፈቀደው ዝግጅት ላይ ሲገኙ የግለሰብ ደህንነታቸው መጠበቅ መብት አላቸው።

5.2 ማንኛውም ተማሪ፣ አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሹም አውቆ የአካል ጉልበት ተጠቅሞ ሌላ ተማሪ፣ አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሹም ላይ ጉዳት ማስከተል አይችልም። ሆኖም በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ከተገኘ አንድ አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሹም የአካል ጉልበት ሊጠቀም ይችላል፦

ሀ. መሳሪያ ወይም ሌላ አደገኛ ዕቃ ለመንጠቅ፣ ወይም

ለ. እራስን ከአደጋ ለመከላከል፣ ወይም

ሐ. ሌላን ሰው ወይም ንብረት ከአደጋ ለመከላከል።

5.3 ማንኛውም አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሹም አንድ ተማሪን ለመቅጣት የአካል ጉልበት መጠቀም አይችልም። አካላዊ ቅጣት በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ነው።

5.4 ማንኛውም ተማሪ፣ አስተማሪ፣ የትምህርት ቤት ሹም ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ አንድ ተማሪን፣ አስተማሪን ወይም የትምህርት ቤት ሹምን በማንኛውም መንገድ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ እንዲሁም ተማሪን ባደባባይ ማዋረድ አይችልም።

## 5.5 <u>የምግባር ደንብ፣ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላ</u>

የጾታ ጉትጎታ እና/ወይም ሌላ ማንኛውም ዓይነት ጥበቃ ባላቸው ጉዳዮች ዙሪያ (ዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ) ማግለል ወይም ጥቃት ደርሶብኛል ብለው የሚያምኑ ተማሪዎች በሙሉ Program Manager for Diversity Development (የሕብረ ባህላት ጉልበታ መርሃ ግብር አስተዳዳሪ) ጋር ወይም Executive Director of Human Resources (የቅጥር ክፍል ዋና ሥራ አስኪያጅ) ጋር ይግባኝ ማለት ይችላሉ። የይግባኙን ሂደት ለመጀመር ተማሪዎች በመጀመሪያ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው፣ ረዳት ተቆጣጣሪው፣ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊው፣ የሕብረ ባህላት ጉልበታ መርሃ ግብር አስተዳዳሪው ወይም Deputy Superintendent of Teaching and Learning (የማስተማርና የመማር ምክትል ተቆጣጣሪ) ጋር ተገናኝተው በጸረ-ማግለል ፖሊሲና በጾታ ጉትጎታ ክልከላ አቅርቦቶች ሂደት መሠረት አቤቱታ ማስገባት ይችላሉ። ምንም ዓይነት ጥቃት ወይም ማግለል ያስተዋሉ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ክስተቱን ወዲያውኑ ለተማሪው ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪ ወይም ለተማሪ ጉዳዮች ኃላፊ ማሳወቅ አለባቸው።

በተጨማሪም ተማሪዎች Massachusetts Commission Against Discrimination (የማሳቹሴትስ ጸረ-ማግለል ኮሚሽን) ጋር በሚከተሉት ቦታዎች አቤቱታ ማስገባት ይችላሉ፡-

Boston Office (የቦስተን ቢሮ)፡-

One Ashburton Place
Suite 601
Boston, MA 02108
ስልክ ቁ፡- 617-994-6000
መስማት ለሚሳናቸው፡- 617-994-6196
ፋክስ፡- 617-994-6024
ኢሜል፡- assistanttochairman@state.ma.us

Springfield Office (የስፐሪንግፊልድ ቢሮ)፡-

436 Dwight Street
Suite 220
Springfield, MA 01103
ስልክ፡- 413-739-2145
ፋክስ፡- 413-784-1056
ኢሜል፡- assistanttochairman@state.ma.us

Worcester Office (ዎርሴስተር ቢሮ)፡-

484 Main Street
Room 320
Worcester, MA 01608
ስልክ፡- 508-453-9630
ፋክስ፡- 508-755-3861
ኢሜል፡-assistanttochairman@state.ma.us

New Bedford Office (ኒው ቤድፈርድ ቢሮ)፡-

800 Purchase Street
Room 501
New Bedford, MA 02740
ስልክ፡- 508-990-2390
ፋክስ፡- 508-990-4260
ኢሜል፡- assistanttochairman@state.ma.us

ወይም Program Quality Assurance Services (የመርሃ ግብር ማረጋገጫ አገልግሎቶች)፣ Massachusetts Department of Elementary and Secondary Education (ማሳቹሴትስ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ) ጋር፡-

75 Pleasant Street, Malden, MA 02148-4906
Phone: 781-338-3700
ስልክ፡- 781-338-3710

መስማት ለሚሳናቸው፡- N.E.T. Relay: 1-800-439-2370
ኢሜል፡- compliance@doe.mass.edu

ወይም United States Department of Education, Office for Civil Rights (የአሜሪካ ትምህርት መምሪያ፣ የሕዝብ መብት ቢሮ) ጋር፡-

5 Post Office Square, 8th Floor
Boston, MA 02109
ስልክ፡- 617-289-0111
ፋክስ፡- 617-289-0150
መስማት ለሚሳናቸው፡- 1-800-877-8339
ኢሜል፡- OCR.Boston@ed.gov

አንዳንድ ጊዜ አቤቱታ የቀረበበት ምግባር በ Title IX ሥር እንደ ጾታዊ ጉትጎታና ወንጀል ሊቆጠር ይችላል። የተከሰተው ጉዳይ ወንጀልም ነው ብለው የሚያምኑ ከሆነ በማንኛውም ጊዜ ወንጀላዊ አቤቱታ ማስገባት ይችላሉ፣ ማለትም አቤቱታዎን ትምህርት ቤቱ በሚመረምርበት ወቅትም ቢሆን።

5.6 <u>የማግለልና የጥቃት ፍቺ</u>

"ማግለል" እና "ጥቃት" ማለት በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ተቀባይነት የሌላቸው የቃልም ሆነ የአካል ምግባሮች ናቸው። ማግለል እና/ወይም ጥቃት በሚከተሉት ብቻ የማይወሰኑ ሆነው የሚከተሉትንም ይጨምራሉ፡-

ሀ. ከላይ የተጠቀሱት ርእሶች የሚመለከተው ሰውን ወይም ቡድኖችን የሚያዋርድ የጽሑፍ መጽሔት ወይም ፎቶግራፎች ማሳየት ወይም ማሰራጨት።

ለ. ከላይ ከተጠቀሱት መሃል የሆነን ሰው ወይም ቡድንን በአፍ መዘለፍ ወይም መሳደብ።

ሐ. አንድ ግለሰብን ወይም ቡድንን (ከላይ እንደተገለጸው) (1) በኬምብሪጅ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሥራ ከመሥራት ወይም አንድ መርሃ ግብር ውስጥ ከመሳተፍ የሚያግድ ዓይነት ኃይለኛና በቀጣይነት የሚከሰት ማንኛውም ድርጊት ወይም ንግግር፣ (2) ወይም አስፈሪ፣ ከልክ ያለፈ ጎጂ የትምህርት ወይም የሥራ ሁኔታ የሚፈጥር ድርጊት።

ብዙ ዓይነት ጥቃትና የማግለል ሁኔታዎች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ውስጥ፣ በስቴት ፍርድ ቤቶች ውስጥ፣ በ U.S. Equal Employment Opportunity Commission (የአሜሪካ የእኩልነት ቅጥር ዕድል ኮሚሽን)፣ በU.S. Department of Education (የአሜሪካ ትምህርት መምሪያ)፣ በOffice for Civil Rights (የሕዝብመብት ቢሮ) እና በMassachusetts Commission Against Discrimination (የማሳቹሴትስ ጸረ ማግለል ኮሚሽን) የሕዝብ መብት ሕግ ጥሰቶች (ሆነው የ Rehabilitation Act of 1973 (የ1973 ዓ.ም. እድሳት ሕግ)፣ Title VI (ታይትል ስድስት) እና Title IX (ታይትል ዘጠኝ) ክፍል 504ን ጨምሮ) ተገኝተዋል።

5.7 <u>የጾታ ጉትጎታ ፍቺ</u>

"የጾታ ጉትጎታ" ማለት ሳይፈልጉት የሚመጣ ግብረስጋዊ ግብዣ፣ ግብረስጋዊ ጥቅም መጠየቅ እንዲሁም ግብረስጋዊ ተፈጥሮ ያለው አንደበታዊ ወይም አካላዊ ምግባር በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ፡-

ሀ.   እንደነዚህ ዓይነት ግብዣዎችን መቀበል ወይም አለመቀበል ሥራ ከማግኘት፣ ከትምህርት ነጥብ፣ ከትምህርት ጋር የተያያዙ ዕድሎች ወይም ከቅጥር ውሳኔዎች ጋር የተያያዙ መስፈርቶች ሆነው ሲቀርቡ።

ለ.   እንደነዚህ ዓይነት ግብዥዎች፣ ጥያቄዎች ወይም ምግባር ያላቸው ዓላማ ወይም የሚያስከትሉት ውጤት የአንድ ግለሰብ የትምህርት ወይም የሥራ አፈጻጸም ላይ አስፈሪ፣ አስጊ፣ አዋራጅ ወይም አስቀያሚ የሥራ ሁኔታ የሚፈጥር አግባብ የሌለው ተጽዕኖ ሲያመጡ።

5.8   ከላይ በተጠቀሱት ፍቺዎች መሠረት፣ አንድ አስተማሪ፣ ተቆጣጣሪ ወይም ሌላ በሥራ ላይ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ሥልጣን ያለው ግለሰብ በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር ሥራ ለመስጠት፣ ጥሩ የትምህርት ውጤት ለመስጠት፣ ደሞዝ ለመጨመር፣ ሹመት ለመስጠት፣ የተሻለ ጥቅማጥቅም ለመስጠት፣ ሥራን ለማራዘም፣ የተሻለ ነጥብ ለመስጠት፣ የቅጥር ወይም የትምህርት ደብዳቤ ለመጻፍ ወይም ሌሎች ነገሮችን ለመስጠት ግብረስጋዊ ጥያቄ ካቀረበ የጾታ ጉትጎታ ነው ይባልበታል። የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ሠራተኞች ከተማሪ ጋር ግብረስጋዊ ጓደኝነት መፍጠር በግልጽ የተከለከለ ነው።  ይህ ዓይነት ተግባር በማንኛውም ሁኔታ፣ በየትኛውም ዕድሜ ያለው ተማሪ ደረጃ፣ ተማሪው ፈቅዶም/ፈቅዳም ሆነ ሳይፈቅድ/ሳትፈቅድ ቢሆን ግብረስጋዊ ጥቃት ተብሎ የሚወሰድና የተከለከለ ነው።

የጾታ ጉትጎታ፣ ግብረስጋዊ ጥቃትን ወይም ማንኛውም ዓይነት በአልኮል መጠጥም ሆነ በአደንዛዥ ዕጽ መጠቀም ምክንያት ሙሉ በሙሉ አንድ ሰው ፈቃድ መስጠት በማይችልበት ሁኔታ ላይ ሆኖ፣ ወይም የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለበትን ሰው አስገድዶ ግብረስጋዊ ድርጊት የተፈጸመበትንም ሁኔታ ይጨምራል። የተለያዩ ድርጊቶች ማለትም አስገድዶ መድፈር፣ ግብረስጋዊ ዛቻ፣ ግብረስጋዊ ማስፈራራት ከግብረስጋዊ ጥቃት ይመደባሉ።  እንደነዚህ ዓይነት ግብረስጋዊ ጥቃቶች በሙሉ በ Title IX ሥር የተሸፈኑ የጾታ ጉትጎታ ዓይነቶች ናቸው።

ሁሉንም ከጾታዊ ጉትጎታ የሚመደቡ ሁኔታዎችን መዘርዘር ባይቻልም የሚከተሉት አግባብ የሌላቸው ምግባሮች ተገቢ ያልሆኑና ያለፈቃድ ከተከሰቱ ከጾታ ጉትጎታ የሚመደቡ ናቸው።  በእያንዳንዱ ሁኔታ ላይ ውሳኔው የሚወሰነው ክስተቱ በአጠቃላዩ ታይቶ የአኳኋኑ አስከፊነትና ስፋትም ከግምት ውስጥ ከገቡ በኋላ ነው።  የጾታ ጉትጎታ በሚከተሉት ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፣ የሚከተሉትን ግን ይጨምራል፦

- ያለፈቃድ የሚሰነዘሩ ግብረስጋዊ ግብዣዎች፣ በአካል መንካት ቢፈጸምም ባይፈጸምም

- ያለፈቃድ የሚሰነዘሩ ማፍጠጦች፣ ማፏጨቶች፣ ሰውነትን መዳበስ፣ ግብረስጋዊ ምልክቶች ወይም ስድቦች

- ግብረስጋዊ ቀልዶች፣ የጽሑፍ ወይም የቃል የሆኑ ግብረስጋዊ ንግግሮች፣ ስለ አንድ ግለሰብ አካል የሚሰነዘሩ አስተያየቶች፣ ስለ አንድ ግለሰብ የግብረስጋ ግንኙነት ታሪክ የሚሰነዘሩ አስተያየቶች፣ ጉድለቶች ወይም ጉብዝና

- ስለ ራስ ግብረስጋ ግንኙነቶች ውይይት ወይም ስለ ሌሎች የግብረሥጋ ግንኙነት ታሪክ ጥያቄዎች

- ግብረሥጋዊ የሆኑ ቁሳቁሶች፣ ስዕሎች፣ ካርቱኖች ማሳየት

የማግለል፣ የጥቃትና የጾታ ጉትጎታ ፍቺዎች ሰፊ ናቸው።  ከላይ ከተጠቀሱት ምሳሌዎች በተጨማሪ ሌላ ያልተፈለገ አውቀውም ሆነ ሳያውቁት ያንጸባረቁት በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በሥራ ላይ ለወንዶች፣ ለሴቶች፣ ሴትም ወንድም አይደለሁም ለሚሉ ሰዎች ጥላቻ የተሞላ፣ የሚያስከፉ፣ የሚያስፈራራ፣ የሚያዋርድ ሁኔታ የሚፈጥር ምግባር ከአግላይ፣ ጥቃታዊ እና/ወይም የጾታ ጉትጎታ ሊመደብ ይችላል።

*"መሥሪያ ቤት" ወይም "ትምህርት ቤት" ማለት በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ማህበራዊ ዝግጅቶችን፣ ጉዞዎችን፣ የስፖርት ዝግጅቶችን፣ ከሥራ ጋር የተያያዙ ጉዞዎችን ወይም ተመሳሳይ ከትምህርት ቤት ወይም ከሥራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ዝግጅቶችን፣ ከትምህርት በተጨማሪ የሚሰጡ እንቅስቃሴዎችን፣ የስፖርት ፕሮግራሞችን፣ ትምህርት ቤቱ ወዳዘጋጀው ዝግጅት መጓዝን ጨምሮ ያጠቃልላል።*

5.9 ማንኛውም በቀናነት የገባ ይግባኝን የሚያስተናግድ ወይም አንድ ክስ ላይ በማንኛውም መንገድ ተሳታፊ የሆነ ሠራተኛ ወይም ተማሪ ላይ የበቀል ምላሽ አይኖርም። በአንድ ይግባኝ ላይ በቀናነት የምስክርነት ቃል የሰጠ፣ የረዳ ወይም በምርመራው፣ ሂደቱ ወይም ይግባኙ ላይ የተሳተፈ ወይም በነዚህ የክስ ሂደቶች ላይ የተባበረ ማንኛውም ሠራተኛ ወይም ተማሪ ላይ የበቀል ምላሽ አይኖርም። ማንኛውም አስተማሪ፣ የትምህርት ቤት ሹም ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ በትምህርት ቤት መምሪያ ውስጥ ለሚገኝ ለከፍተኛ ሹም አንድ ተማሪ ክስ ወይም ተቃውሞ ለማቅረብ ሲሞክር ማስፈራራት ወይም ማዳከም አይችልም። ማናቸውም እነዚህን የመሰሉ ጥረቶች ለትምህርት ቤት ኮሚቴውና ዋና ለተቆጣጣሪው ወዲያውኑ ይተላለፋሉ።

5.10 በዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጠቀሱትን ማናቸውንም መብቶች የሚጥስ ማንኛውም ግለሰብ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ በክፍል 23.0 ላይ ባሉት አቅርቦቶች መሠረት አቤቱታ ሊቀርብበት ይችላል።

5.11 <u>የአካል እገታዎች</u>

የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ለሠራተኞቹና ለተማሪዎቹ ደህንነቱ የተጠበቀና ምርታማ የሥራና የትምህርት ቦታ የመፍጠር ፖሊሲ አለው፣ እንዲሁም በኬምብሪጅ የመንግሥት ትምህርት ቤት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ተማሪም ከማሳቹሴትስ የአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ ደንቦች ጋር የማይጣጣም የአካል እገታ ነጻ መሆኑን ማረጋገጥና የአካል እገታን የሚጠቀሙት በከፍተኛ ጥንቃቄ፣ በድንገተኛ ሁኔታዎች ላይ ሌሎች ሕጋዊና ጫና የማይፈጥሩ መንገዶችን መጠቀም ካልቻሉ ወይም አግባብ ከሌላቸው ብቻ ነው። የትምህርት ቤት ሠራተኞች የአካል እገታ መጠቀም የሚችሉት ሌላ ምንም ዓይነት መንገድ መጠቀም ካልቻሉና አንድ ተማሪን እና/ወይም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባልን ከአስቸኳይ፣ አደገኛ አካላዊ ጉዳት ለመጠበቅ ሲያስፈልግ ብቻ ነው። የአካል እገታ መጠቀም አስፈላጊ ከሆነ፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ተማሪው ላይ በአካል እገታው ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ይህ ፖሊሲ በመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚማሩ ተማሪዎች፣ ልዩ ትምህርት ለማግኘት ብቃት ኖሯቸው የተገኙ ተማሪዎችን ጨምሮ፣ የሚጠብቋቸው ፌዴራልና ስቴት ሕጎች ላይ ውስንነት አይፈጥርም። በተጨማሪም ይህ ፖሊሲ ማንኛውንም አስተማሪ፣ ሠራተኛ ወይም የመንግሥት ትምህርት መርሃ ግብር ተወካይ ተማሪዎችን፣ ሌሎችን ወይም እራሳቸውን ከአስቸኳይ፣ አደገኛ አካላዊ ጉዳት ለመጠበቅ አግባብ ያለውና አስፈላጊ ኃይል ከመጠቀም አያግዳቸውም።

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት አውራጃው ድህረ ገጽ ላይ ተለጥፈው የሚገኙ እንዲሁም ከከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ቢሮ ሊገኙ የሚችሉ ከዚህ ፖሊስ ጋር የተያያዙ የጽሑፍ ሂደቶችና መመሪያዎች አሏቸው፣ እነሱም የሚከተሉትን ይገልጻሉ፦ (1) ወዲያውኑ እርምጃ ሊያስወስዱ የሚችሉ አግባብ ያላቸው ለተማሪ ምግባር አጸፋ ምላሾች፣ እና (2) አንድ ኃይለኛ፣ እራሱን ሊጎዳ ያለ ተማሪን ለማስታገስ እና/ወይም በተማሪ ቡድኖች መካከል ወይም አንድ ተማሪ ላይ አደገኛ ሁኔታ ሲፈጠር ለማብረድ በመጀመሪያ ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው ሌሎች አማራጮች፣ እንዲሁም በአደገኛ ሁኔታዎች ላይ የአካል እገታን ላለመጠቀም ሌሎች መንገዶችን መጠቀም።

<u>የአካል እገታ ሂደቶች</u>

*ፍቺዎች*

*"ፈቃድ" ማለት ስምምነት የሚፈለግበት ጉዳይን በተመለከተ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ሙሉ መረጃ በትውልድ ቋንቋቸው ወይም በሌላ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በሚገባቸው መንገድ ቀርቦላቸው ጉዳዩ እንዲፈጸም መስማማታቸውን በጽሑፍ ሲያሳውቁና ስምምነቱ በፈቃደኝነት ሆኖ*

በማንኛውም ጊዜ ሊሰረዝ እንደሚችል ሲረዱ ነው። ስምምነቱ ጉዳዩን ማናቸውንም ተላልፈው የሚሰጡ መዝገቦችን (ካሉ) በዝርዝርና ለማን እንደሚተላለፉ የሚያገልጽ ነው።

"እገታ" ማለ የተማሪ አካላዊ እንቅስቃሴን በሚታገልበት ጊዜ ኃይል ተጠቅሞ መገደብ።

"አካላዊ እገታ" ማለት የአንድ ተማሪን የመንቀሳቀስ ነጻነት የሚከለክል ወይም በከፍተኛ ሁኔታ የሚገድብ ቀጥተኛ የአካል ንክኪ። አካላዊ እገታ ማለት ፊትን ወደ መሬት አድርጎ መያዝን፣ በቁሳቁስ ማሰርን ወይም በመድሃኒት ማገትን አይጨምርም። በተጨማሪም የአካል እገታ የሚከተሉትን አይጨምርም፡- ኃይል ሳይጠቀሙ የተማሪን ደህንነት ለመጠበቅ ወይም ራሱን እንዳይጎዳ ማገድ፣ አንድ ሙያ ለማስተማር፣ ትኩረትን ወደ ሌላ ለመሳብ፣ ለማጽናናት ወይም በአካል ሲያጅቡ የአካል መምሪያ መስጠት ወይም አጭር አካላዊ ንክኪ መፍጠር።

"በአካል ማጀብ" ማለት አንድ ሁከተኛ ተማሪ ደህንነቱ ወደተጠበቀ ቦት እንዲያመራ እጁን፣ የእጅ አንጓውን፣ ክንዱን፣ ትከሻውን ወይም ጀርባውን ለአጭር ጊዜ መንካት ወይም መያዝ ነው።

"በቁሳቁስ ማገት" ማለት የአንድ ተማሪን እንቅስቃሴ ወይም የተማሪን አንድ የሰውነት ክፍል መደበኛ እንቅስቃሴ ለማገት አንድ መሳሪያ መጠቀም ነው። ዶክተር ያዘዘው መከላከያ ወይም ማረጋጊያ መሳሪያ በቁሳቁስ እንደማገት አይቆጠርም። **ዶክተር ያዘዘውና የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ፈቃድ ሰጥተውበት ካልሆነ በስተቀር የቁሳቁስ ማገቻ መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።**

"ማግለል" ማለት አንድ ተማሪ እንዳይሄድ አድርጎ አንድ ክፍል ውስጥ ወይም አንድ አካባቢ ሳይፈልግ ብቻውን ማቆየት። ማግለል በ 603 CMR 46.02 ውስጥ እንደተጠቀሰው ዓይነት የተማሪ ቅጣት አይደለም። **የማግለል እጋታ በጥብቅ የተከለከለ ነው።**

"የተማሪ ቅጣት" ማለት የባሕርይ ድጋፍ ማድረጊያ ስልት ሲሆን አንድ ተማሪ እራሱ ፈልጎ ወይም አስተማሪ አዝዞት ለአጭር ጊዜ ከክፍል ትምህርቱ ተለይቶ እራሱን እንዲያረጋጋ ሲወጣ። በተማሪ ቅጣት ወቅት ተማሪው ያለፍላጎቱ አንድ ቦታ ብቻ እንዲሆን መወሰን የለበትም፣ ሁልጊዜ አንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ሊከታተለውም ይገባል። በማንኛውም ጊዜ ሠራተኛ ከተማሪው ጋር ሊሆን ወይም በቀላሉ እንዲገኝ ሆኖ መገኘት አለበት። የተማሪ ቅጣት ጊዜ የሚያበቃው ተማሪው እንደተረጋጋ ወይም ሰላሳ (30) ደቂቃ እንዳላፈ መሆን አለበት። የተማሪ ቅጣት በክፍሉ ውስጥ ቢሆን ይመረጣል። ማንኛውም ከክፍሉ ውጪ ለተማሪ ቅጣት ሊጠቀሙት ያሰቡት ቦታ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ያጸደቀው መሆን አለበት።

"መድሃኒት" ማለት አንድ ባሕርይን ጊዜያዊ በሆነ መልኩ ለመቆጣጠር መድሃኒት መስጠት ነው። **ዶክተር በግልጽ ያዘዘውና የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጽሑፍ ፈቃድ የሰጡበት ካልሆነ በስተቀር መድሃኒት መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።**

"ፊት ወደታች እገታ" ማለት አንድ ተማሪን በአንድ ቦታ ይዞ ለማቆየት ፊቱን መሬት ላይ ወይም ሌላ ቦታ ላይ አድርጎ፣ ጫን አድርጎ መያዝ ማለት ነው። **ፊት ወደታች እገታ መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።**

'የከፍተኛ ደርጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ" ማለት የመንግሥት ትምህርት ቤት መርሃ ግብር የማስተማር ሂደት አለቃ ወይም ተወካይ ነው።

<u>የእገታ አጠቃቀም</u>

ሌሎች ሁሉ ሕጋዊና ብዙ ተጽዕኖ የማያደርጉ አማራጮች ካልተሳኩ ወይም የተማሪውን ኃይለኝነትና ጥቃት፣ እራስን የሚጎዳ ባሕርይ እና/ወይም በተማሪዎች መካከል ወይም አንድ ተማሪ ላይ የሚከሰት

አደገኛ ባሕርይን ለማስወገድ አግባብ የሌላቸው ሆነው ከተገኙና ሌላ አማራጭ ከጠፋ የአካል እገታን መጠቀም ይቻላል፡፡ ማለትም **የአካል እገታን መጠቀም የሚቻለው በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ሌላ ምንም ዓይነት አማራጭ ከጠፋና የተማሪው ባሕርይ ለራሱ ወይም ለሌሎች ድንገተኛና ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነና ተማሪው በአፍ የሚነገረውን መመሪያ ካልተከተለ ወይም ሌሎች ብዙ ተጽዕኖ የማያደርጉ አማራጮች ተሞክረው ካልሰሩ ወይም አማራጮቹ ለሁኔታው ተገቢ ሆነው ካልተገኙ ብቻ ነው፡፡** ማንኛውም አካላዊ እገታ በእንደዚህ ዓይነት አግባብ ባለው ኃይል መወሰንና ለአጭር ጊዜ የሚጠቀሙት ሆኖ አንድ ተማሪን ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባልን ከድንገተኛና ከፍተኛ አካላዊ ጉዳት ለመጠበቅ መሆን አለበት፡፡ አካላዊ እገታ ሊደረግ የሚችለው ስለ አካላዊ እገታ በአግባቡ ሥልጠና ባገኙ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ብቻ ነው፡፡

<u>ሌሎች የእገታ አጠቃቀም ውስንነቶች</u>

የሚከተሉት አሠራሮች በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው፡- (1) ከላይ በተጠቀሱት አቅራቦቶች ጋር የማይጣጣም የእገታ አጠቃቀም፣ (2) እገታን እንደ ሥርዓት ማስያዣ ወይም እንደ ቅጣት መጠቀም፣ ንብረት ሲወድም ወይም የትምህርት ቤት ሥርዓትን ሲረብሹ እንደ አጸፋ መልስ መጠቀም ወይም ተማሪ አንድ የትምህርት ቤት ደንብን አላከብርም ሲል ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ የነገረውን መመሪያ አልከተልም ሲል፣ ወይም ድርጊቶቹ ድንገተኛና ከፍተኛ አካላዊ ጉዳት የሚያስከትሉ ሳይሆኑ በቃል ማስፈራራት በጥብቅ የተከለከለ ነው፣ (3)የፊት ወደታች እገታ መጠቀም፣ (4)የቁሳቁስ እገታ መጠቀም፣ (5)ዶክተር ያላዘዘውና የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጽሑፍ ፈቃድ ያልሰጡበት መድኃኒት መጠቀም፣ (6) ተማሪዎች መተንፈስ እንዳልቻሉ ምልክት ሲያደርጉ ወይም ከፍተኛ አደጋ ላይ ያሉ ሲመስሉ (ትንፋሽ እጥረትን፣ እጅግ በጣም ለተራዘመ ጊዜ ማልቀስ ወይም ማሳልን ጨምሮ) እገታን መጠቀም፡፡

እገታ ከምላሾች አንዱ ሆኖ የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ውስጥ መካተት አይችልም፡፡ ሆኖም በተደጋጋሚ እራሳቸውን የሚጐዳት ባሕርይ የሚያሳዩ ተማሪዎችን በተመለከተ በድንገተኛ ሁኔታ ላይና ለተወሰነ ጊዜ እገታ መጠቀምን እንደ ሐሳብ አድርገው የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊዎች ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ለብቻው በጽሑፍ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ ለምን ያክል ጊዜ እንደሆነ እገታውን ተጠቅመው፣ እየቀነሱ ሄደው እንደሚያቆሙ ዕቅዱ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በዝርዝር ማሳወቅ አለበት፡፡ የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ይህን በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ከለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጽሑፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

<u>አካላዊ እገታን ባግባቡ መጠቀም</u>

**አካላዊ እገታን መጠቀም የሚችሉት ተገቢውን ሥልጠና ያገኙ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ብቻ ናቸው፡፡** ሥልጠና ያገኙ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ማለት ወይ ጥልቀት ያለው ሥልጠና ያገኙ ግለሰቦች ወይም ከዚህ በታች የተገለጸውን አስፈላጊ መደበኛ ሥልጠና ያገኙ ግለሰቦች ናቸው፡፡ ሲቻል፣ አካላዊ እገታ የሚጠቀመው ሰው ቢያንስ በአንድ የእገታው ተሳታፊ ባልሆነ አዋቂ ምስክርነት ፊት መሆን አለበት፡፡ የትምህርት ቤት ሠራተኞች አካላዊ እገታ ሲጠቀሙ የሚጠቀሙት ኃይል ተማሪውን ወይም ሌሎችን ከአካላዊ ጉዳት ለመከላከል የሚበቃ መጠን ብቻ መሆን አለበት፡፡ በተጨማሪም የትምህርት ቤት ሠራተኞች አካላዊ እገታ ሲጠቀሙ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የደህንነት መስፈርቶች መሠረት ሆኖ ከሁሉም በላይ ደህንነት የሚጠብቀውን ዓይነትና ከሁኔታው ጋር የሚጣጣም ዓይነት መንገድ ተጠቅመው መሆን አለበት፣ እንዲሁም እገታ መጠቀሙን በተቻለ ፍጥነት ቶሎ ማቆም አለባቸው፡፡ ተማሪው እራሱም ሆነ ሌሎች ላይ አደጋ እንደማያደርስ እንደታወቀ፣ ወይም ተማሪው መተንፈስ እንዳልቻለ እንዳሳወቀ፣ ወይም ተማሪው ከፍተኛ ውጥርት ውስጥ እንደሆነ እንደታወቀ ለምሳሌ መተንፈስ ቢያቅተው ወይም ያለማቋረጥ ቢይለቅስ ወይም ቢያስል ወዲያውኑ አካላዊ እገታው መቆም አለበት፡፡ ሆኖም እነዚህ የሥልጠና መስፈርቶች አንድ አስተማሪን፣ ሠራተኛን ወይም የትምህርት ቤት ተወካይን ተማሪዎችን፣ ሌሎች ሰዎችን ወይም እራሳቸውን ከጥቃት፣ ወይም ከፈጣን፣ ኃይለኛ አካላዊ ጉዳት ለመከላከል ተገቢና አስፈላጊ የሆነ ኃይል ከመጠቀም አያግዳቸውም፡፡

## የደህንነት መስፈርቶች

**አንድ ተማሪን ከመተንፈስ ወይም ከመናገር በሚያግድ ሁኔታ እገታ መጠቀም ክልክል ነው።** የትምህርት ቤት ሠራተኞች እገታ በሚጠቀሙ ጊዜ ያለማቋረጥ የተማሪውን ሁኔታ፣ የቆዳ ቀለሙን፣ የሰውንነት ሙቀቱንና አተነፋፈሱን ጨምሮ መከታተል አለባቸው። ተማሪው እራሱ ላይ ወይም ሌሎች ላይ አደጋ እንደማያደርስ የትምህርት ቤት ሠራተኛው ካረጋገጠ በኋላ ወዲያውኑ እገታውን ማቆም አለበት። በተጨማሪም እገታዎችን ሲጠቀሙ አካል ላይ ጉዳት በማያመጡ መንገድ መሆን አለበት። **ተማሪው አካላዊ እገታ ላይ ሆኖ መተንፈስ እንዳልቻለ ካሳወቀ፣ ወይም ከፍተኛ ውጥርት ውስጥ እንደሆነ እንደታወቀ ለምሳሌ መተንፈስ ቢያቅተው ወይም ያለማቋረጥ ቢይለቅስ ወይም ቢያስል አካላዊ እገታው ወዲያውኑ መቆም አለበት፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞችም ሕክምና እንዲያገኝ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው።** አካላዊ እገታ መጠቀምን በተመለከተ የሚታወቅ የጤና ወይም የስነልቦና ውስንነት መኖሩን እና/ወይም የባሕርይ እርዳታ ዕቅዶች እንዳሉ፣ እንዲሁም በተማሪው የሕይወት ታሪክ ውስጥ የሚታወቅ ወይም አለ ተብሎ የሚገመት የስቃይ ገጠመኝ መኖሩን የትምህርት ቤት ሠራተኞች በመጀመሪያ አይተው ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። አካላዊ እገታ በሚያደርጉ ወቅት በማንኛውም ጊዜ የትምህርት ቤት ሠራተኞቹ የ Office of Student Services (ተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ) ጋር ደውለው የባሕርይ ባለሙያዎችን ማግኘት ወይም የ Crisis Intervention Team (የውጥረት ማስወገጃ ቡድን)ን መገናኘት ወይም ተማሪው ከፍተኛ አካላዊ ጥንቀት ላይ ከሆነ የሕክምና እርዳታ ለማግኘት ሌላ እርምጃ መውሰድ ይችላሉ።

## መከታተያ ሂደቶችና ማሳወቂያ መስፈርቶች

ተማሪው ከእገታ ከተለቀቀ በኋላ በተገቢው ጊዜ የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ የሚቀጥሉትን መከታተያ ሂደቶች በሥራ ላይ ማዋል አለበት፡-

ሀ. እገታውን ያስከተለውን ባሕርይ በተመለከተ ለመወያየት ከተማሪው ጋር እገታውን መቃኘት፣

ለ. እገታውን ከተጠቀሙት የትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር ትክክለኛ የእገታ ሂደቶች መከተላቸውን ለማወቅ ስለ ጉዳዩ ውይይት ማካሄድ፣ እና

ሐ. ጉዳዩን ካዩ የዓይን ምስክር ተማሪዎች ጋር ክትትል ማድረግ፣ ከአስተማሪና ከአማካሪ ጋር ውይይትን ወይም የመልሶ አዳሽ አሠራሮችን ጠቀሜታ ጨምሮ፣ እና

መ. የእገታው ማስታወቂያ በጽሑፍ ወደ ተማሪ አገልግሎቶች ቢሮና ወደ ከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ቀጥተኛ አለቃ መላክ አለበት።

ትምህርት ቤቱ የሚከተላቸው ማሳወቂያ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. አካላዊ እገታ በተጠቀሙት ቁጥር፣ የተማሪውን ስም ጨምሮ፣ የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮና የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ቀጥተኛ አለቃ በጽሑፍ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

ለ. አንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛ አካላዊ እገታ በሚጠቀምበት ጊዜ ተማሪው ላይ ጉዳት ካስከተለ በተቻለ መጠን በፍጥነት እገታ የተደረገበት የትምህርት ቀን ሳይገባደድ የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ወይም ተወካዩን በቃል ማሳወቅ አለበት። የእገታውን መገምገሚያ የሚሆን በጽሑፍ የቀረበ ማሳወቂያ ለትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተቆጣጣሪ እገታው ከተፈጸመ ቢበዛ ከአንድ ቀን

ሳያልፍ መቅረብ አለበት። እገታውን የተጠቀመው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከሆነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ማሳወቂያውን አዘጋጅቶ ለተቆጣጣሪው ካስረከበ በኋላ ተቆጣጣሪው የሰየመው አንድ ቡድን ግምገማውን ያካሂዳል።

ሐ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተቆጣጣሪ እካላዊ እገታ የተከሰተባቸውን ሁኔታዎች በሙሉ በመዝገብ ይይዛል።

መ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ተወካይ እገታው ጥቅም ላይ በዋል በሃያ ዓራት (24) ሰዓት ውስጥ የተማሪውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በተቻለ መጠን በፍጥነት በቃል ያሳውቃቸውና በሶስት (3) የትምህርት ቀን ውስጥ ደግሞ የጽሑፍ ደብዳቤ መላክ አለበት፡፡ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው እገታውንና ማሳወቂያው ውስጥ ስለተጻፈው መረጃ ምላሽ ለመስጠጥ ለተማሪውና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ዕድል ይሰጣል።

ሠ. አካላዊ እገታ ተማሪ ላይ ጉዳት በሚያስከትልበት ጊዜ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ የጽሑፍ ማሳወቂያውን ግልባጭና አካላዊ ጉዳቱ ከመከሰቱ ከሰላሳ (30) ቀን በፊት ተከስተው የነበሩ ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች የያዘውን የትምህርት ቤቱን መዝገብ ግልባጭ ለOffice of the Superintendent (የዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ) ያቀርባል። **ይህ ሰነድ ለዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ መቅረብ ያለበት የጽሑፍ ማሳወቂያው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ጋር በደረሰ በአንድ (1) ቀን ውስጥ መሆን አለበት።** አንድ ተማሪ በሰባት (7) ዓመት ውስጥ ሁለት (2) የተለያየ ጊዜ ወይም በሰላሳ (30) ቀን ውስጥ ሶስት (3) የተለያየ ጊዜ እገታ ከተደረገበት የከፈተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተማሪው የሚያስፈልገው ምን እንደሆነ ግምገማ የሚያደርግ የተማሪ ድጋፍ ቡድን ይሰበስባል። ግምገማው ላይ የክፍሉ ቡድን አባሎች እና ሌሎች የመርሃ ግብሩ ሠራተኞች መሳተፍ ካለባቸው የከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ እንዳስፈላጊነቱ ይወስናል። እያንዳንዱ የተማሪ ድጋፍ ቡድን አባል በጽሑፍ የቀረቡትን የእገታ ማሳወቂያዎችና ተማሪውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የሰጡትን ማንኛውንም አስተያየቶችና የእገታ አጠቃቀሙን በተመለከተ ያነባል። የተማሪ ድጋፍ ቡድኑ ግምገማውን ሲያደርግ እንደነዚህ ዓይነት ማሳወቂያዎችን ከመቃኘትና ከመወያየት በተጨማሪ እያንዳንዱን እገታ ያስከተለውን ሁኔታ፣ ሰዓቱን፣ ቀኑን፣ አስቀድሞ የተፈጠሩ ክስተቶችና የሚመለከታቸውን ግለሰቦች ያጤናል። ግምገማው ማገባደጃው ላይ ሁኔታዎች እንዲባባሱ ያደረጉ ነገሮች ካሉ ለእነሱ መፍትሄ በማቅረብ፣ ከእገታ ሌላ አማራጭ መጠቀም ይቻል እንደሆነ፣ ሁኔታዎችን ለማብረድ መጠቀም የሚችሉት መንገዶች ካሉና ወደፊት እገታን ላለመጠቀም የሚያስችሉ ሌሎች ስልቶችንና ውሳኔዎችን ያቀርባል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊ የእገታው ተሳታፊ ከነበረ የተማሪ ድጋፍ ቡድን ውይይቱን የሚመራው ዋና ተቆጣጣሪው የሰየመው ብቃት ያለው ግለሰብ ይሆናል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊ የተማሪ ድጋፍ ቡድኑ ያደረገው እያንዳንዱ ግምገማ በመዝገብ መቀመጡንና የ Massachusetts Department of Elementary and Secondary Education (የማሳቹሴትስ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መምሪያ) በጠየቀ ጊዜ ለማቅረብ ዝግጁ መሆን አለበት።

ረ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ባጠቃላይ የትምህርት ቤቱን የእገታ አጠቃቀም መረጃ ወርሃዊ ቅኝት ያካሂዳል። ይህ ቅኝት በእገታዎች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ለምሳሌ የተከሰቱበትን ሰዓት፣ ቀን ወይም የሚመለከታቸውን ግለሰቦች፣ ባጠቃላይ በትምህርት ቤቱ ውስጥና በየተማሪው ላይ የተከሰቱት የእገታዎች ቁጥርና ርዝመት እንዲሁም ከእገታ የመጡ ጉዳቶች ካሉ ብዛታቸውንና ዓይነታቸውን ከግምት ያስገባ ይሆናል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የትምህርት ቤቱ የእገታ መከላከያና አስተዳደር አሠራሮችና ሂደቶች ማሻሻል ያስፈልጋቸው ወይም ይገባቸው እንደሆነ፣ ለሠራተኞች ተጨማሪ የእገታ መቀነሻ/ማስወገጃ ሥልጠና ለምሳሌ አዎንታዊ የባሕርይ ማሻሻያና ድጋፍ ያስፈልግ እንደሆነና ሌሎች ተመሳሳይ እገታ መቀነሻ ወይም ማስወገጃ እርምጃም እንዲዳባቡ ያስፈልግ እንደሆነ ይወስናል።

<u>የአውራጃው የሥልጠና መስፈርቶች</u>

ሀ. ለሁሉም የመርሃ ግብሩ ሠራተኞች

የትምህርት ዓመቱ በተጀመረ በመጀመሪያው ወር ውስጥ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የእገታ ማስወገጃና የባሕርት ድጋፍ ሥልጠና፣ እገታ መጠቀም ሲያስፈልግ መስፈርቶቹ ምን እንደሆኑና ይህንን ፖሊሲ ለሁሉም የመርሃ ግብሩ ሠራተኞች ማቅረብ አለበት። በተጨማሪም ሁሉም ከትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ በኋላ ለተቀጠሩ ሠራተኞች፣ በተቀጠሩ በመጀመሪያ ወር ውስጥ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው በዚህ ፖሊሲ ላይ ሥልጠና ማቅረብ አለበት። ሥልጠናው የሚከተሉትን ያካተተ ይሆናል፦ (ሀ) ይህ ፖሊሲና የተያያዙ ዋና ተቆጣጣሪው ያጎለበታቸው ሂደቶችና መመሪያዎች፣ (ለ) እገታ ከማስፈለጉ በፊት መፍትሔዎች፣ ችግር ያላቸው ባሕርዮችን ማብረድና በድንገተኛ ሁኔታዎች ላይ ከእገታ ሌላ ሊጠቀሟቸው የሚችሏቸው አማራጮች፣ ከማግለል ሌላ ዓይነት ቅጣት መጠቀም ጨምሮ፣ (ሐ) ድንገተኛ እገታ የሚያስፈልገው ባሕርይ ሲኖር መጠቀም የሚችሏቸውን የእገታ ዓይነቶችና ተያያዥ የደህንነት መስፈርቶች፣ እገታ ሲጠቀሙ በተለይ የተወሰነ እገታን ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙ ተማሪ ላይ ጉዳት የመድረስ ዕድሉ እንደሚጨምር የሚገልጽ መረጃን ጨምሮ፣ (መ) የታወቀ የጤና ወይም የስነ ልቦና ችግር ያለበት ተማሪ ላይ አካላዊ እገታ መጠቀም እና/ወይም ለአንድ ተማሪ የግል የባሕርይ እርዳታ ዕቅዶች፣ የታወቀ ከፍተኛ ውጥረት በሕይወት ታሪኩ ላይ ሲኖር፣ እና (ሠ) እገታውን መጠቀም እንዳያስፈልግ ተማሪው፣ ሠራተኛውና ቤተሰብ ያላቸው ሚና፣ እና (ረ) በ603 C.M.R. 46.03(3) መሠረት አካላዊ እገታን ስለመጠቀም ጥልቀት ያለው ሥልጠና ያገኙ የመርሃ ግብር ሠራተኞችን ለይቶ ማወቅ። 603 C.M.R. 46.03(2)ን ይመልከቱ።

ለ. አካላዊ እገታዎችን ባግባቡ ስለመጠቀም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሁሉ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ፈቃድ ላላቸው ሠራተኞች

የትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊ አካላዊ እገታዎችን ባግባቡ ስለመጠቀም በትምህርት ቤቱ ውስጥ ሁሉ ትክክለኛ መረጃ ለመስጠት ፈቃድ ያላቸው ሠራተኞች እነማን እንደሆኑ ይለያል። ጥልቀት ያለው የሥልጠናው ይዘታ በብቃት ላይ የተመሠረተ ይሆንና ርዝመቱ ቢያንስ አሥራ ስድስት (16) ሰዓት ይሆናል። እነዚህ ግለሰቦች በሚቀጥሉት የትምህርት ዓመታት ውስጥ ርዝመቱ ከስምንት (8) ሰዓት ያላነሰ ቢያንስ አንድ የክለሳ ሥልጠና መውሰድ አለባቸው። ሥልጠናው ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦ (ሀ) አካላዊ እገታን ከመጠቀም ለመቆጠብ አግባብ ያላቸው ሂደቶች፣ ችግር ያለውን ባሕርይ ማብረድን ጨምሮ፣ ግንኙነት ማጎልበትና ከእገታ ይልቅ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም፣ (ለ) ወደ አካላዊ እገታ ሊያመሩ የሚችሉ ተማሪ ላይ የሚታዩ ልዩ አደገኛ ባሕርዮችን መለየትና መግለጽ እንዲሁም እገታ መጠቀም አስፍላጊ መሆኑን ለማወቅ ክስተቶች ጉዳት የማስከተል ዕድላቸው ምን ያክል እንደሆነ ለመወሰን የሚያስችሉ ዘዴዎች፣ (ሐ) አካላዊ እገታን ሰው ላይ የመጠቀምና እራስ ላይ የማድረስ አስመስሎ ሙከራ፣ እገታ የሚደረግበት ሰው/ዎች ላይ ያለውን ተጽዕኖ በተመለከተ ትምህርት መስጠት፣ በእገታ ላይ ውጥረት መፈጠሩን በቅርብ መከታተልና የሕክምና እርዳታ ማግኘት፣ (መ) የመመዝገብና የማሳወቂያ መስፈርቶችን በተመለከተ ትምህርትና የጉዳቶችና የአቤቱታዎች ምርመራ፣ (ሠ) አካላዊ እገታ ተማሪውና ቤተሰቡ ላይ ያለውን ተጽዕኖ፣ እገታ ማድረግ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ተጽዕኖ እንዳለው መገንዘብ፣ እና (ረ) ተሳታፊዎች አካላዊ እገታ የማድረግ ብቃት እንዳላቸው በተግባር ማሳየት። 603 C.M.R. 46.03(3) and 46.03(4)ን ይመለከቱ።

<u>አቤቱታ ማቅረቢያ ሂደቶች</u>

ሀ. አካላዊ እገታ አጠቃቀምን በተመለከተ ያለ ቅሬታን አፊሲዬላዊ ባልሆነ መንገድ መፍታት

ስለ አንድ እገታ አጠቃቀም ቅሬታ ያለው ተማሪ ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች መደበኛ ሥርዓትን ተከትለው አቤቱታ ከማስገባታቸው

በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ተገናኝተው ችግሩን ለመፍታት መሞከር ይችላሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከላይ እንደተጠቀሰው የአካል እገታ እንደተከሰተ የሚገልጸው የጽሑፍ ማሳወቂያው በደረሳቸው በአሥር (10) ቀን ውስጥ ተማሪው ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ያላቸውን ቅሬታ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ጋር ይዘው መቅረብ ይችላሉ። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የተሰጠው ሥልጣን እስከሚፈቅደው ድረስ አቤቱታውን ትክክለኛ በሆነ መንገድና በፍጥነት ለመፍታት ይሞክራል። ተማሪው እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች መፍትሄውን አጥጋቢ ሆኖ ካላገኙት ወይም ተማሪው እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ኦፊሲዬላዊ ባልሆነ መንገድ ችግሩን መፍታት የማይፈልጉ ከሆነ፣ ተማሪው እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከዚህ በታች በተገለጸው መደበኛ ሥርዓት መሠረት አቤቱታ ማስገባት ይችላሉ።

ለ. አካላዊ እገታ አጠቃቀምን በተመለከተ ያለ ቅሬታን መደበኛ ሥርዓት ተከትሎ መፍታት ስለ አንድ እገታ አጠቃቀም ቅሬታ ያለው ተማሪ ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች Office of the Superintendent (የዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ) ጋር በጽሑፍ አቤቱታ በማስገባት ቅሬታውን ለመፍታት መሞከር ይችላሉ። ተማሪው እና/ወይም የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከላይ እንደተጠቀሰው ከትምህርት ቤቱ የአካል እገታ እንደተከሰተ የሚገልጸው የጽሑፍ ማሳወቂያው በደረሳቸው በሃያ (20) ቀን ውስጥ ይህንን ደብዳቤ Office of the Superintendent ጋር ማስገባት አለባቸው። በጽሑፍ የቀረበው አቤቱቷ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡- (ሀ) የተማሪውን ስም፣ (ለ) አካላዊ እገታው ተከስቷል የተባለበትን ትምህርት ቤት ስም፣ (ሐ) አካላዊ እገታው ላይ የተሳተፉትን የግለሰቦች ስም፣ (መ) የአቤቱታው ምክንያት፣ (ሠ) የተፈለገው እርማት።

የዋና ተቆጣጣሪው ቢሮ አቤቱታው ከደረሰው በኋላ ወዲያውኑ በተወካዮቹ አማካኝነት አቤቱታውን በተመለከተ ምርመራ ያካሂዳል። በምርመራው ወቅት የዋና ተቆጣጣሪው ቢሮ እና/ወይም ተወካዮቹ አቤቱታውን በተመለከተ መረጃ አላቸው የተባሉትን ግለሰቦች ይገናኛል። እያንዳንዱ ክስተት ስለሚለያይ ምርመራውን ለማካሄድ ጥብቅ የሆኑ የጊዜ ገደቦች ማስቀመጥ አይቻልም። የዋና ተቆጣጣሪው ቢሮ እና/ወይም ተወካዮቹ አቤቱታው በተቻለ መጠን በፍጥነት መስተናገዱን ያረጋግጣሉ። የዋና ተቆጣጣሪ ቢሮ መደበኛ ምርመራውን ካጠናቀቀ በኋላ አቤቱታውን ያስገባውን ሰው ይገናኝና የምርመራውን ውጤትና የእርማት እርምጃ ያስፈልግ እንደሆነ የደረሰበትን ውሳኔ ያሳውቃል።

<u>ሌሎች አቤቱታ ማቅረቢያ ሂደቶች</u>

አንድ ተማሪ በሕግ በተጠበቁት ልዩ ምልክቶች ማለትም በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አቤቱታ ካለው የ Cambridge Public Schools "Non-Discrimination Policy and Prohibition Against Sexual Harassment"ን (የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች "ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላ") የአቤቱታ ሂደት ከመከተል እዚህ ክፍል ላይ የቀረቡት ደንቦች አያግዱትም። በተጨማሪም በዚህ *መመሪያ* መሠረት የሙብት መንፈግን በተመለከተ ያለ አቤቱታን ለመፍታት እዚህ ክፍል ላይ ያሉት አቅራቦቶች *የመመሪያው* ክፍል 23.0 ላይ ያለውን የአቤቱታ ሂደት ከመከተል አያግዱትም።

5.12 <u>ጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ</u>

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ሁሉ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ እንክብካቤና አክብሮት የተሞላ አካባቢ ለመፍጠር ቃል የገባ ሲሆን፣ አስፈራሪ ተማሪዎች፣ በኢንተርኔት የሚያስፈራሩትንም ጨምሮ እንዲሁም ስለሚያስፈራሩ ተማሪዎች ጥቆማ የሚያደርጉ፣ አንድ ምርመራ ላይ መረጃ የሚሰጡ፣

ምስክር ሆነው የሚቀርቡ ወይም ስለ አስፈራሪው ጥሩ መረጃ ይዘው የሚቀርቡ ላይ አጸፋ እርምጃ መውሰድን በጥብቅ የሚከለክል ነው። በትምህርት ቤት አስተዳደርና ሠራተኛ፣ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦችና የማህበረሰብ አባሎች ትብብር የጎለበቱ በቦታው ላይ የተመሠረቱ እርምጃዎች የሚከተሉትን ለማድረግ ይጥራሉ፡- (1) በሁሉም ዕድሜ ያሉ ተማሪዎችና ሁሉም ዓይነት ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ ሆኖ በጥሞና እንዲያስቡና በራሳቸው እንዲተማመኑ መርዳት እና (2) ተማሪዎች ለሚዘግቡትና አዋቂዎች እራሳቸው ላስተዋሉት ነገር አዋቂዎች ውጤታማ ምላሽ እንዲሰጡ መርዳት።

ማስፈራራት ማለት አንድ ወይም ብዙ ተማሪ፣ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ማለትም አስተማሪን፣ አስተዳዳሪን፣ የትምህርት ቤት ነርስን፣ የካፌቴሪያ ሠራተኛን፣ ጽዳት ሠራተኛን፣ አውቶቡስ አሽከርካሪን፣ የስፖርት አሰልጣኝን፣ ከትምህርት በተጨማሪ ለሚሰጡ እንቅስቃሴዎች አማካሪን ጨምሮ በተደጋጋሚ በጽሑፍ፣ በቃል ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወይም በአካል ድርጊት ወይም በምልክት ተጠቂው ላይ የሚከተሉትን ሲያስከትሉ ነው፡- (1) ተጠቂው ላይ አካላዊ ወይም ስሜታዊ ጉዳት ወይም ንብረቱ ላይ ጉዳት፣ (2) ተጠቂው ባግባቡ እራሱ ላይ ወይም ንብረቱ ላይ ጉዳት ይደርስብኛል ብሎ ሲፈራ፣ (3) ለተጠቂው በጥላቻ መንፈስ የተሞላ ሁኔታ በትምህርት ቤት ውስጥ ሲፈጥር፣ (4) በትምህርት ቤት ውስጥ የተጠቂው መብቶች ላይ ተጽዕኖ ሲያደርግ፣ ወይም (5) የትምህርት ሂደቱን ወይም የትምህርት ሥርዓቱን በተጨባጭና በከፍተኛ ሁኔታ ሲያጨናግፍ። በስቴቱ ሕግ መሠረት የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች አንዳንድ ተማሪዎች በሚከተሉት መለያዎች ምክንያት ከሌሎች የበለጠ የማስፈራራት ተጠቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያውቃል፡- ማለትም በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ ወይም ጾታ መግለጫ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ፣ የገቢ ደረጃ፣ ቤት አልባነት፣ የትምህርት ነጥብ፣ አካላዊ ገጽታ፣ የወላጅ ሁኔታ ወይም ከእነዚህ ነገሮች ውስጥ አንድ (1) ወይም ከዛ በላይ ካለው ሰው ጋር አብሮ በመሆን። በዚህ ፖሊሲ ላይ ማስፈራራት ማለት የኢንተርኔት ማስፈራራትንም ይጨምራል።

<u>በኢንተርኔት ማስፈራራት</u> ማለት በኤሌክትሮኒክ መሳሪያ በኩል ማስፈራራት ሲሆን፣ ይህም ምልክቶችን፣ ጽሑፎችን፣ ስዕሎችን፣ ድምጾችን፣ መረጃን በሙሉ ወይም በከፊል በድብቅ ማዳመጫ፣ በሬዲዮ፣ በኤሌክትሮማግኔቲክ፣ በኤሌክትሮኒክ ፎቶ ሲስተም፣ በኢሜል፣ በኢንተርኔት መነጋገሪያ መንገዶች፣ በኢንስታንት መልዕክት ወይም በፋክስ ማስተላለፍን ይጨምራል። በኢንተርኔት ማስፈራራት የሚከተሉትንም ይጨምራል፡- (1) ያልሆኑትን ሰው ነኝ ብሎ ድህረ ገጽ ወይም ብሎግ መክፈት ወይም (2) አውቀው ያልሆኑትን ሰው ነኝ ብለው በዛ ሰው ስም መልዕክቶችና ጽሑፎች ማቅረብ፣ ሌላውን ሰው ማስመሰሉ ከመስፈርቶች (1) እስከ (5) ያሉትን የማስፈራራት ፍቺ ውጤቶች ካስከተሉ። በኢንተርኔት ማስፈራራት ማለት በተጨማሪም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ለብዙ ሰዎች መረጃ ማሰራጨት ወይም ከአንድ ሰው በላይ የሚያየው ቦታ ላይ ይህን መረጃ መለጠፍ፣ መረጃው ከመስፈርቶች (1) እስከ (5) ያሉትን የማስፈራራት ፍቺ ውጤቶች ካስከተሉ።

<u>አጥቂ ወይም ወንጀለኛ</u> ማለት በአካልም ሆነ በኢንተርኔት የሚያስፈራራ ወይም አጸፋ መላሽ ተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ማለትም አስተማሪን፣ አስተዳዳሪን፣ የትምህርት ቤት ነርስን፣ የካፌቴሪያ ሠራተኛን፣ ጽዳት ሠራተኛን፣ አውቶቡስ አሽከርካሪን፣ የስፖርት አሰልጣኝን፣ ከትምህርት በተጨማሪ ለሚሰጡ እንቅስቃሴዎች አማካሪን፣ የትምህር ቤት በጎ ፈቃደኛ አገልጋይን፣ ሻጭ ወይም በትምህርት ቤት አውራጃው ኮንትራት ሥር የሚሠራ ሰውን ጨምሮ ነው።

<u>በጥላቻ የተሞላ አካባቢ</u> ማለት በ M.G.L. c. 71, § 37O ውስጥ በተሰጠው ፍቺ መሠረት፣ በማስፈራራት ምክንያት የተማሪው ትምህርት ሁኔታ በዛቻ፣ ውርደት ወይም ስድብ የተሞላ ሲሆን መጠኑ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የተማሪውን የትምህርት ሁኔታ እስከመቀየር ደርሷል ማለት ነው።

<u>በቀል</u> ማለት ማስፈራራትን የሚጠቁም፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ የሚሰጥ ወይም የማስፈራራት ምስክር ሆኖ የሚታመን መረጃ ያለው ተማሪ ላይ ዛቻ ማድረግ፣ አጸፋ ምላሽ መስጠት ወይም መጎትጎት ማለት ነው።

ሠራተኛ ማለት አስተማሪዎችን አስተዳዳሪዎችን፣ አማካሪዎችን፣ የትምህርት ቤት ነርሶችን፣ የካፌቴሪያ ሠራተኞችን፣ ጽዳት ሠራተኞችን፣ አውቶቡስ አሽከርካሪዎችን፣ ስፖርት አሰልጣኞችን፣ የትርፍ ሰዓት እንቅስቃሴ አማካሪዎችን፣ የድጋፍ ሠራተኞችንና ሙያተኞችን ይጨምራል።

ዒላማ ወይም ተጠቂ ማለት ማስፈራራት፣ የኢንተርኔት ማስፈራራት ወይም አጸፋ መልስ የደረሰበት ተማሪ ወይም አዋቂ ነው።

ማስፈራራት በብዙ መልክና በማንኛውም ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። ማስፈራራት የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፦ ዛቻን ለምሳሌ መሳደብ፣ ማህበራዊ ማግለል ለምሳሌ ማራቅ ወይም ስም ማጥፋት፣ ወይም አካላዊ ጥቃት ለምሳሌ ተማሪን ወይም የተማሪውን ንብረት ማጥቃት። ማስፈራራት ለሁሉም የትምህርት ቤት ማህበረሰብ የፍርሃት ስሜት ሊፈጥር ይችላል። በተጨማሪም አንድ ተማሪ ትምህርት ቤት መሄዱን፣ ትምህርት ቤት ውስጥ የመማር ችሎታው፣ የትምህርት ቤት ሕንጻ ውስጥ መራመዱን፣ የትምህርት ቤት ካፌቴሪያ ውስጥ መብላት መቻሉን፣ የትምህርት ቤቱ መዝናኛ ቦታዎች ላይ መጫወት መቻሉን፣ ልዩ ፕሮግራሞች ወይም ከትምህርት ውጪ ያሉ ክፍሎች ውስጥ መሳተፍ መቻሉን ወይም ከቤት ወደ ትምህርት ቤት መመላለሱ ላይ ተጽዕኖ ፈጥሮ አላስፈላጊና አላግባብ የሆነ ጭንቀት ሊፈጥር ይችላል። በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ "በጥላቻ የተሞላ አካባቢ" ማለት በማስፈራራት ምክንያት የተማሪው ትምህርት ሁኔታ በዛቻ፣ ውርደት ወይም ስድብ የተሞላ ሲሆን መጠኑ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ የተማሪውን የትምህርት ሁኔታ እስከመቀየር ደርሷል ማለት ነው። መፍትሄ ያልተገኘላቸው የማስፈራራት ባሕርዮች ወጣቶች ላይ አስከፊ ውጤቶች ሊያስከትሉ ይችላሉ፦ የሥነ ልቦና ውድቀትን፣ ትምህርት ላይ ድክመትና ከትምህርት ቤት መቅረትን ጨምሮ። የማስፈራራት ባሕርዮች ዝም ከተባሉ ሌሎች ተማሪዎች የሚያገኙት መልዕክት አሉታዊ ባሕርይ መያዝ ተቀባይነት እንዳለው ነው።

በትምህርት ቤቱ ውስጥ ማስፈራራት በሕግ የተከለከለ ሲሆን የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች በጭራሽ የሚቀበለው ነገር አይደለም። በዚህ ፖሊሲ ላይ "ትምህርት ቤት" ሲባል ትምህርት ቤቶችን፣ የትምህርት ቤት ግቢዎችን፣ ወደ ትምህርት ቤት እና/ወይም ትምህርት ቤቱ ድጋፍ ወደሚያደርግባቸው ዝግጅቶች መመላለስን፣ የትምህርት ቤት ግቢ ጎን ያሉ ንብረቶችን፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ እንቅስቃሴዎችን፣ ድግሶችን፣ በትምህርት ቤት ውስጥም ውጪም ያሉ መርሀ ግብሮችን (ለምሳሌ ማህበራዊ ዝግጅቶች፣ ጉዞዎች፣ የስፖርት ዝግጅቶች ወይም ተመሳሳይ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች)፣ የትምህርት ቤት አውቶቡስ መጠበቂያ ጣቢያን፣ አውቶቡስ ውስጥ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት አውራጃው ንብረት የሆነ ወይም የተከራየው ተሽከርካሪን፣ ከትምህርት ቤት ወይም ወደ ትምህርት ቤት ጉዞ ላይ ወይም የትምህርት ቤት አውራጃው ንብረትነት የሆነ ወይም የትምህርት ቤት አውራጃው የሚከራየው ወይም የሚጠቀመው ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ በመጠቀም፣ እንዲሁም ከትምህርት ቤት ጋር ያልተያያዘ ቦታ፣ እንቅስቃሴ፣ ዝግጅት ወይም መርሃ ግብር ወይም የትምህርት ቤት አውራጃው ንብረትነት ያልሆነ ወይም የትምህርት ቤት አውራጃው የማይከራየው ወይም የማይጠቀመው ኤሌክትሮኒክ መሳሪያ በመጠቀም የሚደረግ ማስፈራራት ትምህርት ቤት ውስጥ የጥላቻ ስሜት የሚፈጥር ከሆነ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ የተጠቂውን ወይም የምስክሮችን መብቶች የሚነካ ከሆነ፣ እንዲሁም የትምህርት አሰጣጡን ወይም የትምህርት ሥርዓቱን የሚረብሽ ከሆነ ሁሉንም ያጠቃልላል።

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የማስፈራራት ክሶችን በቁም ነገር የሚወስድ ሲሆን የማስፈራራት ክሶች ሲቀርቡ በፍጥነት መልስ ይሰጣል። በተጨማሪም ማስፈራራትን የሚጠቁም፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ የሚሰጥ ወይም የማስፈራራት ምስክር ሆኖ የሚታመን መረጃ ያለው ሰው ላይ በቀል ማድረግ የተከለከለ ነው።

አንድ ተማሪ ማስፈራራት ደርሶበታል ወይም ማስፈራራትን በመጠቆሙ፣ የማስፈራራት ምርመራ ላይ መረጃ በመስጠቱ ወይም ምስክር ሆኖ የሚታመን መረጃ ስላለው በቀል ደርሶበታል ብሎ አንድ ተማሪ፣ የአንድ ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች፣ ሠራተኛ ወይም ሌላ የማህበረሰቡ አባል ካመነ ተማሪው የሚሄድበት ትምህርት ቤት ውስጥ ያለው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ጋር ጉዳዩን ማቅረብ አለባቸው። ይህ በቃል ወይም በጽሑፍ ሊደረግ ይችላል። የማስፈራራት ክሶች

እና/ወይም ማስፈራራትን በመጠቆሙ፣ የማስፈራራት ምርመራ ላይ መረጃ በመስጠቱ ወይም ምስክር ሆኖ የሚታመን መረጃ ስላለው የበቀል ክሶች ተማሪው የሚሄድበት ትምህርት ቤት ውስጥ ያለው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ጋር ስምን ሳይገልጹ በምስጢር ማቅረብም ይቻላል። ሆኖም እባክዎን ልብ ይበሉ፦ በምስጢር ክስ ሲደርስ በሱ ላይ ብቻ ተመስርቶ አንድ ተማሪ ላይ የቅጣት እርምጃ አይወሰድም።

*ሁሉም* የትምህርት ቤት ሠራተኞች (አስተማሪዎችን አስተዳዳሪዎችን፣ አማካሪዎችን፣ የትምህርት ቤት ነርሶችን፣ የካፌቴሪያ ሠራተኞችን፣ ጽዳት ሠራተኞችን፣ አውቶቡስ አሽከርካሪዎችን፣ ስፖርት አሰልጣኞችን፣ የትርፍ ሰዓት እንቅስቃሴ አማካሪዎችን፣ የድጋፍ ሠራተኞችንና ሙያተኞችን ጨምሮ) የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲና የማስፈራራት ማስወገጃና ማስተናገጃ ዕቅድን በተመለከተ ዓመታዊ ስልጠና ያገኛሉ። የሠራተኞች ግዴታዎችና ኃላፊነቶች በኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲና የማስፈራራት ማስወገጃና ማስተናገጃ ዕቅድ ውስጥና *የሠራተኞች ፖሊሲዎች መመሪያ* ውስጥ ይገኛሉ። ሆኖም *ሠራተኞች ሁሉ ያዩትን ወይም የሰሙትን የማስፈራራት ወይም የአጸፋ መልስ ሁኔታ ወዲያውኑ ለትምህርት ቤቱ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ተወካዩ የ CPS ማስፈራራት ማሳወቂያ ቅጽ (የትምህርት ቤቱ አውራጃ ድህረ ገጽ ላይ የሚገኝ) የማሳወቅ ድጌታ* እንዳለባቸው ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው። ለትምህርት ቤቱ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ለተወካዩ የማሳወቅ ግዴታ ሠራተኛው በትምህርት ቤት አውራጃው የባሕርይ አስተዳደርና ቅጣት ፖሊሲዎችና ሂደቶች መሠረት የባሕርይ ወይም የሚያስቀጡ ክስተቶች ሲካሄዱ ምላሽ ለመስጠት ያለውን ሥልጣን ይወስነዋል ማለት አይደለም።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ክሱ ሲደርሰው ወዲያውኑ የሚከተሉትን ያሳውቃል፦

- የተጠቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች
- የአጥቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወይም አጥቂ ተብዬውን የትምህርት ቤት ሠራተኛ ከሆነ
- የደህንነትና ጥበቃ ቢሮ

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወዲያውኑ የደረሰውን ክስ በተመለከተ ምርመራ ያካሂዳል።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የትምህርት ቤት ግልጋሎቶች ሹምን ሊያማክር ይችላል ሆኖም ስለ ተጠቂ ተብዬው ወይም አጥቂ ተብዬው ምንም ዓይነት መለያ መረጃ አያካፍልም።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የተጠቂ ተብዬውና የአጥቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ሲያሳውቅ በ Massachusetts Student Record (ማሳቹሴትስ የተማሪ መዝገብ) ደንቦች 603 C.M.R. 23.00 እና በ Federal Family Educational Rights and Privacy Act (ፌዴራል የቤተሰብ ትምህርት መብቶችና ምስጢራዊ ሕግ) 34 C.F.R. Part 99 ደንቦች 603 C.M.R. 49.07 ውስጥ በተዘረዘረው መሠረት በምስጢር የመያዝ መስፈርቶችን ተከትሎ መሆን አለበት። በተለይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከተጠቂ ተብዬው ወይም ከአጥቂ ተብዬው የተማሪ መዝገብ ውስጥ ምንም ዓይነት መረጃ አሳልፎ መስጠት አይችልም፣ መረጃው ስለ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ልጅ ካልሆነ በስተቀር። አንድ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ማስፈራራት መከሰቱን ወይም የአጸፋ ምላሽ ድርጊት መከሰቱን ለአካባቢው ሕግ አስከባሪ ድርጅት በ603 C.M.R. 49.06 መሠረት የተማሪውን ወይም የለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ፈቃድ ሳይጠይቅ ሊያሳውቅ ይችላል፣ ሆኖም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ጋር ሲነጋገር የዒላማዎችን፣ የምስክር ተማሪዎችንና የአጥቂዎችን ማንነት ሁኔታው እስከሚፈቅደው ድረስ ሳያሳውቅ መሆን አለበት። በተጨማሪ አጥቂው የትምህርት ቤት ሠራተኛ ከሆነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተገቢውን የቅጣት እርምጃ ሊወስድ ይችላል፣ ማባረርን ጨምሮ። በተጨማሪም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪው ወይም ሌሎች ግለሰቦች ለጤናቸው ወይም ለደህንነታቸው አስጊ

ሁኔታ አለ ብሎ ካመነ ከሕግ አስከባሪ ድርጅት ሌላ ለሚመለከታቸው ግለሰቦች ስለ ተጠቂው ወይም ስለ አጥቂው ከተማሪ መዝገቡ ውስጥ መረጃ ሊያካፍል ይችላል፣ በ603 C.M.R. 23.07(4)(e) እና 34 C.F.R. 99.13(a)(10) እና 99.36 መሠረት መረጃውን ማወቅ የተማሪውን ወይም የሌሎች ግለሰቦችን ጤንነት ወይም ደህንነት ይጠብቃል ተብሎ ከታመነ። በዚህ በመጨረሻ በተጠቀሰው ዓይነት ሁኔታ ላይ መረጃ የሚተላለፈው ድንገተኛ ሁኔታው በሚካሄድበት የጊዜ ርዝመት ብቻ ሲሆን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የተላለፈውን መረጃና ለጤና ወይም ለደህንነት አስጊ ሁኔታ ነው ብሎ የደመደመበትን ምክንያቶች መመዝገብ አለበት።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ *የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ሕድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላ* እና *የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲ* ቅጂ ለሚመለከታቸው ሁሉ ክስ አቅራቢውን፣ ተጠቂ ተብዬ ተማሪውን፣ የተጠቂ ተብዬው ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን፣ አጥቂ ተብዬው ተማሪ ከሆነ አጥቂ ተብዬውንና የአጥቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ጨምሮ ይሰጣል።

<u>የክስ ምርመራ</u>

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የማስፈራራት ክስ ወይም ማስፈራራትን በመጠቀም የበቀል ክስ፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ ስለሰጠ የበቀል ክስ ወይም የማስፈራራት ምስክር ሆኖ የሚታመን መረጃ ያለው ሰው ላይ የበቀል ክስ ሲደርሰው፣ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ክሱን ትክክልና ፈጣን በሆነ መንገድ ይመረምራል። ምርመራው የሚካሄደው ሁኔታዎቹ እስከሚፈቅዱት ድረስ ማንነትን በምስጢር ይዞና ማስፈራራትን የሚጠቁም ሰው፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ የሰጠ ሰው ወይም የማስፈራራት ምስክር ሆኖ የሚታመን መረጃ ያለው ሰው ማስፈራራት ወይም በቀል እንዳይደርስበት በመጠበቅ ነው።

ምርመራው ከተማሪው፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች፣ ክሱን ካስገባው ሠራተኛ ወይም የማህበረሰብ አባል፣ የማስፈራራት ወይም የበቀል ተጠቂ ተብዬው ተማሪ፣ ማስፈራራቱን ወይም በቀሉን ፈጽሟል ከተባለው ተማሪ/ዎች ወይም ሠራተኛ/ዎች፣ ከክስተቱ ምስክሮች፣ ወይም ሌሎች ሰዎች ጋር እንደ መምሪያው ውሳኔ ቃለ መጠይቅ ሊያካትት ይችላል። ማስፈራራት ወይም አጸፋ መልስ ተከስቷል ብሎ ከወሰነ በኋላ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የተጠቂውንና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና አጥቂው ተማሪ ከሆነ የአጥቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወዲያውኑ ይህንኑ ውሳኔና ምላሽ መስጫ ሂደቶችን ያሳውቃል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ምርመራው ከመካሄዱ በፊት ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን አስቀድሞ የሚገናኝበት አንዳንድ ሁኔታ ሊኖር ይችላል። ማስታወቂያው የሚሰጠው 603 C.M.R. 49.00 ላይ ባሉት ስቴት ደንቦች መሠረት ይሆናል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የአጥቂውና የተጠቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በሚያሳውቅበት ጊዜ በ Massachusetts Student Record (የማሳቹሴትስ የተማሪ መዝገብ) ደንቦች የምስጢራዊነት መስፈርቶች 603 C.M.R. 23.00 መሠረትና በ Federal Family Educational Rights and Privacy Act (ፌዴራል የቤተሰብ ትምህርት መብቶችና ምስጢራዊ ሕግ) 34 C.F.R. Part 99 በ 603 C.M.R. 49.07 ውስጥ የተጠቀሰውን ተከትሎ መሆን አለበት። በተለይም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከተጠቂ ተብዬው ወይም ከአጥቂ ተብዬው የተማሪ መዝገብ ውስጥ ምንም ዓይነት መረጃ አሳልፎ መስጠት አይችልም፣ መረጃው ስለ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ልጅ ካልሆነ በስተቀር። አንድ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ማስፈራራት መከሰቱን ወይም የአጸፋ ምላሽ ድርጊት መከሰቱን ለአካባቢው ሕግ አስከባሪ ድርጅት በ603 C.M.R. 49.06 መሠረት የተማሪውን ወይም የለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ፈቃድ ሳይጠይቅ ሊያሳውቅ ይችላል፣ ሆኖም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ጋር ሲነጋገር የዒላማዎችን፣ የምስክር ተማሪዎችንና የአጥቂዎችን ማንነት ሁኔታው እስከሚፈቅደው ድረስ ሳያሳውቅ መሆን አለበት። በተጨማሪም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪው ወይም ሌሎች ግለሰቦች ለጤናቸው ወይም ለደህንነታቸው አስጊ ሁኔታ አለ ብሎ ካመነ ከሕግ አስከባሪ ድርጅት ሌላ ለሚመለከታቸው ግለሰቦች ስለ ተጠቂው ወይም ስለ አጥቂው ከተማሪ መዝገቡ ውስጥ መረጃ ሊያካፍል ይችላል፣ በ603 C.M.R.

23.07(4)(e) እና 34 C.F.R. 99.13(a)(10) እና 99.36 መሠረት መረጃውን ማወቅ የተማሪውን ወይም የሌሎች ግለሰቦችን ጤንነት ወይም ደህንነት ይጠብቃል ተብሎ ከታመነ። በዚህ በመጨረሻ በተጠቀሰው ዓይነት ሁኔታ ላይ መረጃ የሚተላለፈው ድንገተኛ ሁኔታው በሚካሄድበት የጊዜ ርዝመት ብቻ ሲሆን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የተላለፈውን መረጃና ለጤና ወይም ለደህንነት አስጊ ሁኔታ ነው ብሎ የደመደመበትን ምክንያቶች መመዝገብ አለበት። በተጨማሪም ይህ ተከስቷል ከተባለ በስቴት ሕግ መሠረት የተጠቂው/ዎቹ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ስለ ምርመራው ውጤትና ሌላ ማስፈራራት ወይም በቀል እንዳይከሰት ስለሚወሰዱ ስለ ማናቸውም እርምጃዎች ማስታወቂያ ይሰጣቸዋል።

በተጨማሪም በስቴት ሕጉና በበኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶችና በኬምፐሪጅ ፖሊስ መምሪያ መካከል ባለው የመግባቢያ ውል መሠረት ማስፈራራት ወይም በቀል ተከስቷል ተብሎ ከተደመደመ የከፍተኛ ደረጃት ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር ጋር አብሮ በመተባበር የሚከተሉትን ያደርጋል፡-

- ከተደመደመ የከፍተኛ ደረጃት ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ አጥቂው ላይ የወንጀል ክስ ይቀርብበታል ብሎ ካሰበ ወይም ለተማሪው ወይም ለሎች ግለሰቦች ጤና ወይም ደህንነት አስጊ ክስተት ሊኖር ይችላል ብሎ ካመነ የትምህርት ቤት ግልጋሎቶች ሹምን ማሳወቅ
- በዚህ መመሪያ መሠረት ተገቢውን የቅጣት እርምጃ መውሰድ
- አጥቂው/ዎቹ ተማሪ ከሆነ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ማሳወቅ ወይም አጥቂው ሠራተኛ ከሆነ እራሱን ማሳወቅ
- የተጠቂውን/ዎቹን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በስቴትና ፌዴራል ሕግና ደንቦች መሠረት ማሳወቅ፣ ሌላ ማስፈራራትና በቀል እንዳይደርስ የተወሰድውን እርምጃ ማሳወቅ።

በተጨማሪም የማስፈራራት ወይም የበቀል ክስተቱ የሚመለከታቸው ተማሪዎች የተለያየ የትምህርት ቤት አውራጃ፣ ቻርተር ትምህርት ቤት፣ የመንግሥት ያልሆነ ትምህርት ቤት፣ ፈቃድ ያለው የግል ትምህርት ቤት፣ የመኖሪያ ቤት ውስጥ ትምህርት ቤት ወይም የትብብር ትምህርት ቤት ውስጥ ከሆነ የሚሄዱት በመጀመሪያ ስለ ማስፈራራቱ ወይም ስለ በቀሉ መረጃ የደረሰው የትምህርት ቤት አውራጃ ወይም ትምህርት ቤት በስቴትና በፌዴራል ሕግ መሠረት የሌላውን ትምህርት ቤት አውራጃ ወይም የሌላውን ትምህርት ቤት አስተዳዳሪ ተገናኝቶ አሳውቆት ሁለቱም ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ተወካዩ የማስፈራራት ወይም የአጸፋ ምላሽ ማስታወቂያ ከደረሰው ከማንኛውም ጊዜ በኋላ፣ ከምርመራውም በኋላ ቢሆን፣ ተጠቂው ላይ ወንጀላዊ ክስ ይመሰረትበታል ብሎ ካመነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተሩ ጋር አብሮ በመሆን የአካባቢውን ሕግ አስከባሪ ድርጅት ያሳውቃሉ። ማስታወቂያው የሚሰጠው 603 C.M.R. 49.00 ሥር ባሉት መስፈርቶችና በኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶችና በኬምፐሪጅ ፖሊስ መምሪያ መካከል ባለው የመግባቢያ ውል መሠረት ነው። በተጨማሪም የማስፈራራት ወይም የበቀል ክስተቱ የተካሄደው በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሆነና አንዱ ተማሪ ዕድሜው ከ21 ዓመት በታች ሆኖ ድሮ እንጂ አሁን የትምህርት ቤት አውራጃ፣ ቻርተር ትምህርት ቤት፣ የመንግሥት ያልሆነ ትምህርት ቤት፣ ፈቃድ ያለው የግል ትምህርት ቤት፣ የመኖሪያ ቤት ውስጥ ትምህርት ቤት ወይም የትብብር ትምህርት ቤት ውስጥ ያልተመዘገበ ተማሪ ከሆነ ስለ ማስፈራራቱ ወይም ስለ በቀሉ የተነገረው የትምህርት ቤት አውራጃ ወይም ትምህርት ቤት በስቴትና በፌዴራል ሕግና ደንቦች መሠረት ሕግ አስከባሪዎችን መገናኘት አለበት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ይህንን ውሳኔ ሲያደርግ በዋናው ዕቅድ መሠረት፣ በሚመለከታቸው የትምህርት ቤት አውራጃ ፖሊሲዎችና ሂደቶች መሠረት እንዲሁም በኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶችና በኬምፐሪጅ ፖሊስ መምሪያ መካከል ባለው የመግባቢያ ውል መሠረት ከትምህርት ቤት ግልጋሎቶች ሹምና ከሌሎች ግለሰቦች ጋር ተማክሮ ነው።

<u>ለማስፈራራት ክስተት የቅጣት እርምጃ/ምላሾች</u>

ቅጣትን በተመለከተ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ያለው ዓላማ የማህበረሰቡ ግለሰቦች እርስ በርስ ሲጎዳዱ መላ ማህበረሰቡ ላይ የደረሰውን ጉዳት ማስተካከል የሚችሉበትን የመማሪያ ገበታ መፍጠር ነው። ማስፈራራት ወይም ሌላ አግባብ የሌለው ባሕርይ ተከስቷል ተብሎ ከተወሰነ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ለሁኔታው አግባብ ያለው እርምጃ ይወስዳል። የቅጣት እርምጃው ኃላፊነት መውሰድንና የትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ላይ የደረሰውን ጉዳት መጠገንን አስታርቆ ትክክለኛውን ባሕርይ ያስተምራል። እንዳግባብነቱ መልሶ ገንቢ መንፈስ በመጠቀም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ አንድ ተማሪ ማስፈራራት እንዳይደርስበት፣ ማስፈራራትን ስለጠቆመ በቀል እንዳይደርስበት፣ የማስፈራራት ምርመራ ሂደት ላይ መረጃ ስለሰጠ በቀል እንዳይደርስበት ወይም የማስፈራራት ምስክር ሆኖ የሚታመን መረጃ ስላለው በቀል እንዳይደርስበት አግባብ ያላቸው የመከላከያ ስልቶች በሥራ ላይ ያውላል።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ አንድ የማስፈራራትን ወይም የበቀልን ክስ ሙሉ በሙሉ ከመመርመሩ በፊት፣ አስፈላጊ ከሆነ የተጠቂ ተብዬው ደህንነት አደጋ ላይ መሆኑን ገምግሞ ሰላም ማምጣት እና/ወይም ተጠቂ ተብዬው ሌላ ነገር እንዳይደርስበት መከላከል ካለበት እርምጃ ይወስዳል። ደህንነትን ለመጠበቅ ከሚደረጉት ነግሮች ውስጥ የሚከተሉት የተወሰኑት ናቸው፦ የግል ደህንነት ዕቅድ መፍጠር፣ በክፍል ውስጥ፣ ምሳ ሰዓት ላይ ወይም አውቶቡስ ላይ ተጠቂው እና/ወይም አጥቂው የሚቀመጡባቸውን ቦታዎች አስቀድሞ መለየት፣ ተጠቂው ችግር ቢያጋጥመው የሚሄድበት "የደህንነት ሰው" መለየት፣ የአጥቂውን የጊዜ ሰሌዳና ተጠቂውን ማግኘት የሚችልበትን ሁኔታ መቀየር። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ በምርመራው ወቅትና ከዛም ባሻገር ደህንነትን ለመጠበቅ አስፈላጊ እርምጃዎች ካሉ እነሱን እርምጃዎች ይወስዳል።

አግባብ ያለው ባሕርይን ማስተማሪያ የተለያዩ አማራጮች አሉ፦ የግል ችሎታ ማጎልበቻ ክፍሎች፣ መልሶ አዳሽ አሠራሮችን ማሳየትና መጠቀም፣ ተማሪዎችን በግል ወይም በቡድን ተያያዥ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከአማካሪዎች እና ከሌሎች ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ጋር እየተመካከሩ ማሳተፍ፣ ተማሪዎች አዎንታዊ በሆነ ማህበራዊ መንገድ ግቦቻቸውን እንዴት ሊመቱ እንደሚችሉ መረዳት እንዲችሉ የተለያዩ ትምህርታዊ እና ትምህርታዊ ያልሆኑ የባሕርይ ዳጋፎች በሥራ ላይ ማዋል፣ ማስፈራራትን ማስወገጃ መንገዶች ለማጠናከርና ማህበራዊ ስልቶችን ማዳበሪያ እንቅስቃሴዎች በቤት ውስጥ የመሥራት ድጋፍ ለማግኘት ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር መገናኘት፣ የተለዩ ማህበራዊ ችሎታዎች ለማጎልበት የባሕርይ ዕቅዶች መጀመር።

ማስፈራራት ውስጥ ተሳትፈው የተገኙ ተማሪዎች ላይ ከሚወሰዱት እርምጃዎች የሚከተሉትም ሊካተቱ ይችላሉ፦ አጥቂው ባሕርዩን እንዲያሻሽል ከአንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ጋር አብሮ መሥራት፣ ለተማሪውና ለሚመለከታቸው የቤተሰቡ አባላት የአማካሪ ማየት ትእዛዝ ወይም የድጋፍ አገልግሎቶች ወይም የሕክምና እርዳታ፣ እስከ ፍርድ ቤት ሊያደርስ የሚችል ቅጣት ለተማሪው፣ ወይም በዚህ መመሪያ መሠረት ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ቅጣት ማለትም ጊዜያዊ ማስወጣትን፣ ማባረርን እና/ወይም ፍርድ ቤት መሄድን ጨምሮ።

ማስፈራራት ውስጥ ተሳትፈው የተገኙ ተማሪዎች በሙሉ በቀል የተከለከለ እንደሆነና የበቀል ድርጊቶች ቅጣት እንደሚያስከትሉ ይነገራቸዋል።

ተገቢ ያልሆነ ምግባር ተከስቷል ተብሎ ከተገመገመ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ምግባሩን ለማስወገድ ወዲያውኑ እርምጃ ይወስድና እንዳስፈላጊነቱ ማረሚያ እንዲደረግ ያደርጋል፣ ይህም ማለት አጥቂው ባሕርዩን እንዲያሻሽል ከአንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ጋር አብሮ መሥራት፣ ለተማሪውና ለሚመለከታቸው የቤተሰቡ አባላት የአማካሪ ማየት ትእዛዝ ወይም የድጋፍ አገልግሎቶች ወይም የሕክምና እርዳታ እና/ወይም ቅጣት እንዳግባብነቱ ማስወጣትን፣ ማባረርን እና/ወይም ፍርድ ቤት መሄድን ጨምሮ። በተጨማሪም ማስፈራራት ወይም በቀል ተከስቷል ተብሎ ከተደመደመ፣ በስቴቱ ሕግ መሠረት የከፍተኛ ደረጃት ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር ጋር አብሮ በመተባበር የሚከተሉትን ያደርጋል፦ (1) የከፍተኛ ደረጃት ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ አጥቂው ላይ የወንጀል ክስ ይቀርብበታል ብሎ ካሰበ ያካባቢውን ሕግ አስከባሪ ድርጅት ማሳወቅ፣ (2) ተገቢውን የቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ (3) የአጥቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ማሳወቅ፣ እና (4) የተጠቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች

ማሳወቅና የስቴቱና የፌዴራል ሕግ እስከሚፈቅደው ድረስ ተጨማሪ ማስፈራራት ወይም በቀል እንዳይከሰት የተወሰደውን እርምጃ ማሳወቅ። ከዚህም በላይ፣ አንድ ተማሪ አውቆ የውሸት የማስፈራራት ክስ ወይም የበቀል ክስ እንዳቀረበ ከታወቀ በዚህ መመሪያ ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ቅጣት ይደርስበታል።

<u>ለዒላማውና ለሌሎች ደህንነትን ማጠናከር</u>

የማስፈራራት ዒላም ለሆነው ተማሪ ደህንነትን ዳግም ለማምጣትና ዒላማው ምን ዓይነት የደህንነት ጥበቃ እንደሚያስፈልገው ለመገምገም ከተማሪው፣ የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ከተገቢዎቹ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ጋር (ማለትም ከትምህርት ቤት ተቆጣጣሪ፣ ከከፍተኛ ደረጃ ዋን ኃላፊ፣ ከረዳት ተቆጣጣሪ፣ ከተማሪዎች ጉዳይ ዋና ኃላፊ፣ ከደህንነት ባለሙያ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ግሊጋሎቶች ሹም ጋር) ስብሰባ ይደረጋል። የዚህ ስብሰባ ዓላማ ለተማሪው የደህንነት ጥበቃ የሚሆን ዕቅድ ጉልበታና ሥራ ላይ መዋልንና ምንም ዓይነት ችግሮች ቢመጡ ተማሪው ሊነግረው የሚችለው ሠራተኛ ማን እንደሚሆን ለመወያየት ነው። የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች እንዳስፈላጊነቱ አማካሪ ማየትን፣ የድጋፍ አገልግሎቶችን ወይም ሌሎች የሕክምና እርዳታዎችን ተማሪው እና የሚመለከታቸው የቤተሰብ አባላት እንዲያገኙ ሐሳብ ሊሰጥ ይችላል።

ማገሚያው እና/ወይም የቅጣት እርምጃው በተወሰነ አግባብ ባለው ጊዜ ውስጥ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ ዒላማውን ይገናኝና የተከለከለው ምግባር ዳግም መከሰቱንና ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ያስፈልጉ እንደሆነ ይጠይቃል። የሚያስፈልግ ከሆነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ተወካዩ ከተገቢው የትምህርት ቤት ሠራተኛ ጋር አብሮ ሆኖ ወዲያውኑ ሥራ ላይ ያውላቸዋል።

ማገጃ የፍርድ ቤት ትእዛዝ ካለ፣ የስብሰባው አንዱ ዓላማ የማገጃ ትእዛዙን ለመቃኘትና የማገቻ ትእዛዝ ጥሰት ቢከሰት የማሳወቂያ ሂደቶቹን ለማወቅ ነው። የማገጃ ትእዛዙ አንድ ተማሪ ወይም ሠራተኛ ላይ ከሆነ፣ ከዛ ግለሰብ ጋር ሌላ ስብሰባ ለብቻው ተደርጎ የማገጃ ትእዛዙን አብሮ ይቃኝና፣ ትእዛዙ ቢጣስ የሚከተሉት ውጤቶች ምን እንደሆኑ ውይይት ይደረጋል።

<u>የውሸት ክስ/በቀል</u>

አንድ ተማሪ አውቆ የውሸት ማስፈራራት ወይም የውሸት በቀል ክስ እንዳደረገ ከተደመደመ በዚህ መመሪያ ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ቅጣት ይደርስበታል።

ተማሪዎች ሁሉ በሕግ ሥር ያለው ሁኔታቸው ምንም ዓይነት ቢሆን አንድ ዓይነት ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

<u>በትምህርት ቤት ላይ የተመሠረቱ እርምጃዎች ክለሳ</u>

የማስፈራራት ክሱን ያቀረበው ሰው፣ የማስፈራራት ተጠቂ ተብዬው እና/ወይም የማስፈራራት ተጠቂ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ጋር ተባብረው ከዚህ በላይ የተገለጹትን ኦፊሲዬላዊ ያልሆኑ መንገዶችን በቅንነት ተጠቅመው ለችግራቸው መፍትሄ ማግኘት ካልቻሉ በጽሑፍ የቀረበ አቤቱታ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለዋና ሥራ አስኪያጁ ሊላክ ይችላል። በጽሑፍ የሚቀርበው አቤቱታ ተጨባጭ ጉዳዮቹን ባጭሩ መግለጽና የሚፈለገው መፍትሄ ምን እንደሆነ መያዝ አለበት።

ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ በጽሑፍ የቀረበው አቤቱታ በደረሰው በሰባት (7) ቀን ውስጥ ስለ ጉዳዩ ለመወያየት ቀንና ሰዓት ወስኖ ማስታወቂያ በፖስታ መላክ አለበት። ከስብሰባው በኋላ ዋና ተቆጣጣሪው ማስፈራራት ወይም ሌላ አግባብ የሌለው ምግባር ተከስቶ እንደሆነ፣ ማስፈራራቱ ወይም ሌላው አግባብ የሌለው ምግባር ዳግም እንዳይከሰት እስካሁን የተወሰደው እርምጃ ምን እንደሆነና ተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ያስፈልጉ እንደሆነ ይገመግማል። ስብሰባው በተካሄደ በአምስት (5) ቀን ውስጥ እነዚህን

ጉዳዮችና ሌሎች ማናቸውም የትምህርት ቤት አውራጃው የሚወስዳቸው እርምጃዎች ካሉ እነሱን የያዘ ደብዳቤ ይላካል።

የማስፈራራት ክስ ያቀረበው ሰው፣ ዒላማ ተብዬው እና/ወይም የዒላማ ተብዬው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከዋና ተቆጣጣሪው ወይም ከተወካዩ ጋር ከተሰበሰቡ በኋላ ለጉዳዩ መፍትሄ ማግኘት ካልቻሉ የግምገማ ጥያቄ የትምህርት ቤት ኮሚቴው ጋር መላክ ይቻላል። የትምህርት ቤት ኮሚቴው በራሱ ፈቃድ ምስክሮች የሚሉትን ማዳመጥ፣ ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል እና የትምህርት ቤቱን ግኝቶችና ሐሳቦች መቃኘት እንዲሁም የዋና ተቆጣጣሪውን ወይም የተወካዩን ግኝቶችና ሐሳቦች መገምገም ይችላል። የትምህርት ቤት ኮሚቴው ግምገማውን ባደረገ በአምስት (5) ቀን ውስጥ የጽሑፍ ውሳኔ ያስተላልፋል፣ ይህም የዋና ተቆጣጣሪውን ግኝቶችና ሐሳቦች የሚደግፍ፣ የሚለውጥ ወይም የሚያሻሽልና ለተጠቀሱት ጉዳዮች መፍትሄ የሚሆኑ እርምጃዎች የትምህርት ቤት አውራጃው የሚወስድ ከሆነ እነሱንም ያካትታል።

<u>ሌሎች የአቤቱታ ማቅረቢያ ሂደቶች</u>

በዚህ ክፍል ውስጥ ከላይና በጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ ውስጥ የተዘረዘሩት የሂደቶች አቅራቦቶች አንድ ተማሪን ማንኛውም ዓይነት የአድሎ ወይም በሕግ በተጠበቁት ልዩ ምልክቶች ማለትም በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ አቤቱታ ካለው የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶችን "ጸረ-አድሎ ፖሊሲና ጾታዊ ጉትጎታ ክልከላ ፖሊሲ" ውስጥ ያለውን የአቤቱታ ሂደት ከመጠቀም አያግዱትም። በተጨማሪም በዚህ *መመሪያ* መሠረት የሙብት መንፈግን በተመለከተ ያለ አቤቱታን ለመፍታት እዚህ ክፍል ላይ ያሉት አቅራቦቶች *የመመሪያው* ክፍል 23.0 ላይ ያለውን የአቤቱታ ሂደት ከመከተል አያግዱትም።

<u>ከሌሎች ሕጎች ጋር ያለው ግንኙነት</u>

በፌዴራልና በስቴት ሕጎችና ደንቦች መሠረት እንዲሁም በትምህርት ቤት አውራጃው ፖሊሲዎች መሠረት ማንም ሰው በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ምክንያት ማንኛውም ከተማ ውስጥ ያለ የመንግሥት ትምህርት ቤት ውስጥ ከመግባት ወይም ትምህርት ቤቱ ውስጥ ያሉትን ሙብቶች፣ ጥቅሞችና ትምህርቶች ከማግኘት አድሎ ሊደርስበት አይችልም። አንድ ሰው በአካባቢው፣ በስቴት ወይም በፌዴራል ሕግ ከተጠበቁት ዘርፎች ውስጥ የአንዱ አባል ስለሆነ አድሎ ወይም ጉትጎታ ቢደርስበት አንድ ትምህርት ቤትን ወይም አንድ የትምህርት ቤት አውራጃን አድሎውን ለማስተካከል እርምጃ ከመውሰድ በዚህ ክፍል ውስጥም ሆነ በጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ ውስጥ የሚያግዱት ነገር የለም። በተጨማሪም በዚህ ክፍል ውስጥም ሆነ በጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ ውስጥ የአንድ ትምህርት ቤትን ወይም የትምህርት ቤት አውራጃን በ M.G.L.c. 71፣ ክፍሎች 37H እና 37H ½ እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው ሕጎች ወይም የአካባቢው ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት አውራጃ ፖሊሲዎች መሠረት አስቃቂ፣ ጎጂ ወይም ረብሻ የተሞላ ባሕርይ ቢኖር፣ ባሕርዩ በኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-አስፈራሪ ተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ ውስጥ ተጠቅሶ ቢሆንም ባይሆንም፣ የቅጣት እርምጃ መውሰጃ ሥልጣናቸውን የሚወስን ነገር የለም።

## 5.13 <u>የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ፖሊሲ</u>

የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃትን በጭራሽ የሚቀበለው ነገር አይደለም። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት፣ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ከፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ነጻ የሆነ አካባቢ ለማጎልበት ቃል ገብቷል። ስለዚህም የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የጎረምሶች ፍቅር

ጓኝነት ጥቃት ግንዛቤን ከፍ ለማድረግ ይጥራል፣ ለተጠቂዎችም ሆነ ለእንደዚህ ዓይነት ጥቃት ምስክር ለሆኑ ልጆችም የሚሰጠውን እርዳታ ከፍ ማድረግ ይሻል።

በማንኛውም ቦታ የሚከሰት የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ሕገወጥ ሲሆን በትምህርት ቤት ውስጥ ለሚከሰት የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ምንም ዓይነት ትእግስት አይኖርም። በተጨማሪም የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃት አቤቱታ ያቀረበ ግለሰብ ላይ ወይም የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ምርመራ ላይ የተባበረ ግለሰብ ላይ የሚደረግ አጸፋ ምላሽ በትዕግስት የምናሳልፈው አይሆንም። የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃትና የበቀል አቤቱታና ማስታወቂያ ሲደርሰው ወዲያውኑ መልስ ይሰጥና አስፈላጊውን የቅጣት እርምጃ ይወስዳል።

***የቤት ውስጥ ጥቃት/የርስ በርስ ጥቃት፦*** የቤት ውስጥ ጥቃት ማለት በሁለት አብረው በሚኖሩ ሰዎች መካከል አንዱ ሌላውን የማስገደድ ባሕርይ በተደጋጋሚ ሲከሰት ነው፣ ማለትም አንዱ ሌላውን በማስፈራራት ወይም ከሚከተሉት መንገዶች አንዱን ተጠቅሞ ለመቆጣጠር ሲሞክር ነው፦ በአካል፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት፣ በቃል፣ በገንዘብ፣ በስነ ልቦና ጥቃት እና/ወይም በቴክኖሎጂ (ማለትም የኢንተርኔት ማስፈራራት)።

የቤት ውስጥ ጥቃት በአገር ውስጥ ሁሉንም ማህበረሰብ፣ ዘር፣ ባህል ወይም ልምድ ሳይል ሁሉንም የሚመለከት ጉዳይ ነው። በማንኛውም ዕድሜ፣ ገቢ፣ ኃይማኖት፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ጾታ እና የትምህርት ደረጃ ያሉ ሰዎች የቤት ውስጥ ጥቃት፡ሊደርስባቸው ይችላል።

***የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝንት ጥቃት፦*** የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት (ወይም የግንኙነት ጭቆና) ማለት ከልክ ባለፈ መንገድ የፍቅር ጓደኛን የመቆጣጠር ባሕርይ ነው። የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት በብዙ መልክ ሊገለጽ ይችላል፦ የአእምሮ/የስሜት ጭቆና፣ የአካል ጭቆናና የግብረ ሥጋ ግንኙነት ጭቆና እና/ወይም ቴክኖሎጂ መጠቀምን (ማለትም በኢንተርኔት ማስፍራራት) ያካትታል። አንድ ሰው የአካል ጭቆና ሳይደርስበት የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ሊደርስበት ይችላል። መደበኛ የፍቅር ጓደኝነት ውስጥም ዘለቄታዊ ግንኙነት ውስጥም ሊከሰት ይችላል።

***የልጅ ምስክር/ለቤት ውስጥ ጥቃት መጋለጥ፦*** ጥቃትን ማየት የአንድ ልጅን ሕይወት ገጽታዎች በሙሉ፣ እድገትና መጎልበት ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል። መጋለጥ ማለት ጥቃቱን ማየት ወይም መስማት፣ የጥቃቱን ውጤቶች ማየት (የወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ቁስል ወይም የተሰበረ የቤት ዕቃ ወዘተ.) እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ከጥቃት እከላከላለሁ ሲል መጎዳትን ሊያካትት ይችላል።

***የቤተሰብ ጥቃት፦*** የቤተሰብ ጥቃት ማለት ሰፋ ያለ ትርጉም ሲኖረው የልጅ ጭቆናን፣ የአዛውንት ጭቆናን እና ሌሎች በቤተሰቦች መካከል የሚከሰቱ አስከፊ ድርጊቶችን ያካትታል።

***ተጠቂ/ተራፊ/ተደብዳቢ፦*** የተጎዳውን፣ የተጨቆነውን ወይም የጥቃት ዛቻ የደረሰበትን ሰው፣ አካላዊ ጉዳት ቢኖርም ባይኖርም፣ ለመግለጽ የሚጠቅሙ ተለዋዋጭ ቃሎች።

***ጨቋኝ/አጥቂ/ደብዳቢ፦*** ጭቆናውንና ጉዳት ያደረሰውን ሰው፣ አካላዊ ጉዳት ቢያስከትልም ባያስከትልም፣ ለመግለጽ የሚጠቅሙ ተለዋዋጭ ቃሎች።

በተጨማሪ እንደዚህ ዓይነቱ ምግባር እንደ ጉትጎታ ይቆጠራል፣ ይህም ከአድሎ ስለሚመደብ በፌዴራልና በስቴት ሕግ የተከለከለ ነው፣ እና/ወይም እንደዚህ ዓይነቱ ምግባር እንደ ማስፈራራት ተቆጥሮ ከኢንተርኔት ማስፈራራት ከተመደበ በስቴት ሕግ የተከለከለ ነው። የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ፣ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ጥቃት ፖሊሲና የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲ።

የጨቋኝ ባሕርይ ምልክቶች የሚከተሉትን ይይዛሉ፡- የተማሪው የፍቅር ጓደኛ ከሌሎች ጋር ለምን አወራ/አወራች ብሎ በጣም መቅናት፣ ሌላው ማድረግ ያለበትን ለመምራት መሞከር፣ አለመስማማት ሲኖር ከልክ በላይ ማጋነን፣ ሁልጊዜ የፍቅር ጓደኝነትን ለማቋረጥ ማስፈራራት፣ በአንደበት እራስን መቆጣጠር መሳን፣ የራስን ችግር ሌሎች ላይ ማላከክ፣ የፍቅር ጓደኛን በአካልም ሆነ በስሜት መጉዳት ወይም የኢንተርኔት ማስፈራራት ድርጊቶች።

የተጠቂ ምልክቶች የሚከተሉትን ይይዛሉ፡- በማይመስሉ ምክንያቶች ቀጠሮን ሁልጊዜ መሰረዝ፣ ሁልጊዜ የፍቅር ጓደኛን እንዳላስቆጣ ብሎ መጨነቅ፣ ለራስ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን መተው፣ የአካል ጉዳት ምልክቶች ማሳየት፡- ለምሳሌ ጠባሳዎች ወይም ቁስሎች፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ለማድረግ ተጽዕኖ ላይ መወደቅ ወይም ለግብረ ሥጋ ዓላማ ብቻ ለመጠቀም የመፈለግ ስሜት፣ በፈለገው/በፈለገችው ጊዜ ሁሉ እንዲገኝ/እንድትገኝ የሚፈልግ የፍቅር ጓደኛ እና ከቤተሰብና ከጓደኞች መገለል ወይም በኢንተርኔት ማስፈራራት እራስ ላይ ሲደርስ።

የፍቅር ጓደኝነት ጥቃትን ማሳወቂያ ሂደት

የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ተጠቂ ነኝ፣ የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ሊደርስብኝ ነው ብሎ የሚያምን ተማሪ ወይም የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዝ ያለው ግለሰብ ጉዳዩን ከሚከተሉት ግለሰቦች ለአንዱ ማሳወቅ ይችላል፡- (1) የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ (2) ረዳት ተቆጣጣሪ፣ (3) የተማሪ ጉዳዮች ኃላፊ፣ (4) አስተማሪ ወይም (5) የትምህርት ቤት ነርስ።

ማሳወቂያ የደረሰው ግለሰብ ወዲያውኑ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ማሳወቅ አለበት።

በተጨማሪም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ የጎረምሶች ፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ያስተዋለ ማንኛውም ሠራተኛ ወዲያውኑ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ማሳወቅ አለበት።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወዲያውኑ የሚከተለውን ማድረግ አለበት፡- (1) የተጠቂውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ማሳወቅ፣ እና (2) የደህንነትና ጥበቃ ቢሮን ማሳወቅ።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ለተማሪው እና/ወይም ለተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ኦፊሲዬላዊ ባልሆነ መንገድ መፍትሄ ማግኛ ሂድቶችንና ኦፊሲዬላዊ አቤቱታዎችን ማስገቢያ ሂደቶች የያዘውን የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላን እና የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲ ያሳያል፣ የቅጂ ጥያቄ በቀረበለትም ጊዜ ቅጂ ይሰጣል።

የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ክስ በሚደርስ ጊዜ፣ ሁኔታው የተከሰተው በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ፣ ከትምህርት ቤት ሲሄዱም ሆነ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡ ወይም የትምህርት ቤት ዝግጅት ቦታ ላይ፣ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ በፍርድ ቤት የታዘዘ ማገጃ ከተጣሰ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ወዲያውኑ ለሚመለከታቸው ባለሥልጣኖችን ተከሰተ ስለተባለው ጉዳይ ያሳውቃል። እንደዚህ ዓይነት ክስተትን ሲያሳውቁ <u>ሁኔታው በሚፈቅደው መጠን ሁሉ</u> ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ይሆናል።

የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃትን በተመለከተ የሶስተኛ አካል መረጃን በጥሞና መቀበል አስፈላጊ ነው። ባግባቡ ሥልጠና ያገኘ ሠራተኛ ስለተሰማው ጉዳይና ሊኖሩ ስለሚችሉ ችግሮች ለመወያየት ተማሪውን ቢያነጋግረው ይመረጣል። ጭቆና አለ ብሎ ተማሪው ካመነ አማካሪ የማየት፣ የድጋፍ ቡድኖችና የፖሊስ/የፍርድ ቤት እርዳታ የሚገኙበትን መንገድ ከማካፈል በተጨማሪ "የደህንነት ዕቅድ" ማጎልበት ይስፈልጋል።

በተጨማሪም ተከስቷል ተብሎ የሚጠረጠር ጭቆናና ከፍተኛ ቸልተኝነት ካለ የትምህርት ቤት ሠራተኞች በሕግና ደንቦች መሠረት ማሳወቅ እናደለባቸው ማስታወስ አለባቸው (ማሳወቂያ51A)። 51A አቤቱታዎችን ሲያስገቡ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች የልጅ ጭቆናና ከፍተኛ ቸልተኝነት ማሳወቂያ መመሪያዎችን ውስጥ ባለው መስፈርት መሠረት መሆን አለበት፣ እንዲሁም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊን ስለ ጭቆናውና ስለ ከፍተኛ ቸልተኝነቱ ማሳወቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪም የትምህርት ቤት ሠራተኞች ለፖሊስ ማሳወቅ ማስታወስ አለባቸው። ሠራተኞች የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊን ያሳውቃሉ፣ እሱ የደህንነትና ጥበቃ ሹሙን ያሳውቃል፣ እሱ ደግሞ ለፖሊስ የማሳወቅ ሂደቱን ያቀነባብራል። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያሳውቁ ሁኔታው እስከሚፈቅደው ድረስ የመረጃውን ምስጢራዊነት በጠበቀ መንገድ መሆን አለበት።

<u>የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዝ ሲሰጠው ትምህርት ቤቱ የሚከተላቸው ሂደቶች</u>

አንድ ተማሪ ሌላ ግለሰብ ላይ የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዝ ሲኖረውና የትእዛዙን ቅጂ ለትምህርት ቤቱ ሲሰጥ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከሠራተኛው ወይም ከተማሪውና ከተማሪው ወላጆች/አስዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ስብሰባ አድርጎ የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዙንና በውስጥ ያሉትን ዝርዝሮች መቃኘት አለበት።

ተጠቂው የሚያስፈልጉትንና የሚያሳስቡትን ነገሮች የሚያመቻች “የደህንነት ዕቅድ” መጎልበት አለበት፣ ይህም ተማሪው ወይም ሠራተኛው በትምህርት ቤት ወይም በትምህርት ቤት ዝግጅት ላይ ሳለ ችግር ቢፈጠር ወይም የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዙ ቢጣስ ተማሪው ሊያሳውቀው የሚገባው ሠራተኛን መለየትን ማካተት አለበት። የፍርድ ቤት ማገጃ ትእዛዙ ሌላ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባል ላይ ከሆነ፣ የፍርድ ቤት ማገጃውን ትእዛዝ ዝርዝሮችን፣ ከግለሰቡ የሚጠበቁ ነገሮችንና ትእዛዙ ቢጣስ ምን እንደሚደርስ ለመቃኘት ከዛ ግለሰብ ጋር ሌላ ስብሰባ ይደረጋል። “የደህንነት ዕቅዱ” ሥራ ላይ የሚውለው ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን የጉዳዩን ምስጢራዊነት በጠበቀ መንገድ ይሆናል።

<u>የቅጣት እርምጃ</u>

አግባብ የሌለው ምግባር ተከስቷል ተብሎ ከተገመገመ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች እንድሁኔታው ይህን እርምጃ ይወስዳል። እርምጃው ከአማካሪ ማየት እና/ወይም ቅጣት እስከ ሌጊዜው ከትምህርት ቤት ማስወጣት ወይም ማባረር ሊሆን ይችላል።

<u>ሌሎች መፍትሄዎች</u>

ትምህርት ቤት ውስጥ፣ ከትምህርት ቤት ወይም ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ወይም የትምህርት ቤት ዝግጅት ላይ የሚከሰትን የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ከማሳወቅ በተጨማሪ ከላይ በተጠቀሱት ሂደቶች መሠረት የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ደርሶብኛል ብለው የሚያምኑ ተማሪዎች የጉትጎታ እና/ወይም የማስፈራራት ክስ በኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላ ሂደት መሠረት እና/ወይም በኬምብሪጅ ትምህርት ቤቶች ጸረ-ማስፈራራት ፖሊሲ መሠረት ማስገባት ይችላሉ። በተጨማሪም ከትምህርት ቤት ውጪ እና/ወይም ከትምህርት ሰዓት ውጪ የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃት ተጠቂ ነኝ ብለው የሚያምኑ ተማሪዎች ክሱን ለፖሊስ ማሳወቅ ይችላሉ።

አደጋ ላይ ነኝ ብለው የሚያምኑ ተማሪዎች እራሳቸውን ከጉዳት ወይም ከዛቻ ለመከላከል ባካባቢው በሚገኘው ፍርድ ቤት ውስጥ ማመልከቻ አስገብተው የማገጃ ትእዛዝ መጠየቅ ይችላሉ።

## 6.0 ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት

6.1 ፍርድ ቤቶች አንዳንድ በሕገ መንግሥት ውስጥ የተጠቀሱ መብቶችን ለትምህርት ቤቶች እንዲሆኑ አድርገው ፍቹ በሰጧቸው መሠረት ተማሪዎች የነዚህ መብቶች ተካፋይ ናቸው። ተማሪዎች በቃል፣ በጽሑፍ፣ አንዳንድ እንደ ቁልፍ፣ አርማ፣ የክንድ ማሰሪያ በማድረግ ወይም በሌላ መንገድ ሐሳባቸውን የመግለጽ መብት አላቸው። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ የተወሰነ ዓይነት ሐሳብ ገለጻ በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ ድንገተኛና ከፍተኛ ረብሻ ያመጣል ብሎ ተጨባጭ ምክንያት ካለው ሐሳብ መግለጽ ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ ይችላል (ለምሳሌ ጸያፍ፣ ስም የሚያጠፋ፣ ዘረኝነትን የሚደግፍ፣ ዘማዊ ወይም ሌሎች የትምህርት ቤት ደንቦችን እንዲጥሱ የሚቀሰቅስ፣ ወዘተ.)።

6.2 ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥና በትምህርት ቤት ሕንጻ ውስጥ ማንኛውንም ዓይነት ህትመት የመያዝና የማሰራጨት መብት አላቸው፣ ጋዜጣን፣ ሜጋዚንንን፣ በራሪ ጽሑፍንና መጽሔቶችን ጨምሮ፣ ሆኖም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ የአንድ ህትመትን አንድ እትም በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ ድንገተኛና ከፍተኛ ረብሻ ያመጣል ብሎ ተጨባጭ ምክንያት ካለው የዛን ህትመት ስርጭት ሊከለክል ይችላል (ለምሳሌ ዘረኝነትን የሚደግፍ፣ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎችን የሚደግፍ፣ የአደንዛዥ እጽ መጠቀምን የሚያበረታታ ወዘተ.)።

6.3 የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ማንኛውም አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ህትመቶች፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚወጡ ህትመቶችን ጨምሮ ከመሰራጨታቸው በፊት ለፈቃድ እንዲገቡ ይጠይቃሉ። ሁሉም የተማሪ ህትመቶች ኃላፊነት የተሞላ ጋዜጠኝነት የሚጠበቁበትን ደንቦች ማሟላት አለባቸው። ይህ ማለት ስም አጥፊ መግለጫዎች፣ መሠረት አልባ ክሶችና ወቀሳዎች፣ ስድብ፣ የሰዎችን ስም ማጥፋት፣ ሐሰት መግለጫዎች፣ በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ጉትጎታ ወይም አድሎ፣ ጥላቻ፣ ጥቃት፣ የትምህርት ቤት ሕጎችና ደንቦች መጣስ፣ ወይም የትምህርት ሂደቱን የሚያቃውሱ ህትመቶች አይፈቀዱም።

በሐሳብ መግለጫ ነጻነት ስም ተማሪዎች በማንኛውም መልክ የገለጹት ሐሳብ የትምህርት ቤቱ ኦፊሲዬላዊ መግለጫ ሆኖ ሊወሰድ አይችልም። ማሰራጨቱ በተጀመረ ጊዜ አንድ ግልባጭ ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ካልተሰጠ በስተቀር የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ምንም ዓይነት ህትመት እንዳይሰራጭ ይከለክላል።

6.4 ተማሪዎች ህትመት የሚያሰራጩበትን ሰዓት፣ ቦታና የማሰራጫውን መንገድ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሊቆጣጠር ይችላል፣ ቁጥጥሩ እንደሚከተለው እስከሆነ ድረስ፦

ሀ. ለሁሉም የህትመት ዓይነት በአንድ ዓይነት መልኩ ሥራ ላይ ከዋለ፣

ለ. ረብሻ ይከሰታል ተብሎ ተጨባጭ ምክንያት ከሌለ የስርጭት ሰዓትና ቦታ አለመከልከል፣ ትምህርት ቤቱ ሕንጻ ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤቱ ውጪ፤

ሐ. ስርጭቱ ይተከለከለበትን ቦታዎችና ሰዓቶች በግልጽ የሚነግር፣ እና

መ. በደንቦቹ መሠረት የተሰራጨ ህትመትን ሰው የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብትን አለመንፈግ።

6.5 ማንኛውም ተማሪ ለባንዲራው ሰላምታ መስጠት ወይም ብሔራዊ የታማኝነት ቃል ኪዳንን የማለት ግዴታ የለበትም። መሳተፍ አልፈልግም የሚል ተማሪ በአክብሮት ዝም ብሎ መቆየት አለበት።

6.6 የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ አስቀድሞ ፈቃድ ሳይሰጥ ማስታወቂያ፣ ተለጣፊ ጽሑፍ ወይም መፈክር መስቀል አይቻልም።

6.7 በዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጠቀሱትን ማናቸውንም መብቶች የሚጥስ ማንኛውም ግለሰብ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ በክፍል 23.0 ላይ ባሉት አቅርቦቶች መሠረት አቤቱታ ሊቀርብበት

## 7.0 የመሰብሰብ ነጻነት

7.1 ተማሪዎች የሕገ መንግሥቱ ሙሉ የመሰብሰብ ነጻነት አላቸው። ተማሪዎች ሐሳባቸውንና አመለካከታቸውን ለመግለጽ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በነጻነትና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መሰብሰብ ይችላሉ። ተማሪዎች ያቀዱት ስብሰባ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ረዳት ተቆጣጣሪ አስቀድሞ ፈቃድ በሰጠበት ሰዓትና ቦታ ነው መካሄድ የሚችለው፣ ይህም ፈቃድ ያላግባብ ሊከለከል አይችልም።

7.2 ተማሪዎች ከውጪ ተናጋሪዎችን መጋበዝና በትምህርት ቤት ውስጥ ማዳመጥ ይችላሉ። የትምህርት ቤት ባለሥልጣናት አግባብ ባለው መንገድ የንግግሮችን ሰዓትና ቦታ ሊቆጣጠሩ ይችላሉ፣ እንዲሁም የጊዜ ግጭቶችን ለማስወገድና ለትምህርት ቤት ማህበረሰቡ ተገቢውን ጥበቃ ለማሰናዳት አስቀድሞ እንዲያሳውቋቸው ሊጠይቁ ይችላሉ። አስቀድሞ ፈቃድ ለማግኘት ተማሪዎች ከውጪ የምሚመጡ ተናጋሪዎችን ስም ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ለረዳት ተቆጣጣሪ የመስጠት ግዴታ አለባቸው። የተናጋሪው መምጣት የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ ረብሻ ይፈጥራል ተብሎ ከፍተኛ ተጨባጭ ምክንያት ከሌለ በስተቀር የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ረዳት ተቆጣጣሪው ፈቃዱን ይሰጣል።

7.3 በዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጠቀሱትን ማናቸውንም መብቶች የሚጥስ ማንኛውም ግለሰብ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ በክፍል 23.0 ላይ ባሉት አቅርቦቶች መሠረት አቤቱታ ሊቀርብበት ይችላል።

## 8.0 የትምህርት ቤት መገልገያዎችን መጠቀም

8.1 የትምህርት ቤት ባለሥልጣኖች አግባብ ባለው መንገድና ጸረ-አድሎ በሆነ መንገድ ተማሪዎች የትምህርት ቤት መገልገያዎችን ለመሰብሰብያና ህትመት ለማሰራጫ መዘጋጃ እንዲጠቀሙና በዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጠቀሱትን መብቶች መጠቀም እንዲችሉ መፍቀድ አለባቸው። የትምህርት ቤት ባለሥልጣኖች ተማሪዎች ለተጠቀሙት መገልገያና ለሌሎች ወጪዎች ወይም መገልገያዎችን ሲጠቀሙ ላበላሹት ነገርና ትምህርት ቤቱ ለማይከፍልበት ነገር አግባብ ባለው መልክ እንዲከፍሉ ሊጠይቁ ይችላሉ።

በዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጠቀሱትን ማናቸውንም መብቶች የሚጥስ ማንኛውም ግለሰብ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ በክፍል 23.0 ላይ ባሉት አቅርቦቶች መሠረት አቤቱታ ሊቀርብበት

## 9.0 ያለባበስ ደንብ

9.1 ተማሪዎች በዚህ ያለባበስ ደንብ መሠረትና በጾታ መለያቸው መሠረት መልበስ ይችላሉ። ተማሪዎች ጤናን፣ ደህንነትንና ንጽሕናን ባግባቡ በጠበቀ መንገድ እስከለበሱ ድረስና የትምህርት ሂደቱን እስካልረበሸ፣ አስጸያፊ እስካልሆነ እና/ወይም የራሳቸውን ወይም የሌሎችን ጤና፣ ደህንነትና ምቾት አደጋ ላይ እስካልጣለ ድረስ በመረጡት አለባበስና የጸጉር አሠራር እራሳቸውን የመግለጽ መብት አላቸው። እግሮቻቸው ሁልጊዜ በጫማ መሸፈን አለባቸው።

9.2 ተማሪዎች አጸያፊ፣ ሀፍረተ ቢስ ወይም ተራ መፈክሮች፣ አስተያየቶች ወይም ስዕል ያላቸው ልብሶች፣ ጌጣጌጥ እና/ወይም ቦርሳና ሌላ ማጌጫ መያዝ፣ እንዲሁም ሌሎችን በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ የሚሳደቡ፣ የሚዝቱ፣ የሚያዋርዱ ጽሑፎች፣ እና/ወይም አሎኮል መጠጥ፣ ሲጃራ ወይም ሕገወጥ፡ አደንዛዥ ዕጽ ማስታወቂያ ያለው ማድረግ ክልክል ነው።

9.3 ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት ከወገብ በላይ ሳይለብሱ፣ ያለ ሱሪ ወይም ያለ ጫማ መምጣት አይችሉም። በዚህ ፖሊስ መሠረት የለበሱ ተማሪዎች ከአለባበሳቸው ጋር የተያያዘ ምንም ዓይነት አጸፋ ምላሽ ከሠራተኞች ሊመጣባቸው አይገባም፣ አለባበሳቸው ከሰውነታቸው፣ ከዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታቸው ጋር ባይሄድም።

9.4 አንድ ተማሪ ለትምህርት ቤት የማይሆን ልብስ ለብሶ ከመጣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ይነገራቸውና ትምህርት ቤቱ ተማሪው ቀኑን ለብሶ የሚውለው ጊዜያዊ ልብስ ይሰጠዋል (ለምሳሌ ሹራብ ወይም ከትምህርት ቤቱ ሱቅ ቲሸርት)፣ ወይም ልብሱን ገልብጦ እንዲለብስ ይጠይቀዋል፣ ወይም ልብሱን ቀይሮ እንዲመጣ ወደቤት መልሶ ይልከዋል ወይም ቀኑን ለብሶት የሚውለው ልብስ ከክፍል ጓደኛው/ከጓደኛው እንዲዋስ ያደርጋል።

9.5 ደህንነት ጠባቂ ልብስን፣ የደህንነት መነጽርን ወይም ሌላ ልዩ መርሃ ግብሮች ውስጥ ለመሳተፍ አስፈላጊ የሆነ ደህንነት መጠበቂያ መሳሪያ ሲጠቀሙ ተማሪዎች የትምህርት ቤቱን ደንቦች ሁሉ እንዲከተሉ ይጠበቅባቸዋል።

9.6 የተማሪ አለባበስን በተመለከተ የሚካሄዱ ውይይቶች ሁለቱም ወገኖች እኩል ድምጽ ባላቸው ሁኔታ መካሄድ አለባቸው። እንደዚህ ዓይነት ውይይቶች በክፍሉ ፊት ወይም በሌሎች ተማሪዎች ፊት መከሰት የለባቸውም።

9.7 ይህ ፖሊሲ እኩልነትና አንድ ወጥ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋል እንዲችል ዋና ተቆጣጣሪው ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዋና ኃላፊ ይህን ፖሊሲ በተመለከተ *መመሪያ* ይሰጣቸዋል። ማንኛውም በዚህ ፖሊሲ ጥሰት ምክንያት የሚሰጥ ቅጣት በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ የሚሰጥ ሲሆን በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባሉት በሚመለከታቸው አቅራቦቶች መሠረት የሚሰጥ ይሆናል።

9.8 በዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጠቀሱትን ማናቸውንም መብቶች የሚጥስ ማንኛውም ግለሰብ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ በሚመለከታቸው አቅርቦቶች መሠረት አቤቱታ ሊቀርብበት ይችላል።

## 10.0 የኃይማኖት ነጻነት

10.1 ተማሪዎች ማንኛውም የኃይማኖት ዝግጅት ውስጥ ያለመሳተፍ ወይም ያለመሄድ መብት አላቸው።

10.2 በነዚህ ደንቦች ውስጥ ምንም ከኃይማኖት ጋር የተያያዙ ርእሶችን መወያየት ወይም ከመደበኛው የትምህርት ቤት ሥርዓት ውስጥ የኃይማኖት መዝሙር መጫወት የሚከለክል ነገር የለም፣ ሆኖም ማንኛውም የሚቃወም ተማሪ ላለመካፈል የመምረጥ መብት አለው።

## 11.0 የተማሪ ጋብቻና እርግዝና

11.1 እርጉዝ የሆኑ፣ ወላጅ የሆኑ ወይም ትዳር የያዙ ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ ትምህርት እንዲቀጥሉ እናበረታታለን። እነዚህ ተማሪዎች መደበኛ የትምህርት ክፍላቸው ውስጥ መቆየትና ከትምህርት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መሳተፍ ይፈቀድላቸዋል። በተጨማሪም ነፍሰ ጡር ተማሪዎች ከወለዱ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሰው መደበኛ የትምህርት ክፍላቸው ውስጥ መልሰው እንዲቀላቀሉና ከትምህርት ውጪ ያሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ከመውለዳቸው በፊት እንደነበረው መሳተፍ ይፈቀድላቸዋል። ማንኛውም ነፍሰ ጡር ተማሪ፣ ወላጅ ወይም ባለትዳር ተማሪ ባለ ትዳር ስለሆነ፣ ነፍሰ ጡር ስለሆነች ወይም ወላጅ ስለሆነ ክፍል ውስጥ ትምህርት መነፈግ ወይም ከትምህርት ውጪ ያሉ ክፍሎችን መነፈግ፣ ለጊዜው መባረር፣ እስከመጨረሻው መባረር፣ መቀጣት አይችልም።

11.2 በዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጠቀሱትን ማናቸውንም መብቶች የሚጥስ ማንኛውም ግለሰብ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ በክፍል 23.0 ላይ ባሉት አቅርቦቶች መሠረት አቤቱታ ሊቀርብበት ይችላል።

## 12.0 የተማሪ አስተዳደር

12.1 ተማሪዎች ራሱን የቻለ፣ ዴሞክራሲያዊ የራስ አስተዳደር የማግኘት መብት አላቸው። ጥሩ የትምህርት ሂደት ሁኔታ ላይ ያሉ ተማሪዎች ሁሉ ድምጽ የመስጠትና የምርጫ ተሳታፊ ሆኖ ከዛ የመምራት መብት አላቸው። የተማሪ አስተዳደሩ በየዓመቱ ምርጫ ይደረግበታል።

12.2 ሁሉም የተማሪ ሹም ለእጩነት ማቅረብና የምርጫ ሂደቶች የሚዋቀሩትና ሥራ ላይ የሚውሉት በተማሪዎች ሲሆን የትምህርት ባለሥልጣን፣ አስተማሪ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ቁጥጥር ያደርጋል እንጂ ጣልቃ አይገባም።

12.3 ሁሉም የተማሪ ሹም እጩዎች የምርጫ ዘመቻ የማድረግ መብትና የትምህርት ቤት መገልገያዎችን እኩል መጠቀ ይችላሉ።

12.4 የተማሪ አስተዳደሩ ድርጅት፣ ሂደቶችና ሥልጣኖች የሚደነገጉት ተማሪዎች በጻፉት ሕገ መንግሥት ሆኖ ሕገ መንግሥቱ በማንኛውም ወቅት አስተዳደሩ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን አናሳ ብሔረሰቦች የማዳመጥ ኃላፊነት ያለበት ሆኖ በተማሪ አስተዳደሩ ውስጥ እነዚህ ቡድኖች ውክልና እንደሚኖራቸው ማረጋገጥ፡ አለበት።

## 13.0 የቅጣት ፖሊሲና ሂደቶች

13.1 አጠቃላይ ፖሊሲ

የትምህርት ቤት ኮሚቴ ፖሊሲ እንደሚለው ተማሪዎች የምግባር ችግር ሲኖራቸው ከፍተኛ የቅጣት እርምጃ ላይ ከመደረሱ በፊት ሁሉም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ችግራቸውን ለመፍታት መርዳት አለበት። ከትምህርት ቤት ለጊዜው ማስወጣት የሚታየው እንደ መጨረሻ አማራጭ ነው። ስለዚህ አንድ ተማሪ ትምህርትና ጥሩ ምግባር እንዲኖረው ለማበረታታት የትምህርት ቤት ሠራተኞች የጊዜያዊ ማስወጣት እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ሌሎች አግባብ ያላቸውን የቅጣት እርምጃዎች ሁሉ መጀመሪያ መሞከር አለባቸው። የጊዜያዊ ማስወጣት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ሊወሰዱ የሚችሉ ሌሎች እርምጃዎች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦ ይቅርታ በመጠየቅ መካስ፣ የማህበረሰብ አገልግሎቶች፣ ግጭት ሲፈጠር ለማስታረቅ ሽምግልና፣ የማረሚያ ሥራ ካሳ፣ አማካሪ ማየት፣ ከትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች

ማገድ፣ በምሳ ሰዓት መታገድ፣ ለቅጣት ወደ ቢሮ መላክ፣ ከክፍል ውጪ የቅጣት ሰዓት፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን መገናኘት፣ የሚወዱትን ነገር መከልከል፣ ተማሪን መገናኘት፣ ወደ መሪ አማካሪ መላክ፣ ወደ ክፍል ደረጃ ወይም ሕንጻ አስተዳዳሪ መላክ፣ ወደ Student Support Team (SST) (የተማሪ ድጋፍ ቡድን) ለመፍትሄ መላክ፣ የተማሪ ባሕርይ ስምምነት፣ የባሕርይ ድጋፍ ዕቅድ፣ የአስተማሪና የወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ስብሰባ፣ የአስተማሪ ተማሪና የወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ስብሰባ፣ የአስተማሪና የተማሪ ስብሰባ እና/ወይም ማስጠንቀቂያ። ሆኖም ይሄ የመፍትሄ ዝርዝር በዚህ ብቻ የሚያልቅ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፣ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ሁኔታ እያንዳንዱን መፍትሄ እንደማይጠቀሙት መታወቅ አለበት፤ የሚጠቀሟቸው መፍትሄዎች እንደ ጥፋቱ ትልቅነት ይለያያሉ።

13.2 ሌሎች አግባብ ያላቸው ቅድመ ዝግጅታዊ የቅጣት እርምጃዎች

ጊዜያዊ ማስወጣትን ሊያስከትል የሚችል ባሕርይን አስቀድሞ እንዳይከሰት ለማድረግ የከፍተኛ ደርጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊና ተወካዮች የተማሪዎችን ትምህርትና ጥሩ ምግባር ለማበረታታት ማንኛውንም እርምጃ የመውሰድ ፈቃድ አላቸው፣ የሚከተሉትንም ጨምሮ፦

ሀ. ከተማሪው ጋር አንድ ለአንድ አብሮ በመሥራት የችግሩን ምንጭ ለማወቅ መሞከርና አማራጭ መስጠት።

ለ. አስፈላጊ ከሆነ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች (ካስገለገ ቤታቸው በመሄድ) ወይም ከጓደኛ/ጓደኞች ጋር መመካከር።

ሐ. የትምህርት ቤት አማካሪ ወይም የሥነ ልቦና ባለሙያ ጋር መላክ።

መ. የውጪ ማህበራዊ ድርጅቶች ጋር መላክ።

ሠ. ከላይ ካሉት ከማናቸውም ጋር ወይም ከሁሉም ጋር መመካከር።

ረ. ወደ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ጋር መላክ።

ሰ. በግል ወይም ከሌሎች ተማሪዎች ጋር አብሮ መምከር ።

ሸ. ከመደበኛ የትምህርት ክፍሎች በተጨማሪ አስጠኚ መመደብ።

ቀ. ተጨማሪ ሥራ መመደብ።

በ. ከመደበኛ ሰዓት ውጪ ተጨማሪ ሥራ መስጠት።

ተ. ልጁ ልዩ ትምህርት ያስፈልገው እንደሆነ በስቴትና በፌዴራል ሕጎችና ደንቦች መሠረት ግምገማ እንዲደረግለት መላክ።

ቸ. የተረጋገጠ ማስረጃ ያላቸው ስልቶችና መርሃ ግብሮች መጠቀም፣ ለምሳሌ ሽምግልና፣ ግጭት መፍቻ፣ መልሶ አዳሽ ፍትህና አዎንታዊ መፍትሄዎችና ድጋፎች።

13.3 አንድ ተማሪ አውቆም ሆነ ሳያውቅ ማንኛውም የትምህርት ቤት ንብረት ላይ ጉዳት ካደረሰ ለምሳሌ አጥር፣ በር፣ ዛፎች፣ አትክልቶች፣ ሕንጻዎች ወይም ማንኛቸውም የሕንጻ ክፍሎች፣ መስኮቶች፣

መጽሐፎች፣ መሳሪያዎች ወይም የቤትና የቢሮ ዕቃዎች ላይ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊውና ተወካዮች ለወጪው ካሳ ሊጠይቁ ይችላሉ።

13.4 የተከሰተው ጉዳይ አደንዛዥ ዕጽን፣ የጦር መሣሪያን፣ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ጥቃትን ወይምን ምንም ዓይነት ወንጀላዊ ጥሰት የሚመለከት ከሆነ በዚህ *መመሪያ* ክፍል 19 ላይ ያሉት ሂደቶች የሚከተሉትንም ጨምሮ ሥራ ላይ ይውላሉ፦

ሀ. ጉዳዩ የሚመለከተው ሠራተኛ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን እና/ወይም ረዳት ተቆጣጣሪውን ይገናኛል

ለ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኀላፊ የሚከተሉትን ያሳውቃል፦
1. የደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር፣
2. ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በስልክ ከዛም ደብዳቤ በመላክ፣ አስፈላጊ ከሆነም ማረጋገጫ ባለው ፖስታ፣ እና
3. ዋና ሥራ አስኪያጁን።

ሐ. የደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ የክስተት ማሳወቂያ ይልክለታል።

መ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የቅጣት ሂደቶችን በዚህ *መመሪያ* ውስጥ በተዘረዘሩት ተገቢዎቹ ሂደቶች መሠረት የቅጣት ችሎት ሂደቱን ይመራል።

## 14.0 ጊዜያዊ ማባረር

14.1 በኬምብሪጅ ትምህርት ቤት መምሪያ መሠረት ተማሪዎች የምግባር ችግር ሲያጋጥማቸው ከፍተኛ የቅጣት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ችግሩን በሌላ መንገድ ለመፍታት መሞከር አለበት። ሆኖም የተማሪው ባሕርይ ትምህርት ቤቱ የሚረብሽ ከሆነ፣ ለራሱ ወይም ለሌሎች ጎጂ ከሆነ ወይም የCommonwealth of Massachusettsን (የማሳቹሴትስ መንግሥት) ሕጎች የሚጥስ የተከለከለ እንቅስቃሴ ከፈጸመ ጊዜያዊ ማባረር ሊያስፈልግ ይችላል።

14.2 ማንኛውንም የቅጣት እርምጃ ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎች ተገቢውን የፍትህ ሂደት መብታቸውን እንዲያገኙ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ አለበት፦

ሀ. <u>በትምህርት ቤት ውስጥ ጊዜያዊ ማባረር</u>
ከትምህርት ቤቱ ሳይሆን ከመደበኛ የትምህርት ክፍል እንቅስቃሴዎች እስከ አሥር (10) ተከታታይ የትምህርት ቀኖች ወይም በትምህር ዓመቱ ወቅት ለተለያዩ ጥሰቶች ባጠቃላይ ከአሥር (10) የትምህርት ቀን ያልበለጠ ጊዜያዊ መባረር ከመከሰቱ በፊት ተማሪው ይሚከተሉት ይነገሩታል፦

1. ቅጣት ያስከተለው ጥሰት፣

2. የክሱ መሠረት፣ እና

3. ተማሪው ምላሽ ለመስጠት ዕድል ይሰጠዋል።

በትምህርት ቤት ውስጥ የሚካሄድ ጊዜያው ማባረር እንደሚደረግ በተወሰነበት ቀን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ስለ ጥሰቱ፣ ተማሪው ጥሰቱን ፈጽሟል ሊያስብል ያስቻለውን ምክንያትና የትምህርት ቤት ውስጥ ጊዜያዊ መባረር ርዝመት ምን ያህል እንደሆነ በቃል ለማሳወቅ አግባብ ያለው ጥረት ያደርጋል፣ በተጨማሪም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች መጥተው የተማሪውን ትምህርት ሂደትና ባሕርይ፣ ተማሪውን የማሳተፊያ ስልቶችና ለባሕርዩ ምላሽ የሚሆኑ ምላሾችን በተመለከተ እንዲወያዩ የስብሰባ ጥሪ ያደርግላቸዋል። ይህ ስብሰባ ቀጠሮ የሚያዘው የጊዜያዊ መባረሩ ዕለት ወይም ካልተቻለ በተቻለ መጠን በቶሎ ከዛ ቀን በኋላ ይሆናል። የትምህርት ቤት ውስጥ ጊዜያዊ ማባረር ስብሰባ ሂደቶችን የያዘውን ክፍል 16.1ን *ይመልከቱ።*

አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ ጊዜያዊ መባረር ላይ በትምህርት ዓመት ውስጥ ከአሥር (10) ቀን በላይ በተከታታይ ወይም ባጠቃላይ ካሳለፈ፣ ይህን ዓይነት ጊዜያዊ ማባረር የፍትህ ሂደት፣ ይግባኝና ማሳወቂያ ላይ የረጅም ጊዜ ማባረር ነው ተብሎ ይቆጠራል። የረጅም ጊዜ ጊዜያዊ ማባረር ምክክር ሂደቶች የሚለውን ክፍሎች 14.3 እና 16.3 ላይ *ይመልከቱ ።* **እባክዎን ልብ ይበሉ፦** የግል ትምህርት ዕቅድ ላላቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ሂደቶችንና ክፍል 18.0 ውስጥ ያሉትን ሂደቶች ምንም ዓይነት የቅጣት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት መከተል ያስፈልጋል።

ለ. <u>የአጭር ጊዜ ጊዜያዊ መባረር</u>

አንድ ተማሪ እንደ ቅጣት ሆኖ እስከ አሥር (10) ተከታታይ ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት መጓጓዣ አገልግሎቶች ከመታገዱ ወይም ከትምህርት ቤት ከመውጣቱ በፊት ወይም እስከመጨረሻ ከመባረሩ በፊት፣ ተማሪውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በቃልና በጽሑፍ በቤት ውስጥ እንግሊዝኛ የማይናገሩ ከሆነ እንዳስፈላጊነቱ በቤት ውስጥ በሚናገሩት ዋና ቋንቋ የሚከተለውን መረጃ የያዘ ማስታወቂያ ይሰጣቸዋል፦

1. ለቅጣት የዳረገው ጥሰት፣
2. የክሱ መሠረት፣
3. ተማሪው ለስንት ጊዜ እንደሚወጣ፣
4. ከከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኀላፊው ጋር ጊዜያዊ ማስወጣቱን በተመለከተ ለተማሪው የይግባኝ ሂደት ዕድል፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችም በዛ ላይ የመገኘት ዕድል፣
5. የይግባኝ ሂደቱ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ፣
6. ተማሪውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች መገኘት ካለባቸው የትርጉም አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው።

   የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተማሪው የአጭር ጊዜ ጊዜያዊ መውጣቱን በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲያሳልፍ የመፍቀድ ሥልጣን አላቸው።

የአጭር ጊዜ ማስወጣት ምክክር ሂደቶችን በተመለከተ ክፍል 16.2ን *ይመልከቱ።*

አንድ ተማሪ በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ በተከታታይ ወይም ባጠቃላይ ከአሥር (10) ቀን በላይ የትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ እንዲወጣ ቢደረግ፣ ይህ ዓይነቱ ማስወጣት ለፍትህ ሂደት፣ ለይግባኝና ለማሳወቅ ሂደቶች የረጅም ጊዜ ማስወጣት ተብሎ ይታያል። የረጅም ጊዜ ጊዜያዊ ማባረር ምክክር ሂደቶችን ክፍሎች 14.3 እና 16.3 ላይ *ይመልከቱ።* . **እባክዎን ልብ ይበሉ፦** የግል ትምህርት ዕቅድ ላላቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ሂደቶችንና ክፍል 18.0 ውስጥ ያሉትን ሂደቶች ምንም ዓይነት የቅጣት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት መከተል ያስፈልጋል።

ሐ. <u>የረጅም ጊዜ ጊዜያዊ ማባረር</u>

አንድ ተማሪ እንደ ቅጣት ሆኖ እስከ አሥር (10) ተከታታይ ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት መጓጓዣ አገልግሎቶች ከመታገዱ ወይም ከትምህርት ቤት ከመውጣቱ በፊት ወይም እስከመጨረሻ ከመባረሩ በፊት፣ ተማሪውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በቃልና በጽሑፍ በቤት ውስጥ እንግሊዝኛ የማይናገሩ ከሆነ እንዳስፈላጊነቱ በቤት ውስጥ በሚናገሩት ዋና ቋንቋ ወይም በሌላ መንገድ የሚከተለውን መረጃ የያዘ ማስታወቂያ ይሰጣቸዋል፦

1. ለቅጣት የዳረገው ጥሰት፣

2. የክሱ መሠረት፣

3. ተማሪው ለስንት ጊዜ እንደሚወጣ፣

4. ከከፍተኛ ትምህርት ቤት ዋና ኀላፊው ጋር ጊዜያዊ ማስወጣቱን በተመለከተ ለተማሪው የይግባኝ ሂደት ዕድል፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችም በዛ ላይ የመገኘት ዕድል፣

5. የይግባኝ ሂደቱ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ፣

6. ተማሪውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች መገኘት ካለባቸው የትርጉም አገልግሎት የማግኘት መብት አላቸው።

7. ከይግባኝ ሂደቱ በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ተማሪውን ለማባረር ወይም ላለማባረር ለመወሰን የሚጠቀምበትን የተማሪውን መዝገብና ሌሎች ሰነዶች የመቃኘት መብት፣

8. በተማሪው ወይም በወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወጪ ተማሪው በመረጠው ጠበቃ ወይም ተራ ሰው የመወከል መብት፣

9. ስለተከሰተው ጉዳይ የተማሪው የበኩሉን ማብራሪያ የሚያቀርቡ በተማሪው ስም የሚመጡ ምስክሮችን ይዞ የመገኘት መብት፣ ተማሪው ይህን የማድረግ ግዴታ የለበትም፣

10. ትምህርት ቤቱ ያቀረባቸውን ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብት፣

11. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የይግባኝ ሂደቱን እንዲቀዳ ጥያቄ የማቅረብና የድምጽ ቅጂውን ተማሪው ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጠየቁ ጊዜ የመረከብ መብት።

12. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ውሳኔ ዋና ተቆጣጣሪው ጋር ይግባኝ፡ የማለት መብት።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊዎች ተማሪው የረጅም ጊዜ ጊዜያዊ መውጣቱን በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲያሳልፍ የመፍቀድ ሥልጣን አላቸው።

የረጅም ጊዜ ጊዜያዊ ማባረር ምክክር ሂደቶችን ክፍል 16.3 ላይ *ይመልከቱ።*
**እባክዎን ልብ ይበሉ፡-** የግል ትምህርት ዕቅድ ላላቸው ተማሪዎች ተጨማሪ ሂደቶችንና ክፍል 18.0 ውስጥ ያሉትን ሂደቶች ምንም ዓይነት የቅጣት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት መከተል ያስፈልጋል።

መ. በማንኛውም ሁኔታ፣ ተማሪው የትምህርት ቤት ባለሥልጣኖችን፣ ሌሎች ተማሪዎችን፣ ሠራተኞችን እና/ወይም እራሱን በድንገት አደጋ ላይ የሚጥል ካልሆነ ወይም ትምህርት ቤቱን አደጋ ላይ የሚጥል ካልሆነ በስተቀር የጊዜያዊ ማባረሩ ማስታወቂያና የይግባኝ ሂደቱ መከሰት ያለባቸው ተማሪው ከትምህርት ቤት እንዲለቅ ከመጠየቁ በፊት መሆን አለበት። የድንገተኛ ማስወጣት ሂደቶችን ክፍል 15.0 ላይ *ይመልከቱ።* በዚህ ጊዜ የይግባኝ ሂደቱ ሊዘገይ ይችላል ሆኖም አግባብ ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ መካሄድ አለበት።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ የይግባኝ ሂደቱ ላይ የመሳተፍ ዕድል እንዳለ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን/ተንከባካቢዎችን በቃልና በጽሑፍ ለማሳወቅ ተገቢውን ጥረቶች ማድረግ አለበት። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በሌሉበት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የይግባኝ ሂደቱን ለማካሄድ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን/ተንከባካቢዎችን ለማግኘት በቂ ጥረት እንዳደረገ መመዝገብ አለበት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው በጽሑፍ ማስታወቂያ ከላከና ቢያንስ ሁለት (2) ጊዜ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በመረጡት የመገናኛ ዘዴ እነሱን ለመገናኘት ከሞከረ አግባብ ያለው ጥረት እንዳደረገ ይቆጠራል። ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የሚላክ የጽሑፍ ማስታወቂያ እነሱ ለትምህርት ቤቱ በሰጡት አድራሻ በእጅ፣ በአንደኛ ደረጃ ፖስታ ወይም በኢሜል ወይም በሌላ በማንኛውም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በተስማሙበት መንገድ ሊላክ ይችላል።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ እና/ወይም ተወካይ ሁኔታውን ሲገመግሙና ሚዛናዊ ሙያዊ ውሳኔ ሲወስዱ አስፈላጊውን ጥንቃቄ መውሰድ አለባቸው። የማባረር ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት ከተለመደው ውጪ የሆነ ልዩ ሁኔታ ካለ ከግምት ይገባል።

14.3 እንደ ክስተቱ ክብደት፣ ተማሪው በትምህርት ቤት ሕንጻዎች ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ጊቢ ውስጥ፣ ከትምህርት ቤት ወይም ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ ወይም በማንኛውም በትምህርት ቤት ፈቃድ በሚካሄድ ዝግጅት ላይ ትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ የሚከተሉትን የትምህርት ቤት ደንቦች ጥሰቶች ቢያደርግ ሊያስወጡት ይችላሉ፡-

*ሀ. ጥቃትና ድብደባ/አካላዊ ጉዳት/ዛቻዎች*

1. ጥቃትን፣ ኃይልን፣ ማስገደድን፣ ዛቻን፣ ማስፈራራትን ወይም ሌላ ተመሳሳይ ምግባር መጠቀም ወይም ለመጠቀም መሞከር።

2. ዛቻ፣ ጉትጎታ ወይም ማስገደድን ተጠቅሞ የትምህርት ቤት ሠራተኛን ካስቸገረ ወይም ከሞከረ ወይም ማንኛውንም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ኃይልን ወይም ጥቃትን ተጠቅሞም ሳይጠቀምም መረበሽ።

3. አንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛን ወይም ሌላ ሰውን በመሳሪያ ወይም በአደገኛ ዕቃ መጉዳት ወይም ለመጉዳት መሞከር።

4. አንድ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ላይ ወይም ሌላ ሰው ላይ ጥቃትን መፈጸም፣ ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ ወይም መደብደብ ወይም ጥቃትን ለመፈጸም፣ ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ ወይም ለመደብደብ ሙከራ ማድረግ።

5. የትምህርት ቤት ሠራተኛ ላይ ወይም ሌላ ሰው ላይ አካላዊ ጉዳት ማድረስ ወይም ለማድረስ መሞከር።

6. የሌላ ሰውን አካላዊ ደህንነት ኃይል ወይም በመፈጸም አደጋ ላይ መጣል ወይም ጥቃት ለመፈጸም ወይም ኃይል ለመጠቀም በመዛት የሌላ ሰውን አካላዊ ደህንነት አደጋ ላይ ለመጣል መዛት። ኃይል ወይም ጥቃት ለመጠቀም መዛት ማለት ተጠቂው እውነት አካላዊ ጉዳት ይደርስብኛል ብሎ የሚፈራበት ሁኔታ ውስጥ የሚጨምር ግልጽ ድርጊት ነው። ይህ ጥሰት ማዋረድን እና/ወይም የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃትን ይጨምራል።

7. የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃትን መፈጸም ወይም ለመፈጸም ሙከራ ማድረግ።

8. የአንድ ግለሰብን ጤናና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል አግባብ የሌለው አደገኛ የስፖርት ቴክኒክ መጠቀም፣ ለምሳሌ የራስ ቁርን ወይም ሌላ የስፖርት መሳሪያን እንደ አጥቂ መሳሪያ መጠቀም።

9. ጥቃትን፣ ኃይልን፣ ማስገደድን፣ ዛቻን፣ ማስፈራራትን፣ ጉዳትን፣ ድብደባን፣ አካላዊ ጉዳትን፣ የጎረምሶች የፍቅር ጓደኝነት ጥቃትን ማነሳሳት፣ ማበረታታት ወይም መገፋፋት ወይም አግባብ የሌለው የአንድን ሰው ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል አደገኛ የስፖርት ቴክኒክ መጠቀም ወይም ሌላ ተመሳሳይ ምግባር። ይህም ረብሻ ወይም ድብድብ ተፈጥሮ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ከቦታው እንዲርቅ ሲጠየቅ አለመተባበርን ይጨምራል።

10. ጥል (በአካልም ይሁን በአፍ) ወይም ድብድብ ውስጥ መሳተፍ ወይም ለመሳተፍ ሙከራ ማድረግ ወይም ጥቃትና ድብድብ ውስጥ።

*ለ. የጦር መሳሪያ፣ አደገኛ መሳሪያ፣ አደገኛ ዕቃዎች መያዝ*

1. ማንኛውም የጦር መሳሪያ ወይም መሳሪያ ይዞ መገኘት።

2. ማንኛውም ቢላዋ ወይም በሕግ የተከለከለ አደገኛ መሳሪያ ይዞ መገኘት።

3. ማንኛውንም ዕቃ አደገኛ በሆነ ሁኔታ ወይም ለማስፈራሪያ መጠቀም።

ሐ. በቁጥጥር ሥር ያሉ ዕጾች፣ አልኮልና ትምባሆ

1. በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ወይም አልኮል ይዞ ወይም ተጠቅሞ መገኘት።

2. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሆኖ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጀ እንቅስቃሴ ወይም ዝግጅት ላይ ወይም ትምህርት ቤት ባቀረበው መጓጓዣ ላይ ሆኖ በሐኪም ትእዛዝም ሆነ ያለ ትእዛዝ የተገኘ በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ወይም የአደንዛዥ ዕጽ መጠቀሚያ ቁሳቁስ መሸጥ፣ ማሰራጨት ወይም ይዞ መገኘት።

3. ያለ ዶክተር ትእዛዝ የተገኘ ማንኛውም በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ፣ አደንዛዥ መድኃኒት፣ በቁም የሚያስቃዥ መድኃኒት፣ አምፌታሚን፣ ባርቢትዩሬት፣ ማሪዋና፣ አልኮል መጠጥ ወይም ምንም ዓይነት የሚያሰክር ዕጽ ይዞ መገኘት።

4. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሆኖ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጀ እንቅስቃሴ ወይም ዝግጅት ላይ ወይም ትምህርት ቤት ባቀረበው መጓጓዣ ላይ ሆኖ ትምባሆ መጠቀም።

5. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሆኖ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጀ እንቅስቃሴ ወይም ዝግጅት ላይ ወይም ትምህርት ቤት ባቀረበው መጓጓዣ ላይ ሆኖ በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ወይም አልኮል ማሳየት፣ መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት።

6. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሆኖ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጀ እንቅስቃሴ ወይም ዝግጅት ላይ ወይም ትምህርት ቤት ባቀረበው መጓጓዣ ላይ ሆኖ በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ፣ አደንዛዥ መድኃኒት፣ በቁም የሚያስቃዥ መድኃኒት፣ አምፌታሚን፣ ባርቢትዩሬት፣ ማሪዋና፣ አልኮል መጠጥ ወይም ምንም ዓይነት የሚያሰክር ዕጽ መሸጥ፣ ማሰራጨት፣ መጠቀም ላይ መሳተፍ ወይም ይዞ መገኘት።

7. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሆኖ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጀ እንቅስቃሴ ወይም ዝግጅት ላይ ወይም ትምህርት ቤት ባቀረበው መጓጓዣ ላይ ሆኖ የአደንዛዥ መጠቀሚያ ቁሳቁስ ማሳየት፣ መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት።

8. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሆኖ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጀ እንቅስቃሴ ወይም ዝግጅት ላይ ወይም ትምህርት ቤት ባቀረበው መጓጓዣ ላይ ሆኖ ማንኛውንም ዓይነት የአደንዛዥ መጠቀሚያ ቁሳቁስ ሽያጭ፣ ስርጭት ላይ መሳተፍ ወይም ይዞ መገኘት።

9. በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሆኖ፣ በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ፣ አደንዛዥ መድኃኒት፣ በቁም የሚያስቃዥ መድኃኒት፣ አምፌታሚን፣ ባርቢትዩሬት፣ ማሪዋና፣ አልኮል መጠጥ ወይም ምንም ዓይነት የሚያሰክር ዕጽ ሲሸጥ፣ ሲሰራጭ፣ ጥቅም ላይ ሲውል ወይም ሲያዝ ወይም ማንኛውም ዓይነት የአደንዛዥ ዕጽ መጠቀሚያ ቁሳቁስ ሲሸጥ፣ ሲሰራጭ፣ ጥቅም ላይ ሲውል ወይም ሲያዝ ባካባቢው ኖሮ ቦታውን ጥሎ ለመሄድ ምንም ዓይነት ጥረት አለማድረግ።

*መ. ጉትጎታ፣ ኢድሎ፣ ማስፈራራት፣ በኢንተርኔት ማስፈራራትና የዜጋ መብቶች*

1. የሌሎችን የዜጋ መብቶች መጣስ።

2. የጉትጎታ ወይም የአድሎ ተካፋይ መሆን፣ የጾታ ጉትጎታ ድርጊቶችን ጨምሮ።

3. ስድብ፣ የንቀት ቃላት፣ አጸያፊ ቃላት ያለማቋረጥ እና/ወይም ጨቋኝ በሆነ መንገድ መጠቀም።

4. የማዋረጃ እንቅስቃሴዎችን የሚከለክለውን የማሳቹሴትስ ሕግን የሚጥስ እንቅስቃሴ ተካፋይ ሆኖ መገኘት (M.G.L. c. 269, §§17-19).

5. በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ ወይም ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውጪ ሆኖ ማንም ሰው ላይ መዛት፣ መጎትጎት ወይም ማስፈራራት።

6. በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ ወይም ማንኛውም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅ ላይ ሆኖ አጸያፊ፣ ትክክለኛ ያልሆነ፣ ተሳዳቢ እና/ወይም አስቀያሚ ቋንቋ እና/ወይም ምልክት መጠቀም።

7. ማስፈራራትን የሚከለክለውን የማሳቹሴትስ ሕግን የሚጥስ እንቅስቃሴ ተካፋይ ሆኖ (M.G.L.c. 71, §37O).

8. በኢንተርኔት ማስፈራራትን የሚከለክለውን የማሳቹሴትስ ሕግን የሚጥስ እንቅስቃሴ ተካፋይ ሆኖ (M.G.L.c. 71, §37O).

ሠ. ስርቆት፣ ንብረት ማጥፋት እና እሳት ማቀጣጠል

1. ማንኛውንም የትምህርት ቤት ሕንጻ ወይም ንብረት ላይ እሳት መለኮስ ወይም እሳት ለመለኮስ ሙከራ ማድረግ ወይም ንብረት ማጥፋት ወይም ለማጥፋት ሙከራ ማድረግ።

2. በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጀ እንቅስቃሴ ላይ ሆኖ ወይም ትምህርት ቤቱ ያቀረበው መጓጓዣ ላይ ሆኖ የትምህርት ቤት ንብረት ላይ እሳት ለኩሶ የሌሎችን ደህንነት አደጋ ላይ መጣል ወይም የሌሎችን ደህንነት አደጋ ላይ ለመጣል ሙከራ ማድረግ።

3. የእሳት ወይም የፖሊስ ድንገተኛ መውጫ በር እንደሌለ እያወቁ የትምህርት ቤት የሚመስል ደወል መደወል።

4. የትምህርት ቤት ወይም የግል ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወይም ጉዳት ለማድረስ መሞከር ወይም መስረቅ ወይም ለመስረቅ ሙከራ ማድረግ።

5. የትምህርት ቤት ወይም የግል ንብረትን ኃይል በመጠቀም ወይም በማስፈራራት ለመስረቅ ሙከራ ማድረግ።

6. ትምህርት ቤት ውስጥ ሆኖ የሌላ ሰውን ንብረት ማጥፋት ወይም መስረቅ ወይም የተሰረቀ የግል ንብረት ይዞ መገኘት።

7. የትምህርት ቤት ንብረት ላይ ጉዳት አደረሰ ወይም ሙከራ አደረገ፣ የትምህርት ቤት ንብረትን ሰረቀ ወይም የመስረቅ ሙከራ አደረገ።

8. ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ የውሸት ደወል በመደወል ረብሻ ለመፍጠር መሞከር።

9. የውሸት ደወል በመደወል የሌሎችን ደህንነት አደጋ ላይ መጣል።

10. ቦምብ አለ ብሎ በማስፈራራት ወይም ሌሎች የውሸት ዛቻዎች ወይም ተመሳሳይ ብጥብጥ መፍጠር። .

11. ትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ የውሸት ማስጠንቀቂያ ደወል ለማቀነባበር ሙከራ ማድረግ፣ ቦምብ አለ ብሎ ማስፈራራትን፣ የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ ደወል መደወል፣ የነዳጅ ክፍል ደወል መደወል ወይም ሌላ ዓይነት ረብሻን ጨምሮ።

ረ. ሌሎች ረብሻዎች

1. የትምህርት ቤት ንብረት በሆነ ቦታ ላይ የሚደረግ ምክክር ወይም ማንኛውም የትምህርት ቀጣይ አሠራር ወይም ትምህርታዊ እንቅስቃሴን ወይም ማንኛውም ሕጋዊ ስብሰባን እንዳይካሄድ ማድረግ ወይም እንዳይካሄድ ሙከራ ማድረግ።

2. ማንኛውንም በሥልጣኑ የሚንቀሳቀስ የትምህርት ቤት ሠራተኛ የሚሰጠውን መመሪያ ባለመከተል የሌሎች ትምህርት ሂደት ላይ ረብሻ መፍጠር።

3. የማሳቹሴትስ መንግሥት ሕግ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ የሚረብሽ ድርጊት ነው ብሎ በሚከለክለው ድርጊት ላይ ተካፋይ መሆን።

4. ትምህርት ቤቱን፣ የትምህርት ክፍሉን ወይም የትምህርት ክፍሉን እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ የሚረብሽ ወይም ሌላ ግለሰብ ላይ ጉዳት የሚያመጣ እንቅስቃሴ ተካፋይ መሆን።

5. M.G.L.c. 71, §§37H & 37H½ን የሚጥስ ምግባር ተካፋይ መሆን።

6. በትምህርት ቤት ንብረት ላይ ወይም ማንኛውም በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጀ ዝግጅት ላይ በትምህርት ቤት ውስጥ ተገቢ ጠቀሜታ የሌለው ዕቃ ይዞ መምጣት።

7. በትምህርት ቤት ውስጥ ተገቢ ጠቀሜታ የሌለው ዕቃ ይዞ በመምጣት ትምህርት ቤቱን፣ የትምህርት ክፍሉን ወይም የትምህርት ክፍሉን እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ መረበሽ ወይም ለመረበሽ መሞከር።

ሰ. ተደጋጋሚ ጥሰቶች

1. በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ካሉት ደንቦችና ኃላፊነቶች ውስጥ አንዱን ወይም ከዛ በላይ በተደጋጋሚ መጣስ።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው በጊዜያዊ ማባረሪያ የይግባኝ ሂደቱ ላይ የቀረቡትን ተጨባጭ ነገሮችና የተደረሰበትን ስምምነት በይበልጥ ቃኝቶ የጊዜያዊ ማበረሪያ ራዝመቱን ሊጨምርበት ይችላል።

አንድ ተማሪ ለጊዜው ከተባረረ በትምህርት ቤቱ አቅራቢያ መሆንና ማናቸውም የትምህርት ቤት ዝግጅቶች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ አይችልም።

14.4 <u>የተማሪ ድብድብ፣ ግጭት</u>

የተደባደቡ ተማሪዎች ወይም በምንም መንገድ ድብድብ የገፋፉ ተማሪዎች ከፍተኛና ፈጣን የቅጣት እርምጃ ይወሰድባቸዋል። እንደዚህ ዓይነት የረብሻ ባሕርይ በፍጹም በትዕግስት አይታለፍም። ለእንደዚህ ዓይነት ተቀባይነት የሌለው ባሕርይ ቅጣት ከአንድ እስከ አሥር ቀን ከትምህርት ቤት ማስወጣት ይሆናል፣ ርዝመቱ ምን ያህል እንደተሳተፉ፣ ምድብ፣ የጥሰት ብዛቶች እና/ወይም የክስተቱ አስከፊነት ይለያያል። ጥቃት ወይም አንድ ሰውን ማጥቃትና መደብደብ ወንጀል ሲሆን ማንኛውም አካባቢ ጥቃት ሲከሰት ፖሊስ እንደሚጠራና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች Middlesex County Court (ሚድልሴክስ አውራጃ ፍርድ ቤት) ጋር ወንጀላዊ አቤቱታ የማስገባት መብት እንዳላቸው እንደሚነገራቸው ማስተዋል ያስፈልጋል። እንደ ጉዳዩ ሁኔታ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች በራሱ ሚድልሴክስ አውራጃ ፍርድ ቤት ጋር ጥቃቱን እና/ወይም ጥቃትና ድብደባውን በተመለከተ ወንጀላዊ አቤቱታ ሊያስገባ ይችላል። ተማሪዎች ጥል ላይ ሲሆኑ ስለሚያውቁ ካስፈለገ እርዳታ ጠይቀው ጥሉን በሰላም ለመፍታት መሞከር ይጠበቅባቸዋል። አንድ ተማሪ ጉዳዩን የትምህርት ቤት ባለሥልጣኑ ጋር በማቅረብ ድብድብ እንዳይከሰት የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ጥሎችን ለመፍታት የሚረዱ የተማሪና አስተማሪ አስታራቂዎችን በማንኛውም ጊዜ በድህንነትና ጥበቃ ቢሮ በኩል ማግኘት ይቻላል።

የምድቡና ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት አምስት ምድቦች የቅጣቱ መጠን ውሳኔ የሚወሰነው ኃላፊነት ባለው አስተዳዳሪ ሲሆን የእያንዳንዱ ጉዳይ ሁኔታ ታይቶ፣ ሁኔታው ወይም ክስተቶቹ ከፍ ያለ እርምጃ የሚወሰድባቸው ዓይነት ከሆኑ አስተዳዳሪው ለመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ጥፋት ቅጣቱን ከፍ ወዳለ ምድብ ማለትም ከትምህርት ቤት እስከ ማስወጣት ምድብ ሊያሸጋግረው ይችላል።

ምድብ አንድ፡-

ቀስቃሽ/ገፋፊ/አነሳሽ፡-

አንድ ተማሪ ረብሻ ወይም ድብድብ ተፈጥሮ ከቦታው እንዲርቅ ሲጠየቅ አልተባበርም ካለ እዚህ ምድብ ውስጥ ይሆናል።

| | |
|---|---|
| አንደኛ ጥፋት፡- | እስከ ሶስት ቀናት ድረስ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስቆይ ማስወጣት። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል። |
| ሁለተኛ ጥፋት፡- | ከሶስት ቀን እስከ አምስት ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ምክክር። |
| ሶስተኛ ጥፋት፡- | ከአምስት ቀን እስከ ለአሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ምክክር። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ቢሮ ውስጥ የጊዜያዊ ማስወጣት የይግባኝ ሂደት። |

ምድብ ሁለት፡-

ሰው ላይ ጥቃትና ድብደባ፡-

አንድ ሰው ላይ ጥቃት መፈጸም ወይም ጥቃትና ድብደባ መፈጸም ወንጀል ነው። የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤት ማናቸውንም በትምህርት ቤት ውስጥ፣ የትምህርት ቤት አውቶቡስ ላይ ወይም በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች ላይ የሚከሰቱ ወንጀሎችን የማሳወቅ ግዴታ ስላለበት ለፖሊስ ያሳውቃል። ተጠቂዎች

ወንጀላዊ ይግባኝ የማስገባት መብት እንዳላቸው ይነገራቸዋል፣ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶችም አጥቂው ላይ ወንጀላዊ ይግባኝ ሊያስገባ ይችላል።

አንደኛ ጥፋት፡- ከሶስት ቀን እስከ አምስት ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ምክክር።

ሁለተኛ ጥፋት፡- ከአምስት ቀን እስከ ለአሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ቢሮ ውስጥ የጊዜያዊ ማስወጣት የይግባኝ ሂደት።

ምድብ ሶስት፡-

ድብድብ/እርስበርስ ጥቃትና ድብደባ፡-

አንድ ሰው ላይ ጥቃት መፈጸም ወይም ጥቃትና ድብደባ መፈጸም ወንጀል ነው። የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤት ማናቸውንም በትምህርት ቤት ውስጥ፣ የትምህርት ቤት አውቶቡስ ላይ ወይም በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች ላይ የሚከሰቱ ወንጀሎችን የማሳወቅ ግዴታ ስላለበት ለፖሊስ ያሳውቃል። ተጠቂዎች ወንጀላዊ ይግባኝ የማስገባት መብት እንዳላቸው ይነገራቸዋል፣ የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶችም አጥቂው ላይ ወንጀላዊ ይግባኝ ሊያስገባ ይችላል።

አንደኛ ጥፋት፡- እስከ ሶስት ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ምክክር። ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ ሽምግልና መሞከር ይቻላል።

ሁለተኛ ጥፋት፡- ከሶስት ቀን እስከ አምስት ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት ጋር ምክክር። ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ ሽምግልና መሞከር ይቻላል።

ሶስተኛ ጥፋት፡- ከአምስት ቀን እስከ ለአሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ቢሮ ውስጥ የጊዜያዊ ማስወጣት የይግባኝ ሂደት።

ምድብ አራት፡-

ድብድብ/እርስበራስ ጥቃትና ድብደባ በትምህርት ክፍሎች ውስጥ፣ ካፌቴሪያ፣ ስብሰባዎች፣ መተላለፊያ ላይ፣ ጊዜ ማሳለፊያ ላይ ወይም የትምህርት ቤት ዳንስ ላይ ወዘተ. ጥሎች (በአካል ሆነም አልሆነ) በትምህርት ቤታችን ውስጥ ብዙ ሰዎች ባሉበት ሲከሰቱ በቀላሉ ተለዋዋጭ ሁኔታ ይፈጥራሉ። ይህ በጣም የሚያመሰቃቅልና ጎጂ የሆነ ውጤት ያለው ባሕርይ ጥብቅ የሆነ የቅጣት እርምጃ ያስከትላል። ምሳሌዎች፡- ካፌቴሪያ ውስጥ በምሳ ሰዓት፣ በመውጫ ሰዓት ወይም ሕንጻ ውስጥ በሚገባበት ጊዜ፣ የዳንስ ዝግጅቶች ላይ፣ የስፖርት ዝግጅቶች ላይ ወይም ማንኛውም የትምህርት ቤት ስብሰባ ወይም ተያያዥ ዝግጅት ላይ።

አንደኛ ጥሰት፡- እስከ ሶስት ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ምክክር። ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ ሽምግልና መሞከር ይቻላል።

አንደኛ ጥሰት፡- ከሶስት ቀን እስከ አምስት ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ምክክር። ወደ ትምህርት ቤት ሲመለስ ሽምግልና መሞከር ይቻላል።

| | |
|---|---|
| አንደኛ ጥሰት፡- | ከአምስት ቀን እስከ ለአሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ቢሮ ውስጥ የጊዜያዊ ማስወጣት የይግባኝ ሂደት። |

14.5 <u>የውሸት ማስጠንቀቂያ ደወል ማስጮህ</u>

በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ ወይም ማንኛውም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ ፖሊስ እና ወይም የእሳት አደጋ ጣቢያ ምላሽን የሚያስከትል የውሸት ማስጠንቀቂያ ደወል ለማስጮህ የሚያቀነባብር ተማሪ (ማለትም ቦምብ አለ ብሎ ማስፈራራትን፣ የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ ደወል መደወል፣ የነዳጅ ክፍል ደወል መደወል ወይም ሌላ ዓይነት ረብሻ) የቅጣት እርምጃ ይወሰድበታል። ይህ ዓይነት ሥነ ምግባር ትምህርት ቤት ውስጥ ረብሻ የሚፈጥ ብቻ ሳይሆን የትምህርት ቤት ማህበረሰቡንና ምላሽ ሰጪ ፖሊሶችና የእሳት አደጋ ሠራተኞችን አደጋ ላይ ይጥላል። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነቱ ስነ ምግባር ፍጹም ተቀባይነት አይኖረውም።

| | |
|---|---|
| አንደኛ ጥፋት፡- | ከአምስት ቀን እስከ ለአሥር ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ማስወጣት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ቢሮ ውስጥ የጊዜያዊ ማስወጣት የይግባኝ ሂደት። |

14.6 <u>ከትምባሆ ነጻ የመሆን ፖሊሲ</u>

በ1993 ዓ.ም. በወጣው Commonwealth of Massachusetts' Educational Reform Act (የማሳቹሴትስ መንግሥት የትምህርት ማሻሻያ ሕግ) ክፍል 37H መሠረት፡- *"የእያንዳንዱ የትምህርት ቤት አውራጃ ዋና ተቆጣጣሪ የአስተማሪዎችና የተማሪዎች ምግባር በተመለከተ ያሉትን ፖሊሲዎች ማተም አለበት። እነዚህ ፖሊሲዎች በትምህርት ቤት ሕንጻዎች ውስጥ፣ በትምህርት ቤት መገልገያዎች ላይ፣ በትምርህት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት አውቶቡሶች ላይ ማንም ሰው፣ የትምህርት ቤት ሠራተኞችን ጨምሮ ትምባሆ መጠቀም እንደማይችል መጥቀስ አለባቸው።"* *ሠራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ማንም ሰው ትምባሆ ማጨስ፣ ማኘክ ወይም ማንኛውም ዓይነት የትምባሆ አጠቃቀም በትምህርት ቤት አውራጃ ሕንጻዎች ውስጥ በሙሉ ክልክል ነው። "የትምባሆ ምርቶች" ማለት በማንኛውም መልኩ የሚቀርብ ትምባሆ ማለትም ሲጋራን፣ ሲጋርን፣ ሱረትን፣ የሚታኘክ ትምባሆን፣ ኤሌክትሪክ ሲጋራን፣ ኒኮቲን ማትነኛን፣ ጭስ የሌላቸው የትምባሆ ምርቶችንና ሌሎች ተመሳሳይ ምርቶችን ያጠቃልላል። ይህ ፖሊሲ የሚመለከተው ሁሉን በትምህርት ቤት ድጋፍ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶችን፣ የስፖርት ጨዋታዎችን፣ እነዚህ ዝግጅቶች በትምህርት ቤት አውራጃው ንብረትና ቅጥረ ግቢ ውስጥ ቢሆኑም ባይሆኑም ነው። የትምህርት ቤት ንብረት እና/ወይም ቅጥረ ግቢ ማለት እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ዙሪያ እስከሚገኘው የእግረኛ መንገድ ድረስ ያለው መሬት ነው። በተለይም የኬምብሪጅ ሪንጅና ላቲን ትምህርት ቤት ቅጥረ ግቢ፣ ከትምህርት ቤት ቅጥረ ግቢ ክፍል ሆኖ የሚቆጠረውን የኬምብሪጅ መንገሥት መጽሐፍት ቤት ቅጥረ ግቢን ያካትታል ስለዚህም የተማሪ ፖሊሲዎች ይመለከቱታል። እነዚህ መስፈርቶች የተጣሱበት ሁኔታ ታይቶ፣ አንድ ተማሪ ቅጣት ይሰጠውና ወደ ተገቢው የትምባሆ እርዳታ እና/ወይም የዕጽ አብዢ የከተማ/ጤና ትምህርት መርሃ ግብር ሊላክ ይችላል።*

## 15.0 ድንገተኛ ማስወጣት

15.1 ድንገተኛ ማስወጣት

አንድ ተማሪ ጥፋት አጥፍቶ ቅጣት ላይ ሳለ ሁልጊዜ መምጣቱ ሰዎችን ወይም ንብረትን አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ወይም የትምህርት ቤት ሥርዓቱን በከፍተኛ ደረጃ የሚረብሽ ከሆነና በከፍተኛ ደረጃ

የትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ግምገማ ረብሻውን ለማብረድ ሌላ አማራጭ ከሌለ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ እና/ወይም ተወካይ አንድ ተማሪን ከትምህርት ቤት ለጊዜው ሲያስወጣው ይቻላል። ድንገተኛ ማስወጣቱ ከወጣበት ቀን በኋላ ከሁለት (2) ቀን በላይ መርዘም የለበትም፣ በዚህ ጊዜ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከዚህ በታች *መመሪያው* ውስጥ ክፍል 15.2 ላይ ያሉትን ሂደቶች መከተል አለበት።

15.2 ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችንና ተማሪን ስለ ድንገተኛ ማስወጣት ማሳወቅ

ድንገተኛ ማስወጣቱን የፈቀደው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ እና/ወይም ተወካይ የሚከተለውን ያደርጋል፦

ሀ. ተማሪውንና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ስለ ድንገተኛ ማስወጣቱ፣ ስለ ምክንያቱና ከላይ በዚህ *መመሪያ* ክፍል 14.2(ለ)(1) – (6) ውስጥ ስላሉት ሌሎች ነጥቦች በቃል ለማሳወቅ ፈጣንና ተገቢ የሆኑ ጥረቶች ማድረግ።

ለ. ማንኛውም ተማሪ ቅጣት የሚያስከትል ጥፋት ሲያጠፋ ለተማሪው ደህንነትና መጓጓዣ ተገቢው ዝግጅት ሳይደረግ ከትምህርት ቤት አለመውጣቱን ማረጋገጥ።

ሐ. ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ለተማሪው ከላይ በዚህ *መመሪያ* ክፍል 14.2(ለ)(1) – (6) ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት የጽሑፍ ማስታወቂያ ማቅረብ።

መ. በዚህ *መመሪያ* ክፍል 16.2 ወይም 16.3 ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ፊት የይግባኝ ዕድል እንዳግባብነቱ ለተማሪው መስጠትና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች አምስቱ (5) የትምህርት ቀኖች የጊዜ ገደብ ከማብቃታቸው በፊት ይግባኙ ላይ የመገኘት ዕድል መስጠት፣ ለይግባኙ የተሰጠው ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ በተማሪውና በወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ስምምነት ካልተራዘመ በስተቀር።

ሠ. ይግባኙ የተካሄደ ዕለት በቃል ውሳኔ ማስተላለፍና ከሚቀጥለው ቀን ሳያልፍ በጽሑፍ ውሳኔውን ማስረከብ።

## 16.0 የጊዜያዊ ማስወጣት ምክክር

16.1 <u>በትምህርት ቤት ውስጥ ቆይታ የሚደረግበት ማስወጣት ምክክር</u>
የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ተማሪውን ቅጣት ስላስከተለው ጥፋትና ስለ ክሱ መሠረት ያሳውቀውና ተማሪው ምላሽ የመስጠት ዕድል ይሰጠዋል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪው ቅጣት የሚያስከትለውን ጥፋት አጥፍቷል ብሎ ከወሰነ ለተማሪው በትምህርት ቤት ውስጥ ሆኖ ከክፍል የሚወጣው ለምን ያህል ጊዜ እንደሆነ መንገር አለበት። የማስወጣት ውሳኔው የተወሰነ ዕለት ቅጣት ስለሚያስከትለው ጥፋት፣ ተማሪው ጥሰቱን አድርጓል ብሎ ለመወሰን ስላስቻሉት ምክንያቶችና በትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረገው ማስወጣት የጊዜ ርዝመቱ ምን ያህል እንደሆነ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን/ተንከባካቢዎችን በቃል ለማሳወቅ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተገቢውን ጥረቶች ማድረግ አለበት። በተጨማሪም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የተማሪውን የትምህርት ሁኔታና ባሕርይ፣ ተማሪን ለማሳተፍ ያሉ ስልቶችንና ለባሕርዩ ምላሽ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ለመወያየት ወላጆችን/አሳዳጊዎችን/ተንከባካቢዎችን ለስብሰባ እንዲመጡ መጋበዝ አለበት። እንደዚህ ዓይነቱን ስብሰባ ለማካሄድ በተቻለ መጠን የማስወጣቱ ዕለት ቀጠሮ መያዝ አለበት፣ ይህ ካልሆነ በተቻለ መጠን በቶሎ ሌላ ጊዜ መደረግ አለበት። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና

ኃላፊው ቢያንስ ሁለት (2) ጊዜ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ለመገናኘት ከሞከረና ከመዘገበ፣ ይህ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ስለ ማስወጣቱ በቃል ለማሳወቅ አግባብ ያለው ጥረት እንደሆነ ይቆጠራል።

በተጨማሪም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ለተማሪውና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ስለ ትምህርት ቤት ውስጥ ማስወጣቱ፣ ምክንያቱንና የጊዜውን ርዝመት ጨምሮ በጽሑፍ ማሳወቂያ ይልካል፣ እንዲሁም የተማሪውን የትምህርት ሁኔታና ባሕርይ፣ ተማሪን ለማሳተፍ ያሉ ስልቶችንና ለባሕርዩ ምላሽ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን ለመወያየት ወላጆችን/አሳዳጊዎችን/ተንከባካቢዎችን ለስብሰባ እንዲመጡ መጋበዝ አለበት፣ ስብሰባው ከዚህ በፊት ካልተከሰተ። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ማስወጣቱ በተከሰተ ቀን የጽሑፍ ማስታወቂያ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች እነሱ ለትምህርት ቤቱ በሰጡት አድራሻ በእጅ፣ በአንደኛ ደረጃ ፖስታ ወይም በኢሜል ወይም በሌላ በማንኛውም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በተስማሙበት መንገድ መላክ አለበት ይችላል። ተማሪው ከትምህርት ቤት በወጣበት ወቅት የትምህርት ሂደቱን ለማስቀጠል ክሬዲት የማግኘት፣ የቤት ሥራዎችን የማካካስ፣ ፈተናዎችን የመውሰድ እና ፕሮጀክቶች የመሥራት ዕድል ይኖረዋል።

በስቴት ደንቦች መሠረት በትምህርት ቤት ውስጥ የሚደረጉ ከተከታታይም ሆነ አጠቃላይ አሥር (10) ቀን በታች የሚቆዩ ማስወጣቶች የአጭር ጊዜ ማስወጣቶች ተብለው አይታዩም። አንድ ተማሪ ከአሥር (10) ቀን በላይ በትምህርት ቤት ውስጥ እንዲወጣ ቢደረግ፣ ይህ ዓይነቱ ማስወጣት ለፍትህ ሂደት፣ ለይግባኝና ለማሳወቅ ሂደቶች የረጅም ጊዜ ማስወጣት ተብሎ ይታያል።

## 16.2 <u>የአጭር ጊዜ ማስወጣት ምክክር</u>

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ቅጣት ስላስከተለው ጥፋትና ስለ ክሱ መሠረትና ማንኛውም ሌላ ተያያዥ መረጃ ለተማሪው ያሳውቃል። ተማሪው ምላሽ የመስጠት ዕድልና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ተማሪው ጥፋቱን አጥፍቶ እንደሆነና ጥፋቱ የሚያስከትላቸውን ነገሮች፣ሌሎች መፍትሄዎች ወይም ውጤቶች ካሉ ውሳኔ ከማድረጉ በፊት ከግምት የሚያስገባቸው መረጃና ስለነበሩት ሁኔታዎች ማብራሪያ የመስጠት ዕድል ይሰጠዋል። በቀረበው መረጃ ላይና በነበሩት ሁኔታዎች ላይ ተመሥርቶ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪው ቅጣት አስከታይ ጥፋቱን አጥፍቶ እንደሆነና ከሆነም ምን ዓይነት መፍትሄ እንደሚኖር ይወስናል።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ስለውሳኔውና ውሳኔው ላይ ለመድረስ ስላስቻሉት ምክንያቶች እንዲሁም ተማሪው እንዲወጣ ከተደረገ የጊዜውን ርዝመት ለተማሪውና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ያሳውቃል። ተማሪው ከትምህርት ቤት በወጣበት ወቅት የትምህርት ሂደቱን ለማስቀጠል ክሬዲት የማግኘት፣ የቤት ሥራዎችን የማካካስ፣ ፈተናዎችን የመውሰድ እና ፕሮጀክቶች የመሥራት ዕድል ይኖረዋል። ውሳኔው በጽሑፍ ይቀርባል።

ተማሪው መዋለ ሕጻናት ውስጥ ከሆነ ወይም ከአጸደ ሕጻናት እስከ 3ኛ ክፍል ባለው ውስጥ ከሆነ ከትምህርት ቤት ከመውጣቱ በፊት ተቆጣጣሪው ለዋና ተቆጣጣሪው ውሳኔውንና ከትምህርት ቤት ውጪ ማስወጣት የተወሰነበትን ምክንያቶች በጽሑፍ ይልክለታል።

## 16.3 <u>የረጅም ጊዜ ማስወጣት ምክክር</u>

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ቅጣት ስላስከተለው ጥፋትና ስለ ክሱ መሠረትና ማንኛውም ሌላ ተያያዥ መረጃ ለተማሪው ያሳውቃል። ተማሪው ምላሽ የመስጠት ዕድልና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ተማሪው ጥፋቱን አጥፍቶ እንደሆነና ጥፋቱ የሚያስከትላቸውን ነገሮች፣ሌሎች መፍትሄዎች ወይም ውጤቶች ካሉ ውሳኔ ከማድረጉ በፊት ከግምት የሚያስገባቸው መረጃና ስለነበሩት ሁኔታዎች ማብራሪያ የመስጠት ዕድል ይሰጠዋል። የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ተገኝተው ከነበረ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ስለ

ተማሪው ምግባር ለመወያየትና ተቆጣጣሪው ውሳኔ ከማስተላለፉ በፊት ከግምት ሊያስገባው የሚገባ መረጃ ለማቅረብና ልዩ ሁኔታዎችን ለማብራራት ዕድል ይሰጣቸዋል።

በተጨማሪም ተማሪውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከይግባኝ ሂደቱ በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪውን ለማስወጣት ወይም ላለማስወጣት ለመወሰን የሚጠቀምበትን የተማሪውን መዝገብና ሌሎች ሰነዶች የመቃኘት መብት፣ በተማሪው ወይም በወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወጪ ተማሪው በመረጠው ጠበቃ ወይም ተራ ሰው የመወከል መብት፣ አላቸው፣ ስለተከሰተው ጉዳይ የተማሪው የበኩሉን ማብራሪያ የሚያቀርቡ በተማሪው ስም የሚመጡ ምስክሮችን ይዞ የመገኘት መብት፣ ሆኖም ተማሪው ይህን የማድረግ ግዴታ የለበትም፣ እንዲሁም ትምህርት ቤቱ ያቀረባቸውን ምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብት፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው የይግባኝ ሂደቱን እንዲቀዳ ጥያቄ የማቅረብና የድምጽ ቅጂውን ተማሪው ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በጠየቁ ጊዜ የመረከብ መብት አላቸው። ተማሪው ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የድምጽ ቅጂ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ካቀረቡ ይግባኙ ከመጀመሩ በፊት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የድምጽ ቅጂ እንደሚደረግና ጥያቄ በቀረበ ጊዜ ግልባጩ ለተማሪውና ለወላጆች/አሳዳጊዎች፣ተንከባካቢዎች እንደሚሰጥ ለተሳታፊዎች ሁሉ ያሳውቃል።

በማስረጃው መሠረትና ልዩ ሁኔታዎችን ከግምት ካስገባ በኋላ፣ መፍትሄ የሚሆነውን ወይም ያስከተለውን ነገር ከረጅም ጊዜ ማስወጣቱ ፋንታ ወይም ከሱ በተጨማሪ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ቅጣት የሚያስከትለውን ጥፋት ተማሪው አጥፍቶ እንደሆነ ይወስናል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ስለውሳኔውና ውሳኔው ላይ ለመድረስ ስላስቻሉት ምክንያቶች እንዲሁም ተማሪው እንዲወጣ ከተደረገ የጊዜውን ርዝመት ለተማሪውና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ያሳውቃል። ተማሪው ከትምህርት ቤት በወጣበት ወቅት የትምህርት ሂደቱን ለማስቀጠል ክሬዲት የማግኘት፣ የቤት ሥራዎችን የማካካስ፣ ፈተናዎችን የመውሰድ እና ፕሮጀክቶች የመሥራት ዕድል ይኖረዋል።
ውሳኔው በጽሑፍ ይቀርባል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ማስወጣቱ በተከሰተ ቀን የጽሑፍ ማስታወቂያ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች እነሱ ለትምህርት ቤቱ በሰጡት አድራሻ በእጅ፣ በአንደኛ ደረጃ ፖስታ ወይም በኢሜል ወይም በሌላ በማንኛውም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በተስማሙበት መንገድ መላክ አለበት ይችላል።

ውሳኔው የረጅም ጊዜ ማስወጣት ከሆነ በጽሑፍ የሚቀርበው ውሳኔ በእንግሊዝኛና በቤት የሚናገሩት ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ሌላ ከሆነ በዛ ቋንቋ፣ ወይም አስፈላጊ ከሆነ በሌላ መንገድ ሲሆን የሚከተሉትን መያዝ አለበት፡-

1. ቅጣት ያስከተለውን ጥፋት ለይቶ ማሳወቅ፣ ይግባኙ የተካሄደበትን ቀንና የይግባኙ ተሳታፊዎች።

2. ቁልፍ ጭብጥ ነጥቦችንና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ያስተላለፋቸውን ውሳኔዎች መግለጽ፣

3. ከትምህርት ቤት የሚወጣበትን ቀንና ወደ ትምህርት ቤት መመልሻ ቀንን ለይቶ ማሳወቅ፣

4. ተማሪው ከትምህርት ቤት በሚወጣበት ጊዜ በትምህርቱ መግፋት እንዲችል የትምህርት አገልግሎቶች የማግኘት ዕድል እንዳለው የሚገልጽ ማስታወቂያ ማካተት፣

5. የረጅም ጊዜ ማስወጣቱ ከሚጀመርበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስ (5) ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ የጽሑፍ ማስታወቂያ በማስገባት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ውሳኔ ዋና ተቆጣጣሪው ጋር ይግባኝ የማለት መብት ተማሪው እንዳለው ማሳወቅ፣ እንዲሁም ተማሪው ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የጽሑፍ ማስታወቂያውን ለማስገባት ያለው የጊዜ

ገደብ እስከ ሰባት (7) ቀን ድረስ እንዲራዘምላቸው ዋና ተቆጣጣሪውን የመጠየቅ መብት እንዳላቸውና ዋና ተቆጣጣሪው የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ውሳኔ በይግባኙ መሠረት እስከሚለውጠው ድረስ የረጅም ጊዜ ማስወጣቱ እንዳለ እንደሚቆይ ማሳወቅ።

ተማሪው መዋለ ሕጻናት ውስጥ ከሆነ ወይም ከአጸደ ሕጻናት እስከ ሶስተኛ ክፍል ባለው መካከል ከሆነ፣ ተማሪው ከትምህርት ቤት ከመውጣቱ በፊት ተቆጣጣሪው ለዋና ተቆጣጣሪው ከትምህርት ቤት ውጪ ማስወጣት የተወሰነበትን ምክንያት የሚገልጽ የጽሑፍ ውሳኔ ይልክለታል።

ምክክሩ M.G.L.c. 71, §37H½ ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት የጊዜው ርዝመት ላልተወሰነ ማስወጣት ከሆነ ክፍል 20.0 ውስጥ ያሉትን ሂደቶች መከተል ያስፈልጋል።

## 17.0 ማስወጣቱን ይግባኝ ማለት

17.1 አንድ ተማሪ ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የረጅም ጊዜ ማስወጣቱ ከሚጀመርበት ቀን ጀምሮ እስከ አምስ (5) ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ የጽሑፍ ማስታወቂያ በማስገባት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ውሳኔ ዋና ተቆጣጣሪው ጋር ይግባኝ ማለት ይችላሉ፣ እንዲሁም ተማሪው ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የጽሑፍ ማስታወቂያውን ለማስገባት ያለው የጊዜ ገደብ እስከ ሰባት (7) ቀን ድረስ እንዲራዘምላቸው ዋና ተቆጣጣሪውን መጠየቅ ይችላሉ፣ ዋና ተቆጣጣሪውም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ውሳኔ በይግባኙ መሠረት እስከሚለውጠው ድረስ የረጅም ጊዜ ማስወጣቱ እንዳለ ይቆያል። ይግባኙ ጊዜውን ጠብቆ ካልገባ ዋና ተቆጣጣሪው ይግባኙን ላይቀበል ይችላል ወይም ጥሩ ምክንያት ካለ በራሱ ፈቃድ ሊቀበል ይችላል።

ተማሪው ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ይግባኝ ካሉና እስከ ሰባት (7) ቀን ይራዘምልኝ ብለው ካልጠየቁና ዋና ተቆጣጣሪው ካልፈቀደ በስተቀር፣ ጥያቄው በገባ በሶስት (3) ቀን ውስጥ ይግባኙ መካሄድ አለበት።

ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ይግባኝ ውስጥ ለማሳተፍ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ በቀና ልብ ጥረት ማድረግ አለበት፣ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ለሱም ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችም የሚመች የቀጠሮ ቀንና ሰዓት ለመያዝ ከሞከረ በቀና ልብ እንደሞከረ ይቆጠራል። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የይግባኙን ቀን፣ ሰዓትና ቦታ የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ ይልካል።

ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ይግባኙን አካሂዶ ተማሪው የተከሰሰበትን ቅጣት አስከታዩን ጥፋት አጥፍቶ እንደሆነና የሚያስከትለው ቅጣት ምን እንደሆነ ይወስናል። በተጨማሪም ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ይግባኙ በድምጽ እንዲቀዳ መሰናዶ ያደርግና ተማሪው ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ቅጂ ይሰጠን የሚል ጥያቄ ባቀረቡ ጊዜ አንድ ቅጂ ይሰጣቸዋል። ይግባኙ ከመጀመሩ በፊት ይግባኙ በድምጽ እንደሚቀዳና ተማሪውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጥያቄ ባቀረቡ ጊዜ አንድ ቅጂ እንደሚሰጣቸው ዋና ተቆጣጣሪው ለተሳታፊዎች በሙሉ አስቀድሞ ያሳውቃል።

17.2 የማስረጃ ቅኝት

ሀ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ተወካይ በመጀመሪያ ዋና ተቆጣጣሪውን በመጀመሪያ ያናግራል፣ በይግባኙ ላይ የቀረበውን ማስረጃም ባጭሩ ያስረዳል። ቀጥሎ ተማሪው፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች እና/ወይም ወካዩ (ጠበቃም ጨምሮ) ስለቀረበው ማስረጃና ስለቅጣቱ ተገቢነት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን ወይም ተወካዩን ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ።

ለ. ተማሪው በይግባኙ ላይ በሙሉ ተገኝቶ ስለ ክሱ ሁሉና ተማሪው ላይ የቀረበውን ማስረጃ መስማት አለበት፣ ሆኖም ስለተማሪው ስነ ልቦናዊ ወይም ስሜታዊ ችግሮች በሚወራበት ጊዜ በወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወይም በወካዩ ፈቃድ ተማሪው ከሂደቱ ሊገለል ይችላል።

ሐ. ይግባኙ ከመጀመሩ በፊት ተማሪው፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወይም ወካዩ የተማሪውን ሙሉ መዝገብ እንዲሁም ስለ ተማሪው ምግባር ማናቸውንም መግለጫ አገላብጦ ለማየት በቂ ጊዜ ይሰጣቸዋል።

መ. ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ይግባኙን በሚያካሂድበት ጊዜ በማስረጃ ደንቦች ወይም በሌሎች የፍርድ ቤት ሂደቶች አይወሰንም፣ አግባብ የሆኑትን ምስክሮች ሁሉ የመጥራትና መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ ሥልጣን አለው።

ሠ. ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ለማንኛውም የትምህርት ቤት ሠራተኛ አማካሪ ሆኖ እንዲያገለግል ወይም ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ አማካሪ ሆኖ እንዲያገለግል ሕጋዊ አማካሪ በይግባኙ ላይ እንዲገኝ ሊያደርግ ይችላል። በይግባኙ ላይ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ አማካሪ ሆኖ የሚያገለግል ሰው ለትምህርት ቤት ሠራተኛውም አማካሪ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፣ ሆኖም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ሕጋዊ አማካሪ የመያዝ መብቱ እንደተጠበቀ ይቆያል።

17.3 ውሳኔ

ሀ. ዋና ተቆጣጣሪው ወይም የትወካዩ የግኝቶችን መዝገብ ይይዛል፣ የዚህም ቅጂ ለተማሪው፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ለከፍተኛ ደረጃት ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ይላካል። ሆኖም ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የዚህ *መመሪያ* ጥሰት አልተከሰተም ወይም ከማስወጣት ጋር ያልተያያዙ አማራጮች በጥሞና ከግምት ውስጥ አልገቡም ብሎ ከገመገመ፣ ማስወጣቱን በተመለከተ ምንም ዓይነት ሰነድ በተማሪው መዝገብ ውስጥ አይካተትም፣ በ Student Record Regulations (የተማሪ መዝገብ ደንቦች) (**ተጨማሪ መግለጫ ሀ**) መሠረት ቅጂ የማግኘት መብት ካላቸው ሰዎች ሌላ ለማንም ግለሰብም አይነገርም። ማስወጣቱ ተጀምሮ ሙሉ ለሙሉ ካላለቀ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ተማሪው ወዲያውኑ ተመልሶ እንዲገባ ወስነው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ተማሪው መልሶ መግቢያ ምክክር ስብሰባ ላይ ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ጋር እንዲገናኙ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ለ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ የማካካሻ ተግባሮች ዝርዝር በጽሑፍ ያቀርብለታል።

ሐ. ዋና ተቆጣጣሪው እንደ ይግባኝ ሹም ሆኖ ላልተገኘባቸው ክሶች በሙሉ፣ እንደ ይግባኝ ሹም ሆኖ የተገኘው የዋና ተቆጣጣሪው ተወካይ የውሳኔውን መነሻ ጨምሮ የጭብጥ ነገሮች ግኝቱን በጽሑፍ ያሰፍራል። ዋና ተቆጣጣሪው ይግባኝ ሹም ሆኖ በተገኘበት ጊዜያት በክፍል 17.3 ውስጥ ያሉት አቅራቦቶች በሥራ ላይ ይውላሉ፣ በዚህ *መመሪያ* ክፍሎች 20 እስከ 23 ውስጥ ያሉት ሌሎች ሂደቶች ሥራ ላይ የሚውሉበት ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር። ይግባኙ በተካሄደ በአርባ ስምንት (48) ሰዓት ውስጥ ለተማሪው፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተቆጣጣሪዎች፣ የተማሪው አማካሪ ወይም ወካይ ካለ፣ ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊና ለዋና ተቆጣጣሪ የግኝቶች ግልባጭ ይላከላቸዋል። የይግባኝ ሹሙ ዋና ተቆጣጣሪው ባልሆነባቸው ጊዜዎች በሙሉ፣ ተማሪው የይግባኝ ሹሙን ውሳኔ ይግባኝ የማለት መብት እንዳለው የሚገልጽ መግለጫ ግኝቶቹ ማካተት አለባቸው።

ሐ. ተማሪው የይግባኝ ሹሙን ውሳኔ ይግባኝ ማለት በሚፈልግበት ወቅት፣ የተማሪው ይግባኝ የይግባኝ ሹሙ ጋር መግባት ያለበት ውሳኔው በደረሰው ባምስት (5) ቀን ውስጥ መሆን አለበት። መርማሪው የይግባኝ ጥያቄ በደረሰው ጊዜ የግኝቶቹንና የይግባኙን መዝገብ ለዋና ተቆጣጣሪው ያስተላልፋል። የይግባኙ መዝገብ ተማሪው በጠየቀ ጊዜ በነጻ ይሰጠዋል። ተማሪው የጽሑፍ መግለጫዎችና መከራከሪያ ነጥቦች ለዋና ተቆጣጣሪው ማስረከብ ይችላል እና/ወይም ከዋና ተቆጣጣሪው ጋር እንዲገናኝ ጣይቄ ሊያቀርብ ይችላል።

መ. ዋና ተቆጣጣሪው ለተማሪው፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች፣ የተማሪው ወካይ ካለ ለወካዩ እና ለከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ይግባኙ ከተካሄድ በኋላ በአምስት(5) ቀን ውስጥ ውሳኔውን መላክ አለበት፣ ይህ ውሳኔ የቀድሞውን የሚያጠናክር፣ የሚለውጥ ወይም የሚያሻሽል ሊሆን ይችላል። የማስወጣቱ ጊዜ በሚያበቃበት ወቅት ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተቆጣጣሪዎችና ተማሪው መልሶ መግቢያ ምክክር ላይ እንዲገኙ ሊጠይቅ ይችላል። ዋና ተቆጣጣሪው የሚያስተላልፈው ውሳኔ ማስወጣቱን በተመለከተ የትምህርት ቤት አውራጃው የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል።

ሠ. አንድ የይግባኝ ሂደት፣ ይግባኝ ወይም ኦፊሲዬላዊ ያልሆነ አስተድደራዊ ውሳኔ ተደርጎ አንድ ተማሪ ክስ የቀረበበትን ጥፋት እንዳላጠፋ ከተደረሰበት፣ ሁሉም ስለጉዳዩ የሚያነሱ ነገሮችና የቅጣት ሂደቶች ከተማሪው መዝገብ ይሰረዛሉ። ዋና ተቆጣጥሪው ወይም ተወካዩ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተቆጣጣሪዎችንና ተማሪውን ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ መዝገቦችና የቅጣት ሂደቶች በሙሉ እንደተሰረዙ በጽሑፍ ያሳውቃቸዋል።

ረ. ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የስቴቱ የትምህርት ቦርድ ባወጣቸው ደንቦች መሠረት፣ የማስወጣት መዝገቦችን በሙሉ (ማለትም ዝርዝሮችን) ይይዛል፣ እነዚህም ስም፣ ቀን፣ ርዝመትና ምክንያቶችን የያዙ መሆን አለባቸው። ሆኖም እነዚህ መዝገቦች ለሕዝብ የሚቀርቡ ከሆነ የማንንም ተማሪ ወይም የተማሪውን ቤተሰብ ማንነት ማሳወቅ አይችሉም።

## 18.0 የልዩ ትምህርት/504 ዕቅድ የቅጣት ሂደቶች

18.1 በፌዴራልና በስቴት ሕጎች ፍቺ መሠረት የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች በዚህ ክፍል ውስጥ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የዚህ *መመሪያ* አቅርቦቶች ይመለከታቸዋል።

18.1.1 የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) እና/ወይም 504 ዕቅድ ለእያንዳንዱ ተማሪ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ያለውን መደበኛ የቅጣት ደንብ መከተል ይችል እንደሆነ ወይም የተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት የዚህን የቅጣት ወይም የማንኛውም የትምህርት ቤት ደንቦች መሻሻል ይጠይቅ እንደሆነ ያመለክታል። ማናቸውም የቅጣት ደንብ ወይም የትምህርት ቤት ደንቦች ማሻሻያዎች በተማሪው IEP እና/ወይም 504 ዕቅድ ውስጥ ይገባል።

18.1.2 የተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት የተማሪው ባሕርይ ላይ የሚንጸባረቅ ከሆነ፣ እንደዚህ ዓይነት ባሕርዮች የሚስተናገዱት በ TEAM ሂደት አማካኝነት ይሆናል።

18.1.3 በ*መብቶችና ኃላፊነቶች መመሪያ* መሠረት አስተዳደራዊ ውሳኔ ከማድረግ በተጨማሪ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው (ወይም ተወካዩ) የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮን (ወይም ተወካዩን) የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለውና የተማሪው IEP እና/ወይም 504 ዕቅድ *መመሪያው* ውስጥ ያሉት የቅጣት ደንቦች ወይም የትምህርት ቤቱ ደንቦች ማሻሻያ እንደማያስፈልጋቸው የሚያሳይ ከሆነ የተማሪውን ጥፋት ያሳውቃል፣ እንዲሁም የማስወጣት ማስታወቂያ ግልባጭ ለተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ይላካል።

18.2 የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ሠራተኞች የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያላቸውን ተማሪዎች በተመለከተ በዚህ *መመሪያ ሥር* ባሉ በሁሉም አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ውስጥ ተሳታፊ ይሆናሉ።

18.2.1 በዚህ *መመሪያ ሥር* ያለ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተማሪ ምደባ ላይ ተጽዕኖ ከሌለው እና/ወይም በአንድ ትምህርት ዓመት ውስጥ ተማሪው በአጠቃላይ ከአሥር (10) ቀን በላይ እንዲወጣ ካልተደረገ የ TEAM ስብሰባ አስፈላጊ አይደለም።

18.2.2 በዚህ *መመሪያ ሥር* ያለ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተማሪ ምደባ ላይ ተጽዕኖ ካለው እና/ወይም በአንድ ትምህርት ዓመት ውስጥ ተማሪው በአጠቃላይ ከአሥር (10) ቀን በላይ እንዲወጣ ከተደረገ፣ ቅጣትን በተመለከተ ምንም ዓይነት አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመደረጉ በፊት የTEAM ስብሰባ መደረግ አለበት።

18.3 በዚህ *መመሪያ ሥር* አስተዳደራዊ ውሳኔ ከመደረጉ በፊት ተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት አለበት ተብሎ መሰየሙን ወይም ልዩ ትምህርት ያስፈልገው እንደሆነ ለመገምገም ተልኮ ግን ገና ብቃት እንዳለው አለመወሰኑን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ መገምገም አለበት።

18.3.1 አንድ ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቃት እንዳለው ገና ግምገማ ያልተደረገለት የምግባር ወይም ሌላ ድንብ የጣሰ ተማሪ፣ የቅጣት እርምጃ ያስከተለውን ጥፋት ከማጥፋቱ በፊት ትምህርት ቤቱ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ያለበት ተማሪ መሆኑን የማያውቅ ከነበረ በስቴቱና በፌዴራል የልዩ ትምህርት ሕጎች የቀረቡ ጥበቃዎችን መጠቀም ይችላል።

ሀ. የቅጣት እርምጃውን ያስከተለው ጥፋት ከመከሰቱ በፊት የሚከተለው ከተከሰተ የትምህርት ቤት መምሪያው ተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት እንዳለው ዕውቀት ነበረው ተብሎ ይታሰባል፦

(1) ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ለተቆጣጣሪዎች ወይም ለአስተዳደር ሥራተኞች ወይም ለልጁ አስተማሪ ልጁ ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉት በጽሑፍ ሐሳባቸውን አካፍለው ነበር፣ ወይም

(2) ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ተማሪው ግምገማ እንዲደረግለት ጥያቄ አቅረበው ነበር፣ ወይም

(3) ተማሪው ስላሳየው ባሕርይ ሐሳብ ይዟቸው የተማሪው አስተማሪ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ሠራተኛ በቀጥታ ለተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ወይም የተማሪ አገልግሎቶች ቢሮ ውስጥ ላለ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ አሳውቀው ነበር።

ለ. የትምህርት ቤት መምሪያው ተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት እንዳለው ዕውቀት አልነበረውም ተብሎ የሚታሰበው የሚከተለው ከተከሰተ ነው፦

(1) ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ተማሪው ግምገማ እንዲደረግለት አልፈቀዱም፣ ወይም

(2) ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ለተማሪው አገልግሎቶች አንቀበለም ብለው እምቢ ብለዋል፣ ወይም

(3) ተማሪው ግምገማ ትደርጎለት ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቃት የለውም ተብሎ ተወስኗል።

ሐ. የትምህርት ቤት መምሪያው ተማሪው የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኛ እንደሆነ ዕውቀት አልነበረውም ተብሎ ከተገመተ፣ ከሚከተሉት ገደቦች በስተቀር ተማሪው ላይ በዚህ መመሪያ ውስጥ ባለው የቅጣት ድንብ መሠረት የቅጣት እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፦

(1) ተማሪው ቅጣት ላይ ባለ ጊዜ የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ግምገማ እንዲደረግለት ከጠየቁ ግምገማው በተፋጠነ መልኩ መካሄድ አለበት፣ እና

(2) ግምገማው እስከሚገባደድ ድረስ ተማሪው የትምህርት ቤት ሥልጣናት በመደቡለት የትምህርት ምደባ ውስጥ ይቆያል።

18.4 በዚህ *መመሪያ ሥ*ር አንድ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተማሪው ምደባ ላይ ተጽዕኖ ካመጣ እና/ወይም በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ ባጠቃላይ ከአሥር(10) ቀን በላይ የሚያስወጣው ከሆነ እና/ወይም ውጤቱ እስከመጨረሻው መባረር ከሆነ የሚቀጥሉት አቅራቦቶች ሥራ ላይ ይውላሉ፦

18.4.1 የተማሪው ጥፋት የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳቱ መገለጫው መሆኑን ለመገምገም ትምህርት ቤቱ፣ የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ሌሎች የሚመለከታቸው የተማሪው TEAM የመገለጫ ግምገማ ያደርጋሉ። TEAM ይህንን ግምገማ ሲያደርግ የሚከተሉትን ከግምት አስገብቶ ነው፦ (ሀ) ምግባሩ የተከሰተው በቀጥታ በልጁ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ምክንያት ወይም ከልዩ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳት ጋር በተያያዘ መሆኑን፣ ወይም (ለ) ምግባሩ የተከሰተው የተማሪው IEP እና/ወይም 504 ዕቅድ በሥራ ላይ ያለመዋሉ ቀጥተኛ ውጤት መሆኑን። እንደ መገለጫው ግምገማ ውጤት ታይቶ፣ የቀረበው ይቅጣት እርምጃ ሥራ ላይ ሊውልም ላይውልም ይችላል።

18.4.2 የተማሪው ምግባር የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳቱ መገለጫው ነው ብሎ TEAM ከገመገመ፣ የተማሪው ባሕርይ ነክ የመፍትሄ ዕቅድ ምደባውን መለወጥ ሆኖ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና የትምህርት ቤት አውራጃው ምደባውን ለመቀየር ካልተስማሙ በስተቀር ተማሪው ከወጣበት ምድብ ይመለሳል። በተጨማሪም IEP እና/ወይም 504 ዕቅድ ውስጥ፣ ምደባ ላይ ወይም ሥራ ማዋል ላይ የተገኙ ጉድለቶችን ለማረም TEAM በስቴትና ፌዴራል ሕጎች መሠረት ፈጣን እርምጃ ይወስዳል፣ የመገለጫ ግምገማ ቡድን ስብሰባ እንዲደረግ መንስኤ የሆነው ምግባር ከመከሰቱ በፊት ለተማሪው ተግባራዊ የባሕርይ ግምገማ ያልተደረገ ከሆነ ይህ እርምጃ ተግባራዊ የባሕርይ ግምገማን ያካትታል፣ እንዲሁም የባሕርይ መፍትሄ ዕቅድ በሥራ ላይ ማዋል ወይም ተማሪው ነባር የባህርይ መፍትሄ ዕቅድ ካለው እሱን ቃኝቶ ማሻሻል ያስፈልጋል።

18.4.3 የተማሪው ምግባር የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳቱ መገለጫው አይደለም ብሎ TEAM ከገመገመ፦

ሀ. ተማሪው ወጥቶ እንዳለ አግባብ ያለው የመንግሥት ትምህርት በነጻ የሚያገኝበትን ዕቅድ TEAM ያጎለብታል፣

ለ. አማራጭ ዕቅዱንና በስቴትና በፌዴራል ደንቦችና ሕጎች መሠረት የሚያስፈልገውን የጽሑፍ ማስታወቂያ TEAM ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ያቀርባል። ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በአማራጭ ዕቅድ ሥር የቀረቡትን አገልግሎቶች ለመቀበል አንስማማም ቢሉ ማስወጣቱን ሥራ ላይ ከማዋል አያግድም።

ሐ. የተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በ Massachusetts Department of Education Bureau of Special Education Appeals (የማሳቹሴትስ ትምህርት መምሪያ የልዩ ትምህርት ይግባኝ ቢሮ) ፊት ቀርበው ይግባኝ እንዲካሄድላቸው አቤቱታ ካስገቡ፣ ትምህርት ቤቱ በዚህ መመሪያ መሠረት ባደረገው አስተዳደራዊ ውሳኔ መሠረት፣ ቅጣቱ እስከሚያበቃ ድረስ ወይም የይግባኝ ሹም የተማሪውን ምደባ እስከሚቀይረው ድረስ ተማሪው ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ምደባ ውስጥ ይቀጥላል።

18.4.4 የምደባ ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ ወይም ከትምህርት ቤት ለአሥር (10) ቀን ወይም ከዛ በላይ ተማሪው በሚወጣበት ጊዜ ሁሉ ተማሪው አግባብ ያለው ነጻ የመንግሥት ትምህርት እንዲቀርብለት ይደረጋል።

የምግባር ደንብ የጣሰ ተማሪን ምደባ ለመቀየር በሚወስኑበት ጊዜ የትምህርት ቤት ሠራተኞች ማናቸውንም ልዩ ሁኔታዎች በግል ይቃኛሉ።

18.4.5 የቅጣት እርምጃውን ሥራ ላይ ለማዋል አስተዳደራዊ ውሳኔ በተደረገ በአሥር (10) ቀን ውስጥ የሚከተለው መከሰት አለበት፡-

ሀ. TEAM ተሰብስቦ ለተማሪው ተግባራዊ የባሕርይ ግምገማ ማድረግ አለበት፣ ይህ የሚሆነው አስቀድሞ የተደረገ ግምገማ ከሌለ ነው፣

ለ. TEAM የተማሪውን የባሕርይ መፍትሄ ዕቅድ ሥራ ላይ ማዋል አለበት፣ ቅጣት ያስከተለው ባሕርይ ከመከሰቱ በፊት እንደዚህ ዓይነት ዕቅድ ሥራ ላይ ውሎ ካልነበረ፣ ወይም

ሐ. ቅጣት ያስከተለው ባሕርይ ከመከሰቱ በፊት ተማሪው የባሕርይ መፍትሄ ዕቅድ ከነበረው TEAM ዕቅዱን ዳግም ቃኝቶ ማሻሻል አለበት።

18.4.6 ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ፈቃድ ቢሰጡም ባይሰጡም፣ ከአርባ አምስት (45) የትምህርት ቀን ላልበለጠ ጊዜና አግባብ ያለው የነጻ መንግሥት ትምህርት ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ ባንዱ ወይም በብዙው ላይ እስከቀረበ ድረስ TEAM ምደባውን ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ መቀየር አለበት ብሎ ሊገመግም ይችላል፡-

ሀ. ተማሪው ትምህርት ቤት ወይም ትምህርት ቤቱ ያዘጋጀው ዝግጅት ላይ መሳሪያ ይዞ ከሄደ፣

ለ. አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም ትምህርት ቤት ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ አውቆ ሕገወጥ ዕጽ እና/ወይም በቁጥጥር ሥር ያሉ ዕጾች ይዞ ቢመጣ፣ ቢጠቀም፣ ቢሸጥ ወይም ቢጠይቅ፣

ሐ. አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፡ወይም የትምህርት ቤት ዝግጅት ላይ ሌላ ሰው ላይ ከፍተኛ የሰውነት ጉዳት ቢያስከትል። "ከፍተኛ የሰውነት ጉዳት" ማለት ለሞት የሚዳርግ፣ ከፍተኛ ሕመም የሚያስከትል፣ ግልጽ የሆነ የሰውነት ክፍል ላይ ወይም አእምሮ ላይ ከባድ ጉዳት የሚያደርስ በሚል ልዩ ፍቺ ይሰጠዋል።

18.4.7 ተማሪው በወቅቱ ያለበት ምደባ ተማሪውን ወይም ሌሎችን ጉዳት ላይ የመጣል ዕድሉ ከፍተኛ ነው ብሎ ትምህርት ቤቱ ከገመገመ፣ ተማሪው እስከ አርባ አምስት (45) ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ወጥቶ ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት ሁኔታ እንዲሸጋገር የሚያደርግ ትእዛዝ ከ

Massachusetts Department of Education Bureau of Special Education Appeals (የማሳቹሴትስ ትምህርት መምሪያ የልዩ ትምህርት ይግባኝ ቢሮ) ሊጠይቅ ይችላል።

## 19.0 የመባረር ፖሊሲ - የጦር መሳሪያዎች፣ አደንዛዥ ዕጾችና ድብደባዎች

19.1 በኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቲ ፖሊሲ መሠረት ተማሪዎች የምግባር ችግር ሲኖራቸው ከፍተኛ የቅጣት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ችግሩን በሌላ መንገድ ለመፍታት ጥረት መደረግ አለበት፣ ማባረር ሁልጊዜ የመጨረሻ አማራጭ መሆን አለበት፣ ሌሎች አማራጮች መጀመሪያ ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው። አንድ ተማሪ ከመባረሩ በፊት ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው የመፍትሄ ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡- ይቅርታ መጠየቅ፣ ካሳ፣ የማህበረሰብ አገልግሎቶች፣ የጥል ሽምግልና፣ የካሳ ፍትህ፣ የእርማት ሥራ፣ አማካሪ ማየት፣ የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ውስጥ አለማሳተፍ፣ በምሳ ሰዓት ቅጣት፣ ለቅጣት ቢሮ መላክ፣ ከትምህርት ክፍል ውጪ ቅጣት፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን መገናኘት፣ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ስብሰባ፣ የልዩ መብት እጦት፣ የተማሪ ውል፣ ወደ መሪ አማካሪ መላክ፣ ወደ ክፍል ደረጃ ወይም ሕንጻ አስተዳዳሪ መላክ፣ ወደ Student Support Team (SST) (የተማሪ ድጋፍ ቡድን) ለመፍትሄ መላክ፣ የተማሪ ባሕርይ ስምምነት፣ የባሕርይ ድጋፍ ዕቅድ፣ የአስተማሪና የወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ስብሰባ፣ የአስተማሪ ተማሪና የወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ስብሰባ፣ የአስተማሪና የተማሪ ስብሰባ፣ ማስጠንቀቂያ፣ የትምህርት ቤት ውስጥ ማስወጣት እና/ወይም ከትምህርት ቤት ውጪ ለጊዜው ማስወጣት። በተጨማሪም በዚህ ፖሊሲ አቅራቦቶች ሥር የሚመደብ ጥሰትን በሚመለከት በአንዳንድ ሁኔታ ላይ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው Massachusetts Department of Children and Families (የማሳቹሴት የልጆችና ቤተሰቦች መምሪያ)፡ጋር ሪፖርት ማስገባት አስፈላጊ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ሆኖም ይሄ የመፍትሄ ዝርዝር በዚህ ብቻ የማያበቃ እንዳልሆነ መታወቅ አለበት፣ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ሁኔታ እያንዳንዱን መፍትሄ እንደማይጠቀሙት መታወቅ አለበት፤ የሚጠቀሟቸው መፍትሄዎች እንደ ጥፋቱ ትልቅነት ይለያያሉ። ሆኖም የተማሪው ባሕርይ ትምህርት ቤቱን የሚረብሽ ከሆነ፣ ለራሱ ወይም ለሌሎች ጎጂ ከሆነ ወይም የCommonwealth of Massachusettsን (የማሳቹሴትስ መንግሥት) ሕጎች የሚጥስ የተከለከለ እንቅስቃሴ ከፈጸመ ቅጣት ሊያስፈልግ ይችላል። የነዚህ መስፈርቶች ጥሰቱ ልዩ ሁኔታ ታይቶ እንደሁኔታው አንድ ተማሪ ቅጣት ተሰጥቶች በተጨማሪም ወደሚመለከተው የከተማ/ጤና ትምህርት መርሃ ግብር ሊላክ ይችላል።

The Commonwealth of Massachusetts Educational Reform Act of 1993 (የ1993 ዓ.ም. የማሳቹሴትስ መንግሥት ትምህርት ሕግ ማሻሻያ) እንደሚለው ማንኛውም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ዝግጅት ላይ፣ የስፖርት ዝግጅትንም ጨምሮ አደገኛ መሳሪያ ወይም በ Chapter 94C ሥር በተሰጠው ፍቺ መሠረት በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ፣ አልኮል፣ ማሪዋና፣ ኮኬይን፣ ኦፒኦይድስና ሄሮይንን ጨምሮ ይዞ የተገኘ ተማሪ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከትምህርት ቤቱ ወይም ከትምህርት ቤት አውራጃው ሊያባርረው ይችላል። በተጨማሪም ማንኛውም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን፣ ረዳት ተቆጣጣሪውን፣ አስተማሪውን፣ ወይም ሌላ የትምህርት ቤት ሠራተኛ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ ወይም ሌሎች ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች ላይ የስፖርት ዝግጅቶችን ጨምሮ፣ የሚደበድብ ተማሪን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከትምህርት ቤቱ ወይም ከትምህርት ቤት አውራጃው ሊያባርረው ይችላል።

ማንኛውም በM.G.L.c. 71, §37H ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ከትምህርት ቤት ለጊዜው ያስወጡት ተማሪ ከዚህ በታች በክፍል 21 ውስጥ ባለው መሠረት የትምህርት አገልግሎቶች የማግኘትና በትምህርቱ የመግፋት ዕድል አለው።

ማንኛውም ስለ እንደዚህ ዓይነት ድብደባ ግንዛቤ ያገኘ ወይም የተመለከተ ሠራተኛ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን በአስቸኳይ ማሳወቅ አለበት።

ስለዚህ ይህ ፖሊሲ የሚመለከተው አደገኛ መሣሪያዎችን ስለመያዝ፣ በቁጥጥር ሥር ያሉ ዕጾችን ስለመያዝና ተማሪዎች ሠራተኞችን ስለመደብደብ ነው።

ማንኛውም በM.G.L.c. 71, §37H አቅራቦቶች መሠረት ከትምህርት ቤት ለጊዜው እንዲወጣ የተደረገ ተማሪ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ከትምህርት ቤት በሚወጣበት ጊዜ የትምህርት አገልግሎቶች የማግኘት ዕድል ይኖረዋል።

19.2 *መሣሪያዎች*

ትምህርት ቤት መሣሪያ ይዞ መምጣት፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም የትምህርት ቤት እንቅስቃሴ ላይ መሣሪያ መጠቀም ወይም ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን ውስጥ፣ ኪስ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ሳሉ፣ በአውቶቡስ ላይ ወይም ከትምህርት ሰዓት ውጪ የሚደረግ እንቅስቃሴ ላይ መሣሪያ ይዞ መምጣት የትምህርት ቤት ደንቦችና ሕጎች ከፍተኛ ጥሰት ነው። **በተጨማሪም ሕገወጥ ነው።** ሶስት ዓይነት መሣሪያዎች አሉ:-

ሀ. "በሕግ አደገኛ" የሆኑ ለምሳሌ ሌላ ሰውን ለማስፈራራት ወይም ለመጉዳት የሚጠቀሟቸው ማናቸውም ሕገወጥ መሣሪያዎች አደገኛ መሣሪያ ይባላሉ። "በሕግ አደገኛ መሣሪያዎች" የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

1. ማንኛውም ዓይነት የጦር መሣሪያዎች፣ ጠብ መንጃን ጨምሮ፣
2. ባለ ሁለት ስለት ጩቤ፣ ሰንጢ ወይም ምንም ዓይነት አውቶማቲክ ስፕሪንግ ያለው እጀታውን በመጫን የሚዘረጋ ቢላዋ፣
3. የጣት መጋጠሚያ ብረት፣ ወይም ሌላ ማንኛውም ዓይነት ተወርዋሪ ወይም ሹል ኮከብ በሳይ ሰው መጉጃ ብረታብረት፣
4. አጭር ዱላ፣ ቀስት ማስፈንጠሪያ ቱቦ ዱላ፣
5. ከቆዳ የተሠራና ሹል ብረቶች ያሉት እጅ ላይ የሚታሠር ነገር፣ ምንም ዓይነት ተመሳሳይ በሌላ ነገር የተሠራ መሳሪያ፣
6. ፊት ላይ መርጫ መሳሪያ፣ አስለቃሽ ጋዝ ወይም ሌላ ማንኛውም ሰውን አቅም ማሳጫ መሳሪያ፣
7. ርችት ወይም ምንም ዓይነት ፈንጂ፣
8. ማናቸውም በ Massachusetts General Laws (የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች) አንቀጽ 269፣ ክፍል 10 ውስጥ የተጠቀሱ መሳሪያዎች።

ለ. ሌሎች የተከለከሉ በ Massachusetts General Laws (የማሳቹሴትስ አጠቃላ ሕጎች) አንቀጽ 269፣ ክፍል 10 ውስጥ መሳሪያ ተብለው ባይጠቀሱም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች ላይ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ

ዝግጅቶች ላይ፣ የስፖርት ዝግጅቶችን ጨምሮ ማምጣት ክልክል ነው። በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች ላይ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች ላይ፣ የስፖርት ዝግጅቶች ላይ ጨምሮ አንድ ተማሪ መያዝ ወይም መጠቀም ክልክል የሆኑ ዕቃዎች፡-

1. ምንም ዓይነት ረጅምም ሆነ አጭር ቢላዋዎች፣ የቁልፍ ማንጠልጠያ ሰንጢዎችና መቅረጫ ቢላዋን ጨምሮ፣

2. ምንም ዓይነት ርዝመት ያለው ስለት፣

3. ምላጮች፣ ካርቶን መቁረጫዎች፣

4. ሰንሰለቶች፣ ጅራፎች ወይም ሌላ ለትምህርት ምንም ጥቅም የሌለው የብረት መሣሪያ ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ምንም ዓይነት አግባብ ያለው ጠቀሜታ የሌለው ዕቃ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች ላይ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች ላይ፣ የስፖርት ዝግጅቶች ላይ ጨምሮ።

ሐ. ሌሎች ማናቸውም አደገኛ በሆነ መንገድ ወይም ለማስፈራራት የሚጠቀሚቸው መደበኛ ዕቃዎች። እነዚህ ዕቃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡- እርሳሶች፣ መቀሶች፣ መርፌዎች፣ ስፒሎች፣ ምስማሮች፣ የአናጺ መሣሪያዎች፣ ወዘተ. እንደነዚህ ዓይነት ዕቃዎችን በአደገኛ ሁኔታ ወይም ለማስፈራሪያ መጠቀም ከትምህርት ቤት ጊዜያዊ ማስወጣትን ወይም እስከመጨረሻው ማባረርን ሊያስከትል ይችላል። በተጨማሪ የአንድ ግለሰብን ጤናና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል አግባብ የሌለው አደገኛ የስፖርት ቴክኒክ መጠቀም፣ ለምሳሌ የራስ ቁርን ወይም ሌላ የስፖርት መሳሪያን እንደ አጥቂ መሳሪያ መጠቀም ጊዜያዊ ማስወጣትን ወይም እስከመጨረሻው ማባረርን ሊያስከትል ይችላል።

***ልብ ይበሉ፡- ምንም ዓይነት የመጫወቻ መሣሪያ ወይም የመሣሪያ ኮፒ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ አውቶቡስ ላይ ወይም በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች ላይ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች ላይ፣ የስፖርት ዝግጅቶች ላይ ጨምሮ ይዞ መምጣት አይፈቀድም። እንደነዚህ ዓይነት ዕቃዎች ከተማሪ ላይ ይወሰዱና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ረዳት ተቆጣጣሪው ይህን ፖሊሲ ጥሷል ብሎ ከገመገመ ተማሪው ከትምህርት ቤት ለጊዜው እንዲወጣ ወይም እስከመጨረሻ እንዲባረር ሊያደርግ ይችላል።***

19.3 <u>*ዕጽ/አደንዛዥ ዕጽ አላግባብ መጠቀም*</u>

ከዚህ በታች የተገለጸው ፖሊሲ የኬምብሪጅ ትምህርት ቤት ኮሚቴ ያጸደቀው አስተዳደራዊ እርምጃ ነው። እነዚህ መመሪያዎች የኬምብሪጅ ፖሊስ መምሪያ ወይም ማንኛውም ሌላ ሕግ አስከባሪ ድርጅት ምርመራ አድርጎ ለሚከሰቱ ሕጋዊ ሂደቶች በምንም ዓይነት መንገድ መተኪያ ሊሆኑ አይችሉም። ይህ ፖሊሲ የተዘጋጀው የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች ሠራተኞች ይህን ፖሊሲ ለጣሱ ተማሪዎች ውሳኔ ለማስተላለፍ እንዲረዳቸው ሲሆን በ603 C.M.R. 28.00 እና ሌሎች የማሳቹሴትስ ስቴት ሕጎችና ደንቦች ውስጥ ያሉ የተማሪ መብቶችን መጣስ የለባቸውም።

ማንኛውም በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የተዘጋጁ ዝግጅቶች ላይ እና/ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዙ ዝግጅቶች ላይ፣ የስፖርት ዝግጅቶች ላይ ጨምሮ በአንቀጽ 94C ውስጥ ባለው ትርጉም መሠረት በቁጥጥር ሥር ያሉ ዕጾችን፣ አልኮል፣ ማሪዋና፣ ኮኬይን ወይም ሄሮይንን ጨምሮ ይዞ የተገኘ ተማሪ በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ከትምህርት ቤቱ ወይም ከትምህርት ቤት አውራጃው ሊባረር ይችላል።

በተጨማሪም አልኮል መጠቀም የተጠቃሚውን ጤናና ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል ስለሚችልና አልኮል ያላቸውን መጠጦች መጠቀም አጠቃላይ ሥርዓትን ማስከበር ላይ ችግር ሊያመጣ ስለሚችል የትምህርት ቤት ኮሚቴው በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም የትምህርት ቤት ዝግጅት ላይ ማንኛውንም አልኮል ያለው መጠጥ ማቅረብ ይከለክላል።

በተጨማሪም በማንኛውም ዕድሜ ያለ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆኖ ትምህርት ቤቱ ያዘጋጀው ፕሮግራም ላይ፣ የስፖርት ዝግጅቶች ላይ ጨምሮ ከመሳተፉ በፊት አልኮል ያለው መጠጥ ሲጠጣ የነበረ ተማሪ፣ ፕሮግራሙ ላይ ከመሳተፍ ይከለከልና እዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባለው የቅጣት እርምጃ መሠረት ቅጣት ይሰጠዋል። እንዲሁም በማንኛውም ዕድሜ ያለ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ሆኖ ትምህርት ቤቱ ያዘጋጀው ፕሮግራም ላይ፣ የስፖርት ዝግጅቶች ላይ ጨምሮ ከመሳተፉ በፊት አልኮል ያለው መጠጥ ይዞ፣ ሲጠቀም፣ አቅራቢያው ሆኖ፣ ሲያሰራጭ ወይም ሲሸጥ የተገኘ ተማሪ፣ ፕሮግራሙ ላይ ከመሳተፍ ይከለከልና እዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባለው የቅጣት እርምጃ መሠረት ቅጣት ይሰጠዋል። ማንኛውም በM.G.L.c. 71, §37H አቅራቦቶች መሠረት ከትምህርት ቤት ለጊዜው እንዲወጣ የተደረገ ተማሪ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ከትምህርት ቤት በሚወጣበት ጊዜ የትምህርት አገልግሎቶች የማግኘትና በትምህርቱ የመግፋት ዕድል ይኖረዋል።

19.4 <u>የዕጽ/አደንዛዥ ዕጽ አላግባብ መጠቀም ፍቺዎች</u>

ሀ. በቁጥጥር ሥር ባለ ዕጽ እና/ወይም አደገኛ ዕጽ አካባቢ መሆን ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ፣ ወይም በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሆኖ፣ በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ፣ ያለ ዶክተር ትእዛዝ የተገኘ በቁጥጥር ሥር ያለ መድኃኒት፣ አደንዛዥ መድኃኒት፣ በቁም የሚያስቃዥ መድኃኒት፣ አምፌታሚን፣ ባርቢትዩሬት፣ ማሪዋና፣ አልኮል መጠጥ ወይም ምንም ዓይነት የሚያሰክር ዕጽ ሲሸጥ፣ ሲሰራጭ፣ ጥቅም ላይ ሲውል ወይም ሲያዝ ወይም ማንኛውም ዓይነት የአደንዛዥ ዕጽ መጠቀሚያ ቁሳቁስ ሲሸጥ፣ ሲሰራጭ፣ ጥቅም ላይ ሲውል ወይም ሲያዝ ባካባቢው ኖሮ ቦታውን ጥሎ ለመሄድ ምንም ዓይነት ጥረት አለማድረግ ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ተማሪ በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ እና/ወይም አደገኛ ዕጽ አካባቢ ተገኘ ማለት በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ፣ ያለ ዶክተር ትእዛዝ የተገኘ በቁጥጥር ሥር ያለ መድኃኒት፣ አደንዛዥ መድኃኒት፣ በቁም የሚያስቃዥ መድኃኒት፣ አምፌታሚን፣ ባርቢትዩሬት፣ ማሪዋና፣ አልኮል መጠጥ ወይም ምንም ዓይነት የሚያሰክር ዕጽ ከሚሸጥ፣ ከሚያሰራጭ፣ ከሚጠቀም ከአንድ ወይም ከብዙ ተማሪዎች ጋር አብሮ የትምህርት ቤት ኮሪዶር ውስጥ ሲራመድ ቢገኝና ይህ ተማሪ አካባቢውን ለቅቆ ለመሄድ ምንም ዓይነት ጥረት ሳያደርግ ሲቀር። ማለትም ተማሪው የምግባር ጥሰት እየተካሄደ መሆኑን እያወቀ ተማሪዎቹንና ጥሰቱን ጥሎ በመሄድ ፋንታ ጥሰቱ አካባቢ መቆየት ከቀጠለ።

ለ. አንድ ተማሪ ትምህርት ቤት ውስጥ ሳለ አልኮል መጠጥ ወይም እጽ ከተጠቀመና አግባብ ያለው ሁኔታ ከሆነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ ተማሪውን ወደ ነርስ ወይም ዶክተር ልኮ፣ የተማሪውን ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች አሳውቆ፣ ጉዳዩን ወደ ተገቢው የሕክምና እና/ወይም የሕግ ተቋም አስተላልፎ ከተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር የምክክር ስብሰባ ቀጠሮ ሊይዝ ይችላል።

ሐ. ዕጽ፣ አልኮልና የሌላ አደንዛዥ ዕጽ ያላግባብ የመጠቀም ችግር ያላቸው ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎቻቸው ችግሩን ለመፍታት የትምህርት ቤት ሠራተኛን እርዳታ ቢጠይቁ ሕክምናና ድጋፍ እንዲያገኙ ወደ ተገቢዎቹ ዕጽ-አብዢ የከተማ/ጤና ድርጅቶች ይመራሉ።

መ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ረዳት ተቆጣጣሪ ፈቃደኛ ከሆነ ተማሪው እንደዚህ ዓይነት ችግር ያለባቸው ሰዎች የሚታከሙበት ልዩ ተቋም ጋር እንዲሄድ ዕድል ሊሰጠው ይችላል። ዕጽ፣ አልኮልና የሌላ አደንዛዥ ዕጽ ያላግባብ የመጠቀም ችግር ያላቸው ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎቻቸው ችግሩን ለመፍታት የትምህርት ቤት

ሠራተኛን እርዳታ ቢጠይቁ ዕቅድ ለማውጣት፣ መፍትሄ ለመፈለግ እንዲሁም ሕክምናና ድጋፍ እንዲያገኙ ወደ ተገቢዎቹ ዕጽ-አብዢ የከተማ/ጤና ድርጅቶች ይመራሉ።

ሠ. እንደዚህ ዓይነት ችግሮችን በተመለከተ የሚደረጉ ውይይቶች በሙሉ በምስጢር ይያዛሉ።

ረ. በተጨማሪም የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊዎች እያንዳንዱን ክስተትና በተማሪውም ላይ ሆነ በምስክሮች ላይ ያስከተለውን ተጽዕኖ በጥሞና አይተው እንዳስፈላጊነቱ ተገቢው ስሜታዊ/ማህበራዊ የደህንነት እርምጃ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋሉ።

ሰ. አልኮልና በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ሲኖር የተማሪዎች ሂደት:-

1. ተማሪው አንድ ሰው ዕጽ ወይም አልኮል እየተጠቀመ፣ እያሰራጨ ወይም እያሳየ እንደሆነ እያወቀ ለመራቅ ጥረት ካላደረገ፣ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት እንዲወጣና ተገቢው የከተማ/ጤና ድርጅት ጋር ሄዶ ስለ ዕጽ ማብዛት ትምህርታዊ መርሃ ግብር ውስጥ እንዲሳተፍ ይደረጋል።

2. ተማሪው የዕጽ ወይም አልኮል መጠቀም ላይ ሊሳተፍ ነበር የቀረበው ብሎ አስተዳዳሪው በቂ ማስረጃ አለ ብሎ ከወሰነ ተማሪው የተጠቀሚው ዓይነት እጣ ፋንታ ይደርሰዋል።

ሸ. በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ይዞ መገኘት ማለት በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሳለ ተማሪው እላዩ ላይ ወይም በተማሪ ቁጥጥር ሥር ያለ ነገር ውስጥ (ለምሳሌ ዕቃ ማስቀመጫ ሳጥን) በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ነበረው ማለት ነው።

ቀ. በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ እና/ወይም አደገኛ ዕጽ መጠቀም ማለት አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ሥልጣን ሥር ሳለ ይህን (ማለትም አልኮል መጠጣት፣ ኮኬይን ወይም ኦፒኦይድ መጠቀም፣ ማሪዋና ማጨስ፣ ኪኒን መዋጥ፣ ወዘተ.) መጠቀሙ ይታወቃል ወይም እንደተጠቀመ ያስታውቃል ማለት ነው። መጠቀም የሚለው በዶክተር ትእዛዝ የተገኘን መድኃኒት አብዝቶ መውሰድንም ይጨምራል።

በ. ይህን ዓይነት ዕጽ ማሰራጨት ማለት ይህን ዕጽ ለሌላ ሰው በገንዘብም ሆነ ያለ ገንዘብ ማስተላለፍ ማለት ነው። በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ መያዝ፣ መጠቀምና ማሰራጨት በማባረር ፖሊሲ ሥር የሚተዳደሩ ናቸው።

19.5 <u>የትምህርት ቤት ሠራተኛ ላይ ድብደባ/ዛቻ</u>

ተማሪዎች ማንኛውንም የትምህርት ቤት ሠራተኛ መደብደብ፣ ማጥቃትና መጎትጎት አይችሉም። እነዚህ ምግባሮች የሚከተለው ፍቺ ይሰጣቸዋል:- (1) አውቆ ወይም በግዴሌሽነት ሌላ ሰው ላይ የአካል ጉዳት ማድረስ፣ (2) አውቆ ሌላ ሰው ላይ በአካል እጎዳሃለሁ ብሎ መዛት፣ ወይም (3) አውቆ ሌላው ሰው መነካቱን እንደማይፈልገው፣ በመጥፎ እንደሚወስደው፣ ፍርሃትና አደጋ ላይ ሊጥል እንደሚችል እያወቀ የዛን ሰው አካል መንካት።
ድብደባ የሚከተሉትን ሊያስከትል ይችላል:- (1) ከአምስት እስከ አሥር ቀን ከትምህርት ቤት ማስወጣት፣ (2) ወንጀላዊ አቤቱታ ማቅረብ፣ እና (3) ፖሊስ ማሳወቅ።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊን፣ ረዳት ተቆጣጣሪን፣ የተማሪዎች ጉዳይ ኃላፊን፣ አስተማሪን፣ የአስተማሪን ረዳት ወይም ሌላ ሠራተኛን በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በትምህርት ቤት ድጋፍ የተደረገ ዝግጅት ላይ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ ስፖርትንም ጨምሮ

ማንኛውም ተማሪ ቢደበድብ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ከትምህርት ቤት ወይም ከትምህርት ቤት አውራጃ ሊያስወጣው ይችላል።

19.6 <u>የመሣሪያ፣ ዕጽና የሠራተኛ ድብደባ ጥሰት ሂደት</u>

19.6.1 <u>ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ላሉ ሂደቶች።</u> አንድ ተማሪ ሕጋዊ አደገኛ መሣሪያ ወይም ማንኛውም ዓይነት ሌላ መሣሪያ ይዞ ከተገኘ ወይም አንድ ዕቃን ለሠራተኛ ማስፈራሪያ፣ መደብደቢያ ወይም ማጥቂያ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ ከተጠቀመ ወይም አልኮል ወይም በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ይዞ ወይም ሲያሰራጭ ቢገኝ ወይም አልኮል ወይም በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ አካባቢ ቢገኝ ቅጣቱ በጣም ከባድ ይሆናል። የሚከተለው ሂደት ይቀጥላል፡-

ሀ. የሁኔታው ተሳታፊ የነበረው ሠራተኛ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊውን እና/ወይም ረዳት ተቆጣጣሪውን ይገናኛል።

ለ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው የሚከተሉትን ያሳውቃል፡-

1. የደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር፣ እና
2. ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በስልክ፣ ከዛም በደብዳቤ እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ ማረጋገጫ ባለው ደብዳቤ፣
3. ዋና ሥራ አስኪያጅ።

ሐ. የደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ የክስተት ማሳወቂያ ይልክለታል።

መ. በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባሉት በሚመለከታቸው አቅራቦቶች መሠረት ተማሪው ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እንዲወጣ ይደረጋል።

ሠ. ሕግ በሚጣስበት ጊዜ የደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር የኬምብሪጅ ፖሊስን ያሳውቅና Middlesex County District Court (ሚድልሴክስ አውራጃ ፍርድ ቤት) ጋር አቤቱታ ካስገባ በኋላ አስፈላጊ ከሆነ ሌላ ተገቢ እርምጃ ይወስዳል።

ረ. የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት የማስወጫ ይግባኝ ሂደት ያካሂዳል።

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተማሪው የመሣሪያ ፖሊሲን እንደጣሰ ካገኘ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ከላይ በክፍሎች 14.3 (ሀ) እና/ወይም 14.3 (ለ) እንዲሁም ከክፍል 19.1 እስከ ክፍል 19.5 ውስጥ በተዘረዘረው መሠረት ተማሪውን በመሣሪያ፣ ዕጽና የትምህርት ቤት ሠራተኞች ድብደባ ምክንያት እስከ አሥር (10) ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ሊያስወጣው ይችላል። ለስንት ቀን ተማሪው መውጣት እንዳለበትና ለጥሰቱ የማባረር ሂደት ማካሄድ ያስፈልግ እንደሆነ በሚወሰንበት ጊዜ የተማሪውን የክፍል ደረጃና የጥሰቱ ዓይነት ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። በዚህ መሠረት አንድ ተማሪን ለማስወጣት የቀረቡት መመሪያዎች እንደሚከተለው ናቸው፡-

| | |
|---|---|
| ከአጸደ ሕጻናት እስከ 2ኛ ክፍል | ማስወጣት የለም፣ ሆኖም ከ ተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር የስብሰባ ቀጠሮ መያዝ |
| ከ3ኛ እስከ 5ኛ ክፍል | ከሶስት እስከ አምስት ቀን |

ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ከአምስት እስከ አሥር ቀን

እንደ ጥሰቱ ሁኔታ፣ ተማሪው ወደ ተገቢው የከተማ/ጤና ተቋም የትምህርት መርሃ ግብር ሊላክ ይችላል። ተማሪው ከትምህርት ቤት ወጥቶ ሊመለስ ሲል የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ተማሪው ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ጋር መልሶ የመግቢያ ስብሰባ እንዲያደርጉ ይጠይቃል።

ሰ. ከትምርህት ቤት በወጣበት ጊዜና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ግኝቶች አስፈላጊ መሆኑን ካሳዩ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው አፊሲዬላዊ ማባረር ይግባኝ ሂደት እንዲጀመር ያደርጋል። የማባረር ሂደቶቹን ለመጀመር የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪውንና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በትምህርት ቤት ውስጥ የይግባኝ ሂደት ዕድል እንደሚኖር በጽሑፍ ያሳውቃቸዋል። የማባረሪያው የይግባኝ ማስታወቂያ በጽሑፍ ሆኖ በእንግሊዝኛና የተማሪው የቤት ቋንቋ ሌላ ከሆነ በዛ ቋንቋም መሆን አለበት። በተጨማሪም ማስታወቂያው ከዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጣሰውን ክፍልና ጥሰቱን የሚመለከቱ ተጨባጭ ነገሮችን መዘርዘርና ተማሪው በይግባኙ ላይ የመወከል መብት እንዳለውና ማስረጃና ምስክሮች የማቅረብ ዕድል እንደሚኖረው እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ አስተርጓሚ እንደሚቀርብ መግለጽ አለበት። **የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ወይም ክፍል 504 ዕቅድ ያላቸው ተማሪዎች ከሆኑ ግን ይግባኝ የሚደረገው የተከሰተው ምግባር የተማሪው አካል ወይም አእምሮ ጉዳት መገለጫ አለመሆኑን TEAM ከገመገመ በኋላ ብቻ ነው። ከላይ ያለውን ክፍል 18.0 *ይመልከቱ*። በተጨማሪም ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚያገኝ ተማሪ ከትምህርት ቤት በወጣበት ጊዜ አግባብ ያለው ነጻ የመንግሥት ትምህርት ማግኘት አለበት። ከላይ ያለውን ክፍል 18.0 *ይመልከቱ*።**

19.6.2 <u>የመሣሪያ፣ ዕጽና ሠራተኛ ላይ ድብደባ ጥሰቶች ከአጸደ ሕጻናት እስከ 8ኛ ክፍል ያሉት ላይ የይግባኝ ሂደት።</u>

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ራሱ ተጠቂ ወይም ምስክር ካልሆነ በስተቀር ይግባኙ የሚካሄደው በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ይሆናል፣ እሱ ተጠቂው ወይም ምስክር ከሆነ ግን ረዳት ተቆጣጣሪው ወይም ሌላ ሚዛናዊ ክስተቱ በቀጥታ የማይመለከተው የትምህርት ቤቱ አስተዳደራዊ ሠራተኛ ያካሂደዋል። ይግባኙ ላይ የሚገኙት ተማሪው፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች፣ ተማሪው ሕጋዊ አማካሪ ካለው አማካሪውና ሌሎች የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው እና/ወይም ተወካዩ መገኘት አለባቸው ብሎ የገመገመው እና/ወይም ተማሪው እንዲቀርቡለት የጠየቃቸው ሰዎች።

ሀ. <u>ክሶች</u>። የይግባኝ ሹሙ ክሶቹን ይገልጽና ተማሪው ተረድቶት መሆኑን ይገመግማል።

ለ. <u>ምስክሮች</u>። ተማሪው ክሶቹን ካልተቀበለ ስለ ክስተቱ የሚያውቁ ሰዎች መጥሪያ ይላክላቸዋል። ሁሉም ቃል የሚሰጡ ምስክሮች በግል መቅረብ አለባቸው፣ ከሚከተሉት በስተቀር፦ (1) የተወንጫፊዎች ጥናት ሳይንስ ባለሙያ ቃልና የዕጽ ትንተና ባለሙያ፣ ወይም (2) የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ እና/ወይም ተወካዩ የተማሪ ምስክሩ ማንነት ቢታወቅ አደጋ ላይ ይጥለዋል ብለው ካመኑ ተማሪ ምስክር(ሮች)።

19.6.3 ይግባኙ ከተካሄደ በኋላ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተማሪውን ለማባረር ከወሰነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ለተማሪውና ለተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የውሳኔውን ምክንያቶች በጽሑፍ ይሰጣቸዋል። ይህ ማስታወቂያ ከደረሰ በኋላ በአሥር (10) ቀን ውስጥ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ጋር ተማሪው በጽሑፍ ይግባኝ ማለት እንደሚችልና ይግባኙ ላይ ተማሪው በሕግ አማካሪ መወከል እንደሚችል ማሳወቅ አለበት፣ በተጨማሪም ተማሪው ተመልሶ ሊገባ ሲል

ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ተማሪው ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ጋር የምክክር ስብሰባ እንዲያደርጉ ጥያቄ የሚያቀርብ ይሆናል።

19.6.4 ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ፊት የሚደረገው የይግባኝ ሂደት ላይ የይግባኙ ርእስ ተማሪው እዚህ *መመሪያ* ውስጥ ያለ አቅራቦት መጣሱን በሚያሳይ ተጨባጭ ግምገማ ላይ ብቻ መወሰን የለበትም። ተማሪው ይግባኙን ሲያቀርብ ቅሬታውን ገልጾ ይግባኙ የተመሠረተበትን ጉዳይ(ዮች) በአንድ መግለጫ ማቅረብና ጭብጥ ነጥቦቹን እንዲሁም የሚጠይቀውን ውጤት በግልጽ ማስቀመጥ አለበት።

በዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ፊት የሚካሄደው ይግባኝ የሚከተሉት መስፈርቶች ይኖሩታል፦

ሀ. ይግባኙ ለውጪ ሰው ክፍት ባልሆነና ኦፊሲዬላዊ ባልሆነ መንገድ የሚካሄድ ይሆናል፣

ለ. ሁሉም ወገኖች በሕጋዊ አማካሪ ወይም በሌላ በመረጡት ሰው የመወከል መብት አላቸው፣

ሐ. ሁሉም ወገኖች የትምህርት ቤት መዝገቦችንና ከይግባኙ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን መመርመር ይችላሉ፣

መ. ሁሉም ወገኖች ሁሉም ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ እንዲጠይቁ ይፈቀድላቸዋል፣

ሠ. ሁሉም ወገኖች ምስክርና ማስረጃ የማቅረብ መብት ይኖራቸዋል፣

ረ. ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ለማንኛውም የትምህርት ቤት ሠራተኛ አማካሪ ሆኖ እንዲያገለግል ወይም ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ አማካሪ ሆኖ እንዲያገለግል ሕጋዊ አማካሪ በይግባኙ ላይ እንዲገኝ ሊያደርግ ይችላል። በይግባኙ ላይ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ አማካሪ ሆኖ የሚያገለግል ሰው ለትምህርት ቤት ሠራተኛውም አማካሪ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም።

ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ተማሪው በይግባኙ ውስጥ የተጠቀሰውን ልዩ መብት(ቶች) ተነፍጎ እንደሆነ ይወስናል። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ መብቶች እንደተነፈጉ ከገመገመ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የመብት መነፈጉ ወዲያውኑና እስከመጨረሻው እንዲያቆም አስፈላጊውን ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የማስወጣቱ ጊዜ ሲያበቃ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ተማሪው ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ጋር መልሶ መግቢያ ስብሰባ እንዲያደርጉ ሊጠይቅ ይቻላል።

በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባሉ በሚመለከታቸው አቅራቦቶች መሠረት በአልኮል ወይም ዕጽ ጥሰት ምክንያት ተማሪ ለጊዜው የሚያስወጣ ወይም የሚያባርር ትምህርት ቤት፣ ተማሪው ከትምህርት ቤት ውጭ በሚሆንበት ጊዜ በክፍል 21 አንቀጽ 76 መሠረትና በዚህ *መመሪያ* ውስጥ በሚመለከታቸው አቅራቦቶች መሠረት የትምህርት አገልግሎቶች ማቅረብ መቀጠል አለበት።

በዚህ ፖሊሲ አቅራቦቶች መሠረት የተባረረ ተማሪ ሌላ ትምህርት ቤት በሚያመለክትበት ጊዜ የላኪው ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ወይም ተወካይ የተቀባዩን ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ወይም ተወካይ ተማሪው የተባረረበትን ምክንያቶች ማሳወቅ አለበት።

19.6.5 ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ላሉ ሂደቶች። አንድ ተማሪ ሕጋዊ አደገኛ መሣሪያ ወይም ማንኛውም ዓይነት ሌላ መሣሪያ ይዞ ከተገኘ ወይም አንድ ዕቃን ለሠራተኛ ማስፈራሪያ፣ መደብደቢያ ወይም ማጥቂያ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ ዝግጅት ላይ ከተጠቀመ ወይም አልኮል ወይም በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ ይዞ ወይም ሲያሰራጭ ቢገኝ ወይም አልኮል ወይም በቁጥጥር ሥር ያለ ዕጽ አካባቢ ቢገኝ ቅጣቱ በጣም ከባድ ይሆናል። የሚከተለው ሂደት ይቀጥላል፦

ሀ. የሁኔታው ተሳታፊ የነበረው ሠራተኛ የተማሪ ጉዳዮች ኃላፊን፣ ረዳት ተቆጣጣሪውን ወይም ተቆጣጣሪውን ይገናኛል።

ለ. የተማሪ ጉዳዮች ኃላፊ፣ ረዳት ተቆጣጣሪው ወይም ተቆጣጣሪው የሚከተሉትን ያሳውቃል፦

1. የደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር፣ እና
2. የ Cambridge Rindge and Latin School (ኬምብሪጅ ሪንጅ እና ላቲን ትምህርት ቤት) ተቆጣጣሪ፣ እና
3. ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በስልክ፣ ከዛም በደብዳቤ እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ ማረጋገጫ ባለው ደብዳቤ።

ሐ. የደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር ተቆጣጣሪውን እና ዋና ተቆጣጣሪውን ወይም ተወካዩን ያሳውቃል፣ የትምህርት ቀኑ ከማለቁ በፊት የክስተት ማሳወቂያ ቅጂ ለተቆጣጣሪው እና ለዋና ተቆጣጣሪውን ወይም ተወካዩ ለ ይልክለታል።

መ. በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባሉት በሚመለከታቸው አቅራቦቶች መሠረት ተማሪው ከትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እንዲወጣ ይደረጋል።

ሠ. ሕግ በሚጣስበት ጊዜ የደህንነትና ጥበቃ ዳይሬክተር የኬምብሪጅ ፖሊስን ያሳውቅና Middlesex County District Court (ሚድልሴክስ አውራጃ ፍርድ ቤት) ጋር አቤቱታ ካስገባ በኋላ አስፈላጊ ከሆነ ሌላ ተገቢ እርምጃ ይወስዳል።

ረ. ተቆጣጣሪው በዚህ መመሪያ ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት የማስወጫ ይግባኝ ሂደት ያካሂዳል።

ሰ. ተቆጣጣሪው ተማሪው የመሣሪያ፣ ዕጽ ወይም የትምህርት ቤት ሠራተኛ ድብደባ ፖሊሲዎችን እንደጣሰ ካገኘ ተቆጣጣሪው በዚህ መመሪያ ውስጥ ባሉት በተገቢዎቹ አቅራቦቶች መሠረት ተማሪውን በመሣሪያ፣ ዕጽና የትምህርት ቤት ሠራተኞች ድብደባ ምክንያት ከአምስት (5) እስከ አሥር (10) ቀን ድረስ ከትምህርት ቤት ሊያስወጣውና የማባረሪያ ሂደት ሊጀምር ይችላል። የማስወጫ ደብዳቤው ግልባጮች ለዋና ሥራ አስኪያጁ፣ ለተቆጣጣሪው፣ ለጥበቃና ለአማካሪ ይላካሉ። እንደ ጥሰቱ ዓይነት፣ ተማሪው ወደ ተገቢው የከተማ/ጤና ትምህርት መርሃ ግብር ሊላክ ይችላል። ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት ሊመለስ ሲል ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ተማሪው ከተቆጣጣሪው ጋር መልሶ መግቢያ የምክክር ስብሰባ እንዲያደርጉ ይጠይቃል።

ሸ. ከትምርህት ቤት በወጣበት ጊዜና የተቆጣጣሪው ግኝቶች አስፈላጊ መሆኑን ካሳዩ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ኦፊሴላዊ ማባረር ይግባኝ ሂደት እንዲጀምር ያደርጋል። የማባረር ሂደቶቹን ለመጀመር ተቆጣጣሪው ተማሪውንና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን በትምህርት ቤት ውስጥ የይግባኝ ሂደት ዕድል እንደሚኖር በጽሑፍ ያሳውቃቸዋል። የማባረሪያው የይግባኝ ማስታወቂያ በጽሑፍ ሆኖ በእንግሊዝኛና የተማሪው የቤት ቋንቋ ሌላ ከሆነ በዛ ቋንቋም መሆን አለበት። በተጨማሪም ማስታወቂያው ከዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጣሰውን ክፍልና ጥሰቱን የሚመለከቱ ተጨባጭ ነገሮችን መዘርዘርና ተማሪው በይግባኙ ላይ የመወከል መብት እንዳለውና ማስረጃና ምስክሮች የማቅረብ ዕድል እንደሚኖረው እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ አስተርጓሚ እንደሚቀርብ መግለጽ አለበት። **የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ወይም ክፍል 504 ዕቅድ ያላቸው ተማሪዎች ከሆኑ ግን ይግባኝ የሚደረገው የተከሰተው ምግባር የተማሪው አካል ወይም አእምሮ ጉዳት መገለጫ አለመሆኑን TEAM ከገመገመ በኋላ ብቻ ነው። ከላይ ያለውን ክፍል 18.0 *ይመልከቱ*። በተጨማሪም ልዩ**

**ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚያገኝ ተማሪ ከትምህርት ቤት በወጣበት ጊዜ አግባብ ያለው ነጻ የመንግሥት ትምህርት ማግኘት አለበት። ከላይ ያለውን ክፍል 18.0 *ይመልከቱ።***

19.6.6 <u>*የመሣሪያ፣ ዕጽና ሡራተኛ ላይ ድብደባ ጥሰቶች ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት ላይ የይግባኝ ሂደት።*</u>

*ተቆጣጣሪው ራሱ ተጠቂ ወይም ምስክር ካልሆነ በስተቀር ይግባኙ የሚካሄደው በተቆጣጣሪው ይሆናል፣ እሱ ተጠቂው ወይም ምስክር ከሆነ ግን ረዳት ተቆጣጣሪው ወይም ሌላ ሚዛናዊ ክስተቱ በቀጥታ የማይመለከተው የትምህርት ቤቱ አስተዳደራዊ ሡራተኛ ያካሂደዋል። ይግባኙ ላይ የሚገኙት ተማሪው፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች እና/ወይም ተወካይ እና/ወይም ተማሪው እንዲቀርቡለት የጠየቃቸው ሰዎች።*

*ሀ.* <u>ክሶች።</u> *የይግባኝ ሹሙ ክሶቹን ይገልጽና ተማሪው ተረድቶት መሆኑን ይገመግማል።*

ለ. <u>ምስክሮች።</u> *ተማሪው ክሶቹን ካልተቀበለ ስለ ክስተቱ የሚያውቁ ሰዎች መጥሪያ ይላክላቸዋል። ሁሉም ቃል የሚሰጡ ምስክሮች በግል መቅረብ አለባቸው፣ ከሚከተሉት በስተቀር፦* (1) *የተወንጫፊዎች ጥናት ሳይንስ ባለሙያ ቃልና የዕጽ ትንተና ባለሙያ፣ ወይም* (2) *ተቆጣጣሪው እና/ወይም ተወካዩ የተማሪ ምስክሩ ማንነት ቢታወቅ አደጋ ላይ ይጥለዋል ብለው ካመኑ ተማሪ ምስክር(ሮች)።*

*ይግባኙ ከተካሄደ በኋላ ተቆጣጣሪው ተማሪውን ለማባረር ከወሰነ ተቆጣጣሪው ለተማሪውና ለተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ ባሉት ተገቢዎቹ አቅራቦቶች መሠረት የውሳኔውን ምክንያቶች በጽሑፍ ይሰጣቸዋል። ከይግባኙ በኋላ ተቆጣጣሪው ተማሪውን ከማባረር ይልቅ ለጊዜው አስወጥቶ አማራጭ መርሃ ግብር ጋር ሊልከው ይችላል። የሚላከው ማስታወቂያ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ጋር ተማሪው በጽሑፍ ይግባኝ ማለት እንደሚችል እዚህ መመሪያ ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ማሳወቅ አለበት።*

19.6.7 *ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ፊት የሚደረገው የይግባኝ ሂደት ላይ የይግባኙ ርእስ ተማሪው እዚህ መመሪያ ውስጥ ያለ አቅራቦት መጣሱን በሚያሳይ ተጨባጭ ግምገማ ላይ ብቻ መወሰን የለበትም። ተማሪው ይግባኙን ሲያቀርብ ቅሬታውን ገልጾ ይግባኙ የተመሠረተበትን ጉዳይ(ዮች) በአንድ መግለጫ ማቅረብና ጭብጥ ነጥቦቹን እንዲሁም የሚጠይቀውን ውጤት በግልጽ ማስቀመጥ አለበት።*

*በዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ፊት የሚካሄደው ይግባኝ የሚከተሉት መስፈርቶች ይኖሩታል፦*

*ሀ.* *ይግባኙ ለውጪ ሰው ክፍት ባልሆነና ኦፊሲዬላዊ ባልሆነ መንገድ የሚካሄድ ይሆናል፣*

*ለ.* *ሁሉም ወገኖች በሕጋዊ አማካሪ ወይም በሌላ በመረጡት ሰው የመወከል መብት አላቸው፣*

*ሐ.* *ሁሉም ወገኖች የትምህርት ቤት መዝገቦችንና ከይግባኙ ጋር የተያያዙ ሰነዶችን መመርመር ይችላሉ፣*

*መ.* *ሁሉም ወገኖች ሁሉም ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ እንዲጠይቁ ይፈቀድላቸዋል፣*

*ሠ.* *ሁሉም ወገኖች ምስክርና ማስረጃ የማቅረብ መብት ይኖራቸዋል፣*

ረ. ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ለማንኛውም የትምህርት ቤት ሠራተኛ አማካሪ ሆኖ እንዲያገለግል ወይም ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ አማካሪ ሆኖ እንዲያገለግል ሕጋዊ አማካሪ በይግባኙ ላይ እንዲገኝ ሊያደርግ ይችላል። በይግባኙ ላይ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ አማካሪ ሆኖ የሚያገለግል ሰው ለትምህርት ቤት ሠራተኛውም አማካሪ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም።

ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ተማሪው በይግባኙ ውስጥ የተጠቀሰውን ልዩ መብት(ቶች) ተነፍጎ እንደሆነ ይወስናል። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ መብቶች እንደተነፈጉ ከገመገመ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የመብት መነፈጉ ወዲያውኑና እስከመጨረሻው እንዲያቆም አስፈላጊውን ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የማስወጣቱ ጊዜ ሲያበቃ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ተማሪው ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ጋር መልሶ መግቢያ ስብሰባ እንዲያደርጉ ሊጠይቅ ይቻላል።

በዚህ ፖሊሲ አቅራቦቶች መሠረት የተባረረ ተማሪ ሌላ ትምህርት ቤት በሚያመለክትበት ጊዜ የላኪው ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ወይም ተወካይ የተቀባዩን ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ወይም ተወካይ ተማሪው የተባረረበትን ምክንያቶች ማሳወቅ አለበት።

በዚህ መመሪያ ውስጥ ባሉ በሚመለከታቸው አቅራቦቶች መሠረት በአልኮል ወይም ዕጽ ጥሰት ምክንያት ተማሪ ለጊዜው የሚያስወጣ ወይም የሚያባርር ትምህርት ቤት፣ ተማሪው ከትምህርት ቤት ውጭ በሚሆንበት ጊዜ በክፍል 21 አንቀጽ 76 መሠረትና በዚህ መመሪያ ውስጥ በሚመለከታቸው አቅራቦቶች መሠረት የትምህርት አገልግሎቶች ማቅረብ መቀጠል አለበት።

## 20.0 ከትምህርት ቤት ውጪ ምግባር

20.1 የMassachusetts General Laws (የማሳቹሴትስ አጠቃላይ ሕጎች) አንቀጽ 71፣ ክፍል 37H½ የአንድ ትምህርት ቤት ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ በከፍተኛ ወንጀል የተከሰሰ ተማሪን ወይም የከፍተኛ ወንጀል ኃላፊነት ስላልተወጣ ክስ ያለበት ተማሪን፣ ክስተቱ የተከሰተው ትምህርት ቤት ቢሆንም፣ ከትምህርት ቤት ጋር የተያያዘ እንቅስቃሴ ላይ ቢሆንም የተማሪው ትምህርት ቤት መቆየት ለትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ደህንነት አስጊ ነው ብሎ ከደመደመ ለጊዜው እንዲያስወጣው ይፈቅዳል። ክፍል 37H½ እንዲሁም በከፍተኛ ወንጀል ተከሶ የተፈረደበትን ተማሪ ወይም የከፍተኛ ወንጀል ኃላፊነት ስላልተወጣ የተፈረደበት ተማሪን ወይም ጥፋት ያመነ ተማሪን የተማሪው ትምህርት ቤት መቆየት ለትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ደህንነት አስጊ ነው ብሎ ከደመደመ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪውን ማባረር ይችላል።

**የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ወይም ክፍል 504 ዕቅድ ያላቸው ተማሪዎች ከሆኑ ግን ይግባኝ የሚደረገው የተከሰተው ምግባር የተማሪው አካል ወይም አእምሮ ጉዳት መገለጫ አለመሆኑን TEAM ከገመገመ በኋላ ብቻ ነው። ከላይ ያለውን ክፍል 18.0 *ይመልከቱ*። በተጨማሪም ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚያገኝ ተማሪ ከትምህርት ቤት በወጣበት ጊዜ አግባብ ያለው ነጻ የመንግሥት ትምህርት ማግኘት አለበት። ከላይ ያለውን ክፍል 18.0 *ይመልከቱ*።**

ማንኛውም በ M.G.L.c. 71, §37H ½ውስጥ ባሉት አቅራቦቶች መሠረት ከትምህርት ቤት ለጊዜው ያስወጡት ተማሪ ከዚህ በታች በክፍል 21 ውስጥ ባለው መሠረት የትምህርት አገልግሎቶች የማግኘትና በትምህርቱ የመግፋት ዕድል አለው።

20.2 የጊዜው ርዝመት ላልተወሰነ ጊዜ የሚደረጉ የማስወጣቶችን ሂደቶች እና/ወይም የማባረር ሂደቶችን በተመለከተ በ M.G.L.c. 71, §37H½ ሥር ባሉት አቅራቦቶች መሠረት የሚከተሉትን ሂደቶች መከተል ያስፈልጋል፦

ሀ. ከ10 ቀን በታች ከሆነ ተማሪው ከትምህርት ቤት የሚወጣው፣ በዛን ወቅት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ምግባሩ ወይ ላልተወሰነ ጊዜ ከትምህርት ቤት የሚያስወጣ ነው ወይ እስከመጨረሻ የሚያስባርር ነው ብሎ ከወሰነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪውንና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ትምህርት ቤት ውስጥ ይግባኝ እንደሚደረግ ያሳውቃቸዋል። ማስታወቂያው በእንግሊዝኛና የተማሪው የቤት ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ሌላ ከሆነ በዛም ቋንቋ መላክ አለበት። በተጨማሪም ማስታወቂያው ከዚህ *መመሪያ* ውስጥ የተጣሰውን ክፍልና ጥሰቱን የሚመለከቱ ተጨባጭ ነገሮችን መዘርዘርና ተማሪው በይግባኙ ላይ የመወከል መብት እንዳለውና ማስረጃና ምስክሮች የማቅረብ ዕድል እንደሚኖረው እንዲሁም አስፈላጊ ከሆነ አስተርጓሚ እንደሚቀርብ መግለጽ አለበት። **የግል ትምህርት መርሃ ግብር (IEP) ወይም ክፍል 504 ዕቅድ ያላቸው ተማሪዎች ከሆኑ ግን ይግባኝ የሚደረገው የተከሰተው ምግባር የተማሪው አካል ወይም አእምሮ ጉዳት መገለጫ አለመሆኑን TEAM ከገመገመ በኋላ ብቻ ነው። ከላይ ያለውን ክፍል 18.0 *ይመልከቱ*። በተጨማሪም ልዩ ትምህርትና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚያገኝ ተማሪ ከትምህርት ቤት በወጣበት ጊዜ አግባብ ያለው ነጻ የመንግሥት ትምህርት ማግኘት አለበት። ከላይ ያለውን ክፍል 18.0 *ይመልከቱ*።**

ለ. <u>የይግባኝ ሂደት።</u>

የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው እራሱ ተጠቂ ወይም ምስክር ካልሆነ በስተቀር ይግባኙ የሚካሄደው በከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ይሆናል፣ እሱ ተጠቂው ወይም ምስክር ከሆነ ግን ረዳት ተቆጣጣሪው ወይም ሌላ ሚዛናዊ ክስተቱ በቀጥታ የማይመለከተው የትምህርት ቤቱ አስተዳደራዊ ሠራተኛ ያካሂደዋል። ይግባኙ ላይ የሚገኙት ተማሪው፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች፣ ተማሪው ሕጋዊ አማካሪ ካለው አማካሪውና ሌሎች የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው እና/ወይም ተወካዩ መገኘት አለባቸው ብሎ የገመገመው እና/ወይም ተማሪው እንዲቀርቡለት የጠየቃቸው ሰዎች።

1. <u>ክሶች።</u> የይግባኝ ሹሙ ክሶቹን ይገልጽና ተማሪው ተረድቶት መሆኑን ይገመግማል።
2. <u>ምስክሮች።</u> ተማሪው ክሶቹን ካልተቀበለ ስለ ክስተቱ የሚያውቁ ሰዎች መጥሪያ ይላክላቸዋል። ሁሉም ቃል የሚሰጡ ምስክሮች በግል መቅረብ አለባቸው፣ ከሚከተሉት በስተቀር፦ (1) የተወንጫፊዎች ጥናት ሳይንስ ባለሙያ ቃልና የዕጽ ትንተና ባለሙያ፣ ወይም (2) የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ እና/ወይም ተወካዩ የተማሪ ምስክሩ ማንነት ቢታወቅ አደጋ ላይ ይጥለዋል ብለው ካመኑ ተማሪ ምስክር(ሮች)።

ሐ. ይግባኙ ከተካሄደ በኋላ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ተማሪውን ለማባረር ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ለማስወጣት ከወሰነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ለተማሪውና ለተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የውሳኔውን ምክንያቶች በጽሑፍ ይሰጣቸዋል። ይህ ማስታወቂያ ከደረሰ በኋላ በአምስት (5) ቀን ውስጥ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ጋር ተማሪው በጽሑፍ ይግባኝ ማለት እንደሚችልና ይግባኙ ላይ ተማሪው በሕግ አማካሪ መወከል እንደሚችል ማሳወቅ አለበት። በተጨማሪም የተማሪው ማስወጣት ወይም ማባረር ጊዜ ሊያበቃፍ ሲል ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ተማሪው ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ጋር የምክክር ስብሰባ እንዲያደርጉ ጥያቄ የሚያቀርብ ይሆናል።

## 21.0 ከትምህርት ቤት በወጡበት ጊዜ ትምህርታዊ አገልግሎቶችና የትምህርት ሂደት

21.1 ማንኛውም በትምህርት ቤት ውስጥ ሆኖ እንዲወጣ፣ ለአጭር ጊዜ እንዲወጣ፣ ለረጅም ጊዜ እንዲወጣ ወይም እንዲባረር የተደረገ ተማሪ ከትምህርት ቤት በወጣበት ወቅት የትምህርት ሂደቱን ለማስቀጠል

ክሬዲት የማግኘት፣ የቤት ሥራዎችን የማካካስ፣ ፈተናዎችን የመውሰድ እና ፕሮጀክቶች የመሥራት ዕድል ይኖረዋል። ማንኛውም በትምህርት ቤት ውስጥም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጪ ከአሥር ተከታታይ ቀኖች በላይ የተባረረ ወይም እንዲወጣ የተደረገ ተማሪ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ባጎለበተው የትምህርት አገልግሎት ዕቅድ አማካኝነት ትምህርታዊ አገልግሎቶች የማግኘትና የስቴትና የአካባቢውን መስፈርቶች ለማሟላት የሚያስፈልገውን ትምህርታዊ ሂደት የማድረግ ዕድለ ይኖረዋል። ማስወጣቱ ወይም ማባረሩ እንደተወሰነ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ተማሪውንና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችን ይህ ዕድል እንዳለ ያሳውቃል።

21.2 ይህ የትምህርት አገልግሎት ዕቅድ የትምህርት ቤት አውራጃው ከአሥር(10) ተከታታይ ቀናት በላይ ለተባረሩ ወይም እንዲወጡ ለተደረጉ ተማሪዎች የሚያቀርባቸውን የትምህርት አገልግሎቶች መዘርዘርና ተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች እንዲያውቁ የሚደረግበትን መንገድና እነዚህ አገልግሎቶች የሚመቻቹበትን መንገድ ማሳወቅ አለበት። የትምህርት አገልግሎቶች የሚሰጡት ለሁሉም ተማሪዎች በስቴት ሕግና ደንቦች መሠረት በሚሰጠው የትምህርት ደረጃዎችና ሥርዓት መሠረት ነው።

## 22.0 ማባረር

22.1 ማንኛውም ተማሪ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ባለው ሂደት መሠረት ካልሆነ በስተቀር በምንም ዓይነት መንገድ ወይም ለምንም ያህል ጊዜ ያለ ፍላጎቱ ከትምህርት ቤት ሊገለል አይችልም፤ ሆኖም ተማሪው ተላላፊ በሽታ ወይም ሌላ ለሕዝብ ጤና ጠንቅ የሆነ ሕመም ካለው፣ ወይም የክትባት ሰርተፊኬት ካላቀረበ ሊገለል ይችላል፣ ይህ ከሆነ ደሞ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ወዲያውኑ እንዲያውቁ ይደረግና ተማሪው ወደ ቤት ይላካል፣ ሆኖም ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በሕክምናና በኃይማኖት ምክንያት ከዚህ ግዴታ ነጻ እንደሆኑ ማሳወቅ ይችላሉ። ክትባት የሌላቸው ወይም በከፊል ክትባት ያላቸውና የሕክምና ወይም የኃይማኖት ምክንያት የሌላቸው ልጆች ከዚህ ግዴታ ነጻ መሆን የሚችሉት ቤት አልባ ከሆኑ ብቻ ነው። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊና የትምህርት ቤት ነርስ ከወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ጋር ስለ ተማሪው ወደ ትምህርት ቤት መመለስ አብረው ይመክራሉ።

22.2 ዕድሜው አሥራ ስድስት (16) ዓመት ወይም ከዛ በላይ የሆነ ተማሪ በፍላጎቱ ትምህርት ቤት መልቀቅ ከፈለገ፣ ተማሪው ትምህርት ቤት መሄድ ባቆመ በሰባት (7) ቀን ውስጥ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ተወካዩ ለተማሪው ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች የጽሑፍ ማስታወቂያ በእንግሊዝኛና የተማሪው የቤት ቋንቋ ከእንግሊዝኛ ሌላ ከሆነ በዛም ቋንቋ ልኮ ተማሪው በቋሚነት ትምህርት ቤቱን ከመልቀቁ በፊት ተማሪውና ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ ወይም ከተወካዩ ጋር እንዲገናኙ ጥይቁ ያቀርባል።

22.3 የመውጫ ቃለ መጠይቅ። አስፈላጊ ከሆነ ደብዳቤው ማረጋገጫ ባለው ፖስት መላክ አለበት። የዚህ ስብሰባ ዓላማ ተማሪው ትምህርት ቤት የሚለቅበትን ምክንያቶች፣ የተማሪውን መዝገብና የተማሪውን የወደፊት የትምህርት ወይም የሥራ ዕቅዶች ለመቃኘትና ተማሪው በገዛ ፈቃዱ እንደሆነ የሚለቀው ለመገምገም፣ ተማሪው ትምህርት ቤት እንዲለቅ ግፊት ያደረገበት ማንም የትምህርት ቤት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነው።

22.4 ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች እና/ወይም ተማሪው የመውጫ ቃለ መጠይቅ እንዲደረግለት ለመጠየቅ በአሥር (10) ቀን ውስጥ መልስ ካልሰጡ፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ተወካዩ ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ተማሪው ከትምህርት ቤት መዝገብ ሊሰረዝ እንደሚችል የሚያሳውቅ ማስታወሻ ይልክላቸዋል።

22.5 ይህ ክፍል በቋሚነት ማግለል ሲል ወደፊት ትምህርቱን መቀጠል የሚፈልግ ተማሪን አይመለከትም። ተማሪው ዕድሜው ሃያ አንድ (21) ዓመት ከመሙላቱ በፊት መልሶ መግቢያ የምክክር ስብሰባ ለማድረግ

የጽሑፍ ማመልከቻ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ጋር አስገብቶ በማንኛውም ቀጣይ ሰሚስተር መጀመሪያ ላይ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ይችላል።

22.6 የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ኃላፊው ወይም ረዳት ተቆጣጣሪው የስቴቱ የትምህርት ቦርድ ባወጣቸው ደንቦች መሠረት፣ ለአንድ (1) ወር በተከታታይ ወይም ከዛ በላይ የሚወጡ ተማሪዎችን፣ በመባረርም ምክንያት ሆነ፣ በሕመም፣ አውቀው ወይም በማንኛውም ምክንያት ቢሆን መዝገብ ይይዛል። ይህ መዝገብ ስም፣ ዕድሜ፣ ዘር፣ ጾታ፣ አድራሻ፣ የክፍል ደረጃ፣ ተማሪው ትምህርት ቤት በመደበኛ ሁኔታ መምጣት ያቆመበትን ቀንና ተማሪው ትምህርት ቤት መምጣት ያቆመበትን ምክንያት ያካትታል። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ እና/ወይም ረዳት ተቆጣጣሪ ዓመታዊ ሪፖርት ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩና ለትምህርት ቤት ኮሚቴው ያደርጋል፣ ይህም ትምህርት ቤቱን ለአንድ (1) ወር ወይም ከዛ በላይ የለቀቁ ተማሪዎችን ባጭሩ የሚገልጽ ሲሆን የተማሪዎችን ማንነት ግን አይገልጽም።

## 23.0 የመብት ንፍገትን ለማስተካከል ይግባኝ የማለት መብት

23.1 አንድ የትምህርት ቤት መምሪያ ባለ ሥልጣን ወይም ሠራተኛ ተማሪውን ማንኛውም እዚህ መመሪያ ውስጥ ያለ መብትን ነፍጎታል ብለው ተማሪው እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ካመኑና ተማሪው እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ቅሬታውን ከከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊው ወይም ከሌሎች የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣናት ጋር በቀና ልብ ኦፊሲዬላዊ ባልሆኑ መንገዶች መፍታት ካልቻሉ፣ ተማሪው እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ዋና ተቆጣጣሪው ጋር ወይም ዋና ሥራ አስኪያጁ ጋር በጽሑፍ ይግባኝ የማለት መብት አላቸው። በጽሑፍ የሚቀርበው ይግባኝ ቅሬታው ምን እንደሆነ ገልጾ፣ የትኛው መብት እንደሆነ የተነፈገው በግልጽ አቅርቦ ጭብጥ ነጥቦቹን እንዲሁም የሚጠይቀውን ውጤት በአንድ መግለጫ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት።

23.2 ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ወይም ዋና ሥራ አስኪያጁ ምርመራ አድርገው ክሱ ቁም ነገር የለውም ወይም ተገቢ አይደለም ብለው ካልወሰኑ በስተቀር ወይም ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ወይም ዋና ሥራ አስኪያጁ ቅሬታውን አቤት ለባዩ አጥጋቢ በሆነ መንገድ የጽሑፍ ይግባኙ በደረሰው በሰባት (7) የትምህርት ቀን ውስጥ መፍታት ካልቻለ በስተቀር፣ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ወይም ዋና ሥራ አስኪያጁ ለትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዋና ኃላፊ፣ በጽሑፍ የቀረበው ይግባኝ ውስጥ በስም የተጠቀሰ የትምህርት ቤት መምሪያ ሠራተኛ(ዎች) ካለ ለእርሱ እና ይግባኙን ላስገባው ተማሪ እና ለወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎች ማስታወቂያ ይልካል። ይህ ዓይነቱ ማስታወቂያ የሚከተለውን መያዝ አለበት፡-

ሀ. ይግባኙ በደረሰ በአሥር (10) የትምህርት ቀን ውስጥ የሚካሄደውን ስብሰባ ሰዓትና ቦታ፣ አንደኛው ወገን ለይግባኙ ለመዘጋጀት እስከ አምስት (5) ተጨማሪ የትምህርት ቀን ይሰጠኝ ካላለ በስተቀር፣

ለ. በጽሑፍ የቀረበው ይግባኝ ውስጥ በተጠቀሰው መሠረት የቅሬታው ገለጻ፣

ሐ. ወደ ክስ(ሶች) ያመራውን ጭብጥ ነጥቦች፣ የምስክሮችን ስሞች ጨምሮ የሚገልጽ ሙሉ መግለጫ፣

መ. የሚፈለገው መፍትሄ መግለጫ፣

ሠ. የሁሉንም ወገኖች መብት የሚገልጽ መግለጫ፣ ስብሰባው ላይ ጠበቃ ወይም ሌላ ሰው መወከል እንደሚቻል፣ ምስክሮችና ማስረጃ ማቅረብ እንዲሁም ተቃዋሚ ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብትን ማካተት አለበት።

23.3 ስብሰባው የሚከተሉት መስፈርቶች ይኖሩታል፡-

ሀ. ስብሰባው የሚካሄደው በዋና ተቆጣጣሪው ወይም በተወካዩ ፊት ይሆናል፣

ለ. ይግባኙ ለውጪ ሰው ክፍት ባልሆነና ኦፊሲዬላዊ ባልሆነ መንገድ የሚካሄድ ይሆናል፣

ሐ. ሁሉም ወገኖች በሕጋዊ አማካሪ ወይም በሌላ በመረጡት ሰው የመወከል መብት አላቸው፣

መ. ሁሉም ወገኖች የትምህርት ቤት መዝገቦችንና ከቅሬታው ጋር የተያያዙ ሰነዶችን መመርመር ይችላሉ፣

ሠ. ሁሉም ወገኖች ሁሉም ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ እንዲጠይቁ ይፈቀድላቸዋል፣

ረ. ሁሉም ወገኖች ምስክርና ማስረጃ የማቅረብ መብት ይኖራቸዋል፣

ሰ. ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ለማንኛውም የትምህርት ቤት ሠራተኛ አማካሪ ሆኖ እንዲያገለግል ወይም ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ አማካሪ ሆኖ እንዲያገለግል ሕጋዊ አማካሪ በይግባኙ ላይ እንዲገኝ ሊያደርግ ይችላል። በይግባኙ ላይ ለዋና ተቆጣጣሪው ወይም ለተወካዩ አማካሪ ሆኖ የሚያገለግል ሰው ለትምህርት ቤት ሠራተኛውም አማካሪ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም።

23.4 ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ ተማሪው በጽሑፍ የቀረበው ቅሬታ ውስጥ የተጠቀሰውን/የተጠቀሱትን ልዩ መብት(ቶች) ተነፍጎ እንደሆነ ይወስናል። ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ መብቶች እንደተነፈጉ ከገመገመ ዋና ተቆጣጣሪው ወይም ተወካዩ የመብት መነፈጉ ወዲያውኑና እስከመጨረሻው እንዲያቆም አስፈላጊውን ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋሉ። ተገቢውን መፍትሄ በመገምገሚያ ጊዜ፣ የተማሪዎች የተለያዩ የግል ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው በተለይም በሚከትሉት ላይ ያተኩሩት፡- ዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ፣ አካላዊ ገጽታ፣ የወላጅንነት ሁኔታ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚ ሁኔታ እና ቤት አልባነት፣ እንዲሁም የተማሪው እኩልነት፣ ቋንቋ፣ ማህበራዊ፣ስሜታዊ ደህንነትና ቴክኖሎጂ።

23.5 እዚህ ክፍል ውስጥ ከሉት አቅራቦቶች ባሻገር፣ አንድ ተማሪ በሕግ በተጠበቁት ልዩ ምልክቶች ማለትም በዘር፣ ቀለም፣ ዜግነት፣ ዘር ማንዘር፣ ኃይማኖት፣ ዕድሜ፣ አካል ብቃት፣ የሥነ ዘር መረጃ፣ ውትድርና ውስጥ በፊት በማገልገል፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታ፣ መታወቂያ ጾታ፣ የጓደኛ ጾታ ምርጫ፣ ነፍሰ ጡርነት፣ ወይም ከነፍሰ ጡርነት ጋር የተያያዘ ሁኔታ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያው ሁኔታ ወይም ቤት አልባነት ላይ የተመሠረተ አቤቱታ ካለው የ Cambridge Public Schools “Non-Discrimination Policy and Prohibition Against Sexual Harassment”ን (የኬምብሪጅ መንግሥት ትምህርት ቤቶች “ጸረ-አድሎ ፖሊሲና የጾታ ጉትጎታ ክልከላ”) የአቤቱታ ሂደትን መጠቀም ይችላል፤ አንድ ተማሪ በዚህ *መመሪያ* ውስጥ ያለውን የይግባኝ ሂደት ተጠቅሞ ከተማሪ ቅጣት ጋር ለተያያዙ ይግባኞች መፍትሄ መፈለግ ይችላል፤ እንዲሁም አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት አውራጃው ጸረ-አስፈራሪ የተማሪዎች ፖሊሲና የአስፈራሪ ተማሪዎች ማገጃና መፍትሄ ማምጫ ዕቅድ ውስጥ ያለውን የይግባኝ ሂደት ተጠቅሞ ማስፈራራትን በተመለከተ ላሉ ክሶች መፍትሄ ለማምጣት መሞከር ይችላል።

23.6 ማንም በዋና ተቆጣጣሪው ወይም በተወካዩ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን በትምህርት ቤት ኮሚቴው ፊት ይግባኝ ማለት ይችላል። ሆኖም እንደዚህ ዓይነት የይግባኝ መብት በስቴቱ ሕግ መሠረት የዋና ተቆጣጣሪው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ነው የሚላቸው ውሳኔዎችና ሐሳቦችን አይመለከትም። የትምህርት ቤት ኮሚቴው ፊት ይግባኝ ይደረግልኝ ተብሎ የሚቀርበው ጥያቄ የዋና ተቆጣጣሪው ውሳኔ በደረሰ በአምስት (5) የትምህርት ቤት ቀኖች ውስጥ መሆን አለበት።

23.7 የትምህርት ቤት ኮሚቴው የሙብት ንፍገት(ቶች) አለ ለተባለው በቂ ማስረጃ መኖሩንና የተሰጠው መፍትሄ ለንፍገቱ (ቶቹ) አግባብ መሆኑን ለመወሰን የትምህርት ቤት ኮሚቴው የዋና ተቆጣጣሪውን ግኝቶችና ውሳኔዎችና ሐሳቦች ይቃኛል። ይግባኙ ከተካሄደ በኋላ በአሥር (10) ቀን ውስጥ የትምህርት ቤት ኮሚቴው የጽሑፍ ውሳኔ ያስተላልፋል፣ ይህ ውሳኔ የዋና ተቆጣጣሪውን ወይም የተወካዩን ውሳኔ የሚደግፍ፣ የሚለውጥ ወይም የሚያሻሽል ይሆናል።.

23.8 ሁሉም ወገኖችና ተወካዮቻቸው፣ ጠበቃውንም ጨምሮ፣ ይግባኙ ላይ የቀረበውን ማስረጃና የመፍትሄውን አግባብነት በተመለከተ የትምህርት ቤት ኮሚቴውን ማነጋገር ይችላሉ። የትምህርት ቤት ኮሚቴው ፈቃደኛ ከሆነ ምስክሮች መስማትና ተጨማሪ ማስረጃ መቀበል ይችላል።

## 24.0 የተማሪ መመሪያ መጽሐፎች

ተጨማሪ የምግባር ደንቦች በCambridge Rindge and Latin School Student Handbook (የኬምብሪጅ ሪንጅና ላቲን ትምህርት ቤት የተማሪ መመሪያ መጽሐፍ) ውስጥና የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተማሪ መመሪያ መጽሐፍ ውስጥ ታትመዋል። የተማሪ ሕይወትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሁሉም ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች/ተንከባካቢዎችና ሠራተኞች እነዚህን መመሪያ መጽሐፎች ማየት አለባቸው።

**ተጨማሪ መግለጫ ሀ**